

OSSE

# የኮሎምቢያ ግዛት የመጀመሪያ ትምህርት መስፈርቶች 2019

## የኮሎምቢያ ግዛት የመጀመሪያ ትምህርት መስፈርቶች መግቢያ

ይህ የተሻሻለው *የኮሎምቢያ ግዛት የመጀመሪያ ትምህርት መስፈርቶች* እትም በመላው አገሪቷ ያለው የቀዳሚ እንክብካቤ እና ትምህርት የመስፈርቶች ለውጥ እንቅሳቃሴ ምላሽ ነው። የ *የመጀመሪያ የመማር መስፈርቶች* ከ *Common Core State Standards for English Language Arts and Mathematics* (2010) እንዲሁም ከ Next Generation Science Standards *(የቀጣይ ትውልድ የሳይንስ መስፈርቶች)* (2013) ጋር መተካከልን ያካትታል። በተጨማሪ መስፈርቶቹ ከ *Head Start Early Learning Outcomes Framework Ages Birth to Five* (2015) ጋር የሚስተካከሉ ናቸው፣ ይህም ሁሉም ልጆች የፕሮግራሙ መግለጫዎች ምንም ይሁኑ ተመሳሳይ የሆነ መስፍርቶችን መሰረት ያደረገ ትምህርት እና ተገቢ የሆነ የመማር ልምዶችን ማግኘታቸውን ያረጋግጣል።

የ *ኮሎምቢያ ግዛት የመጀመሪያ የመማር መስፈርቶች*፣ በዚህ ሰነድ ውስጥ በሙሉ የመጀመሪያ የመማር መስፈርቶች ተብሎ ሪፈር የተደረገው፣ ለጨቅላ ህጻናት፣ ለታዳጊዎች፣ ሁለት አመት ልጆች እና ቅድመ ትምህርት ቤት ያሉ ልጆች መለኪያዎችን ፣ እንዲሁም ቅድመ መዋእለ ህጻናት እና መዋእለህጻናትን ከሚለቁ ህጻናት የሚጠበቁ ነገሮችን ያካትታል። እነዚህ መስፈርቶች ልጆች ሊያውቋቸው እና ሊያደርጓቸው የሚችሉትን ነገሮች እና በተለያዩ እድሜዎች እና የእድገት ደረጃዎች ልጆች እንዴት እንደሚያድጉ ለወላጆች እና ለአስተማሪዎች መረጃ ይሰጣሉ። እነሱ በልጁ ላይ በሙሉ ያተኩራሉ እናም የወጣት ልጆች ትምህርት እና እድገት እርስ በእርስ የተዛመዱ እና ሁሉንም የትምህርት ስፍራዎች ስለሚነኩ ሰፋ ያለ ማእቀፍ ያላቸውን ጎራዎችን ያካትታሉ። *የመጀመሪያ ትምህርት መስፈርቶች* አስተማሪው ከቤተሰቦች ጋር በመተባበር በከፍተኛ ጥራት ባለው የመጀመሪያ እንክብካቤ እና የትምህርት አከባቢ የታቀደ የልጆች ትምህርት እና እድገትን ለመምራት ያለውን አስፈላጊ ሚና እውቅና ይሰጣል።

የ *መጀመሪያ ትምህርት መስፈርቶች* ትናንሽ ልጆች እንዲያድጉ፣ እንዲማሩ እና በመጨረሻም ለትምህርት ቤት ዝግጁ እንዲሆኑ ባለው ሂደት ውስጥ አስተማሪዎች ቁልፍ ውሳኔ ሰጪዎች መሆናቸውን ይገነዘባል። The Head *Start Early Learning Outcomes Framework: Ages Birth to Five* ትናንሽ ልጆች በትምህርት ቤት እና በኋለኛው የሕይወት ዘመናቸው ስኬታማ ለመሆን እንዲዘጋጁ ለማገዝ አስተማሪዎች የመጀመርያ ትምህርት መስፈርቶችን በተሳካ ሁኔታ እንዲጠቀሙባቸው ሰባት መሪ መመሪያዎችን ይሰጣል፣ [1]

1. “ እያንዳንዱ ልጅ ልዩ ነው እና ስኬታማ ሊሆን ይችላል። ልጆች የተለያዩ ደረጃዎች እና የእድገት መንገዶች ያላቸው ግለሰቦች ናቸው። እያንዳንዱ ልጅ በቅድመ ወሊድ አከባቢው ፣ ሁኔታ ፣ ፊዚዮሎጂ እና የህይወት ልምዶቹ በልዩ ሁኔታ ተጽእኖ ያድርበታል። ተገቢ ከሆነ ድጋፍ ጋር፣ ሁሉም ልጆች ስኬታማ የሆኑ ተማሪዎች ሊሆኑ እና በ [*መጀመርያ ትምህርት መስፈርቶች* ] *ላይ የተገለጹትን ክህሎቶች፣ ባህርይ እና እውቀት ሊያገኙ ይችላሉ።*
2. መማር የሚከናወነው በግንኙነቶች ማእቀፍ ውስጥ ነው። ተንከባካቢ ወላጆች፣አስተማሪዎች እና ሌሎች አዋቂዎች በወጣት ልጅ ህይወት ላይ አስፈላጊ ናቸው። ከአዋቂዎች ጋር ምላሽ የሚሰጥ እና ደጋፊ ግንኙነቶች ለልጆች መማር አስፈላጊ ነው።
3. ቤተሰቦች የልጆች የመጀማሪያ እና በጣም አስፈላጊ ተንከባካቢዎች፣ አስተማሪዎች እና ተሟጋቾች ናቸው። ቤተሰቦች የልጃቸው የመጀመሪያ የመማር እና ትምህርት ዋና ተጽእኖ ፈጣሪ እንደመሆናቸው መጠን መከበር እና መደገፍ አለባቸው። የነሱ እውቀት፣ ክህሎቶች እና ባህላዊ መነሻዎች ለልጆቹ የትምህርት መዘጋጀት አስተዋጾኦ ያደርጋል።
4. ልጆች በስሜት እና በአካል ደህንነት ሲሰማቸው በይበልጥ ይማራሉ። እንክብካቤ፣ ምላሽ የሚሰጥ እና ወጥነት ያለው እንክብካቤ ልጆች ደህንነት እና ዋጋ እንዳላቸው እንዲሰማቸው ያደርጋል። በእነዚህ ሁኔታዎች፣ ልጆች በመማር ልምዶች ላይ በሙሉ መሳተፍ ይችላሉ።
5. የእድገት ስፍራዎች የተቀናጁ ናቸው እና ተማሪዎች በተመሳሳይ ጊዜ ብዙ ንድፈ ሀሳቦችን እና ክህሎቶችን መማር ይችላሉ። ማንኛውም ነጠላ ክህሎት፣ባህርይ ወይም ችሎታ በርካታ የእድገት ስፍራዎችን ሊያካትት ይችላል።
6. ማስተማር ልጆች እንዴት ሊማሩ እና ሊያድጉ እንደሚችሉ ላይ የተቃደ እና ያተኮረ መሆን አለበት። ልጆች ንቁ፣ ተሳታፊ እና ጉጉ ተማሪዎች ናቸው። ጥሩ የማስተማር ልምዶች ለዳሰሳ እና ትርጉም ያለው ጨዋታ ከእድገት ጋር ተገቢነት ያላቸው መመርያ እና እድሎችን በማቅረብ እነዚህን ጥንካሬዎች ያሳድጋሉ።
7. እያንዳንዱ ልጅ በቤተሰባቸው ባህል ፣ ታሪክ ፣ ቋንቋ እና እምነቶች ላይ የተመሠረተ የተለያየ ጥንካሬዎች አሏቸው። ምላሽ ሰጭ እና አክብሮት ያላቸው የትምህርት አካባቢዎች ከተለያዩ ባህላዊ እና ስነቋንቋዊ ታሪኮች የመጡ ልጆችን ይቀበላሉ። ውጤታማ የማስተማር ልምዶች እና የመማር ልምዶች በእያንዳንዱ ልጅ ልዩ ታሪኮች እና የቀድሞ ልምዶች ላይ ይመሰረታሉ።”

## የመጀመሪያ ትምህርት መስፈርቶች ዓላማ እና ጥቅሞች

የመጀመሪያ ትምህርት መስፈርቶች ዋና ዓላማ በኮሎምቢያ ግዛት ውስጥ ያሉ ልጆች በትምህርት ቤት ውስጥ እና ለህይወት ዘመን ትምህርት ስኬታማ እንዲሆኑ የሚያዘጋጃቸውን የበለጸገ እና ጠንካራ የመጀምርያ የትምህርት ልምዶች እንዲኖራቸው ማረጋገጥ ነው። የመጀመርያ ትምህርት መስፈርቶች የጨቅላ ህጻናት፣ ታዳጊዎች፣ ሁለት አመት ልጆችን እና ቅድመትምህርትቤቶችን፣ እንዲሁም ቅድመመዋእለ ህጻናትን እና መዋእለ ህጻናትን የሚለቁ ልጆች ለመውጫ የሚጠበቁ ሁኔታዎችን መለኪያዎችን ያካትታል። የመዋእለ ህጻናት ለመውጫ የሚ Common Core State Standards for English Language Arts and Mathematics እና Next Generation Science Standards (NGSS) ነጸብራቅ ነው፣ እና ባሁን ጊዜ ስራ ላይ ያሉ ማንኛውም መስፈርቶችን አይቀይሩም።

ይህን ግብ ለማሳካት፣ *የመጀመሪያ ትምህርት መስፈርቶች* **ለሚከተሉት አላማዎች ጥቅም ላይ መዋል አለባቸው** ፣

- የሥርዓተ ትምህርትን ምርጫ እና አፈፃፀም ለመምራት የሚያስችል ግብአት፣
- የወጣት ልጆችን እንክብካቤ እና ትምህርት በተመለከተ በቤተሰቦች፣ በአስተማሪዎች፣ በማኅበረሰብ አባላት እና ፖሊሲ አውጪዎች ላይ የውይይት ትኩረት፣
- ከተለያዩ ሁኔታዎች የመጡ የተለያዩ ችሎታዎች ላላቸው ልጆች ተገቢነት ያለው መመዘኛዎችን የመምረጫ መመሪያ፣
- መስፈርቶቹን በማሟላት ረገድ ልጆች እድገት እንዲያሳዩ የሚያስችላቸው ልምዶችን እና መማሪያዎችን የማቀጃ መምሪያ፣ እና
- ለትምህርት ባለሞያዎች የሞያ እድገት እድሎችን ማእቀፍ ማቀድ።

*የመጀመርያ ትምህርት መስፈርቶች* ለሚከተሉት ሁኔታዎች ጥቅም ላይ መዋል **የለባቸውም** ፣

- ልጆች ወደ መዋእለ ሕፃናት ደረጃ እንዳይገቡ መከልከል፣
- በአካል ጉዳት ወይም በቤት ውስጥ በሚነገረው ቋንቋ ላይ በመመርኮዝ በማንኛውም የቅድመ እንክብካቤ እና የትምህርት መርሃ ግብር እና / ወይም እንቅስቃሴዎች ውስጥ ልጆችን አያካትቱ ::
- የልጆችን እድገትና ትምህርትን መመርመር ወይም መገምገም ።

## ባለሁለት ቋንቋ ተማሪዎች በመጀመሪያ እንክብካቤ እና ትምህርት ፕሮግራሞች

*የመጀመሪያ ትምህርት መስፈርቶች* **ባለሁለት ቋንቋ ተማሪዎችን (DLLs)** ከልደት እስከ መዋእለህጻናት ደረጃ መግቢያ ያሉ እና ሁለት (ወይም ከዚያ በላይ) ቋንቋዎችን በተመሳሳይ ጊዜ እየተማሩ ያሉ ወይም የመጀመሪያ ቋንቋቸውን እያሳደጉ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ልጆች በማለት ትርጉም ይሰጣቸዋል።[2]

“ባለሁለት ቋንቋ ተማሪ” የሚለው ቃል አዘውትረው ጥቅም ላይ ከሚውሉ ሌሎች ቃላቶች ጋር እንደ ሁለት ቋንቋ ተናጋሪ፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪ (English language learner, ELL)፣ ውስን የእንግሊዝኛ ችሎታ (limited English proficient, LEP)፣ እንግሊዘኛ ተማሪ (English learner, EL) እና ከእንግሊዝኛ ውጭ ሌላ ቋንቋ የሚናገሩ ልጆች (language other than English, LOTE) ሊያጠቃልል ይችላል።[3]

DLLs የሚመጡት ከእንግሊዘኛ ውጪ ሌላ ቋንቋ ከሚነገርበት ቤት ውስጥ ነው።[4] ለተወሰኑ ከእንግሊዘኛ ውጪ እና እንግሊዘኛ ሁለቱም ቤት ውስጥ ሊነገር ይችላል።[5]

DLLs ተብለው የሚቆጠሩ ተማሪዎች በማናቸውም አይነት የመጀመሪያ እንክብካቤ እና የትምህርት ፕሮግራም ሊመዘገቡ ይችላሉ። ይህ የሚያካትተው፣

- እንግሊዘኛ ዋና የክፍል ቋንቋ የሆነበት የህዝብ ቅድመ ትምህርት ቤት፣
- ሁሉም ተማሪዎች ሁለት ቋንቋዎች ወይም ከዚያ በላይ በክፍል ውስጥ የሚማሩበት ባለሁለት ቋንቋ ፕሮግራሞች፣
- የልጅ እድገት ቤቶች (እንግሊዘኛ ወይም ሌላ ቋንቋ የሚናገሩ ተንከባካቢዎች ያሏቸው)፣ እና
- የልጅ እድገት ማእከላት (እንግሊዘኛ ወይም ሌላ ቋንቋ የሚናገሩ ተንከባካቢዎች ያሏቸው)።

ለነዚህ መስፈርቶች አላማ፣ DLLs በሁሉም የፕሮግራም አይነቶች ሁለት ቋንቋ የሚማሩ ልጆችን ሪፈር የሚያደርግ መሆኑን ማስተዋል አስፈላጊ ነው። አብዛኛው DLLs ሆነው የሚቆጠሩ ልጆች በግዛቱ ባለሁለት ቋንቋ ፕሮግራሞች፣ ሁሉም ተማሪዎች የክፍል ደረጃ ይዘት ያላቸውን በሁለት ቋንቋዎች በሚያጠኑበት ላይ አልተመዘገቡም። በዚህ ፕሮግራሞች ላይ የተመዘገቡ ተማሪዎች፣ የተወሰኑት በቅድመ ትምህርት ቤት የሚጀምሩት፣ አብዛኛውን ጊዜ Dual Language (ባለሁለት ቋንቋ) ተማሪዎች ተብለው ይጠራሉ።

የእንግሊዘኛ ተማሪዎች እና ውስን የእንግሊዘኛ ብቃት የሚሉት ቃላቶች ሪፈር የሚያደርጉት በፌደራል እያንዳንዱ ተማሪ ስኬታማ ይሆናል ህግ ያለውን ትርጉም እድሜያቸው ከ3 እስከ 21 የሆኑ እድሜ ያላቸው ልጆችን ነው።[6] እነዚህ ቃላቶች በነዚህ መስፈርቶች ላይ ለተገለጹት DLLs ለሆኑ ልጆች የልጆቹ የእድገት ደረጃ እና የእንግሊዘኛ ቋንቋ ደረጃን መሰረት በማድረግ ተፈጻሚነት ሊኖራቸውም ላይኖራቸውም ይችላል።

## የቤተሰብ ተሳትፎ

ቤተሰቦች በመጀመሪያ ልጅነት ትምህርት እና የትምህርት ቤት ዝግጁነት ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ። ልጆች የመጀመርያ የትምህርት ስፍራ ከመግባታቸው በፊት ቤት ውስጥ መማር ይጀምራሉ። የክልል የትምህርት ዋና ተቆጣጣሪ የዲሲ ቢሮ (OSSE) እና የፌደራል የልጆች እና የቤተሰቦች አስተዳደር፣ Office of Head Start (OHS) (የሄድ ስታርት ቢሮ) አወንታዊ የወላጅ ልጅ ግንኙነቶች ለልጆች ትምህርት መሰረት መሆኑን ይቀበላሉ። ከቤተሰቦች ጋር ትርጉም ባለው ግንኙነት መሳተፍ ከፍተኛ ጥራት ላለው የመጀመርያ እንክብካቤ እና ትምህርት ወሳኝ ነው። ውጤታማ የቤተሰብ ተሳትፎ ልምዶች የወጣት ልጆችን ፣ ማህበራዊ፣ ስሜታዊ፣ አእምሯዊ፣ የቋንቋ እና የማንበብ እና የመጻፍ እና የአካል እድገታቸውን ጨምሮ ጤና እና እድገታቸውን ያግዛል። ልጆች ከቤተሰቦቻቸው ጋር ያላቸው ልምዶች ለትምህርት ቤት ዝግጁነት በሚገባ አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል።

- ባለሁለት ቋንቋ ተማሪዎች፣ እንደ ሁሉም ልጆች፣ የእያንዳንዱን ቋንቋቸውን እድገት የሚደግፍ ሞቅ ባለ እና ክብር ባለው የትምህርትቤት- ቤተሰብ ግንኙነት ይጠቀማሉ። አስተማሪዎች የባለሁለት ቋንቋነትን አስመልክቶ የግንዛቤ፣ የስነቋንቋ እና የማህበራዊ ጥቅሞችን አስመልክቶ ጠቃሚ መረጃ እና መመሪያ ሲያቀርቡ እና ቤተሰቦች የቤት ቋንቋን መጠበቅ አስመልክቶ ያላቸውን ማንኛውንም ጥያቄዎችን ሊመልሱላቸው ይችላሉ። አስተማሪዎች እና የፕሮግራም ሰራተኛ ከቤተሰቦች ጋር በሚመርጡት ቋንቋ(ዎች) በመነጋገር፣ እና የሚያስፈልግ/ሲያስፈልግ የሰለጠኑ አስተርጓሚዎችን በመጠቀም ለሁሉም ቋንቋዎች ክብርን ማሳየት አለባቸው። በተጨማሪ፣ ከቤተሰቦች ጋር የሚጋሩ ሰነዶችን ወደ አገር ቤት ቋንቋቸው እንዲተረጎሙ District of Columbia Municipal Regulations (DCMR) Language Access Act (በኮሎምቢያ ከተማ ግዛት ደንቦች የቋንቋ ተደራሽነት ህግ)፣ ምእራፍ 12 ክፍል 2(2) እና 2(3) ላይ ይጠየቃል። (D.C. ይፋዊ ኮድ §§2-1931(2) እና 1931(3))።

## የስርአተ ትምህርት ሚና

የ *የመጀመሪያ የመማር መስፈርቶች* ባሁን ወቅት ጥቅም ላይ ያሉትን የስርአተትምህርት ሞዴሎችን ለማገዝ የታቀዱ ናቸው እና አግባብነት ያላቸውን ስነትምህርት እና ውጤታማ አተገባበር መመረጥን ለማሳወቅ በፕሮግራሞች ጥቅም ላይ ሊውሉ ይገባል። ለልጆች የሚፈለጉ ውጤቶችን ለማስገኘት ፣ ሥርዓተ-ትምህርት ፣ የመማሪያ ክፍሎች ልምዶች እና የማስተማሪያ ዘዴዎች በጥንቃቄ የታቀዱ ፣ ባህላዊ እና ስነቋንቋዊ ምላሽ የሚሰጡ እና ለእድገት አግባብነት ያላቸው ፣ ባህላዊ እና ቋንቋዊ ምላሽ ሰጪ እና አጠቃላይ መሆን አለባቸው። The National Association for the Education of Young Children (NAEYC)(የወጣት ልጆች ትምህርት ብሄራዊ ማህበር) እና የ National Association of Early Childhood Specialists in State Departments of Education (NAECS-SDE) (በክልል የትምህርት ዲፓርትመንቶች የመጀመሪያ ልጅነት ስፔሺያሊስቶች ብሔራዊ ማህበር) ውጤታማ የስነትምህርት አመላካቾችን እንዲሚከተለው ተርጉመዋል፣ [7]

- ልጆች ንቁ እና ተሳታፊ ናቸው።
- ግቦች ግልጽ እና በሁሉም የሚጋሩ ናቸው።
- ስርአተ ትምህርቱ ማስረጃን መሰረት ያደረገ ነው።
- ዋጋ ያለው ይዘት የሚገኘው በምርመራ እና ትኩረት ባለው፣ በታቀደ ማስተማር ነው።
- ስርአተትምህርቱ አስቀድሞ በነበሩ ትምህርት እና ልምዶች የተገነባ ነው።
- ስርአተ ትምህርቱ አጠቃላይ ነው።
- የባለሞያ መለኪያዎች የስርአተትምህርቱን ይዘት ያጸናሉ።
- ስርአተ ትምህርቱ ልጆችን ሊጠቅም ይችላል።

## የምዘና ሚና

የግምገማ ዘዴዎች “ከእድገት ጋር አግባብነት ያላቸው ፣ ባህላዊ እና ስነቋንቋዊ ምላሽ የሚሰጡ፣ ከልጆች የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎች ጋር የተቆራኙ፣ በባለሙያ እድገት የተደገፉ ፣ ቤተሰቦችን የሚያካትቱ እና ከተወሰኑ፣ ጠቃሚ ዓላማዎች ጋር የተገናኙ መሆን አለባቸው።” እነዚያ አላማዎች የሚያካትቱች “(1) ስለ ማስተማር እና መማር ውሳኔዎችን መስጠት፣ (2)ለእያንዳንዱ ልጆች ትኩርት ያለው ጣልቃገብነትን የሚያስፈልጉ ዋና ስጋቶችን መለየት እና (3) ፕሮግራሞች የትምህርት እና የእድገት ጣልቃገብነታቸውን እንዲያሻሽሉ መርዳት።”[8]

*የመጀመሪያ የመማር መስፍርቶች* እንደመመዘኛ እንዲያገለግሉ የታቀዱ አይደሉም። ይልቁንም፣ ፕሮግራሞች ከራሳቸው ስርአተ ትምህርት ጋር የሚጣጣም እና እነዚህን መስፈርቶች ለማሟላት የልጆችን የእድገት ሂደት በተመለከተ ዳታ የሚሰጥ የምዘና ሲስተምን መጠቀም አለባቸው። ምዘና ስለልጆች ትምህርታቸውን የሚደግፍ ቀጣይነት ያለው የመርጃ ማሰባሰብ ሂደት ነው። የምዘና ዋነኛ አላማዎች የሚከተሉት ናቸው፣

- እያንዳንዱን ልጅ ማወቅ— እሱ/እሷ ስለሚያውቁት እና ከትምህርት ግቦች አንጻር መስራት ስለሚችሉት ነገር፣
- ለእያንዳንዱ ልጆች እና ለልጆች በቡድን ተግባሮችን እና ትምህርቶችን ማቀድ፣
- እድገትን መከታተል እና እያንዳንዱ ልጅ በሁሉም ስፍራዎች እያደገ መሆኑን ማረጋገጥ፣ እና
- ሪፖርቶችን ማዘጋጀት— ለቤተሰቦች፣ ለገንዘብ ሊጋሾች እና ለሚፈልጉ ሌሎች ወገኖች።

## ለ ባለሁለት ቋንቋ ተማ ሪዎች የምዘና ሁኔታዎች

የመማር ግቦችን አስመልክቶ ቀጣይነት ያለው እውነተኛ የልጆች እድገት ምዘና ለሁሉም DLLs ለሆኑ ልጆች አስፈላጊ ነው። DLLs ለእነዚህ መመዘኛዎች በእነሱ በእንግሊዝኛ፣ በቤት ቋንቋ ወይም ባልተመጣጠነ (በችሎታው፣ በልጁ ቋንቋ ዳራ እና መቼት ላይ በመመርኮዝ) ከእነዚህ መመዘኛዎች ጋር የሚዛመዱ ዕውቀታቸውን እና ችሎታቸውን ሊያሳዩ ይችላሉ። ግምገማው የልጁ የእንግሊዝኛ ቋንቋ እውቀት እና ችሎታ ካልሆነ በስተቀር ግምገማዎች በማንኛውም ቋንቋ ወይም ለልጁ ምቹ እና ተገቢ በሆነ መልኩ ምላሽ ለመስጠት DLLs ን መደገፍ አለባቸው። ይህ በተለያዩ ቅንብሮች ውስጥ በተለየ ሁኔታ ይተገበራል። የቤተሰብ አባሎች ያዩትን እና ያጋጠማቸውን ፣ ግባቸውን እና ከልጃቸው እድገት የሚጠብቁትን እና ማንኛውንም ሊኖራቸው የሚችለውን ስጋቶች በማጋራት ለዚህ ሂደት አስተዋጽኦ ሊያደርጉ ይችላሉ። አስተማሪዎች የቤተሰቦች ተሳትፎ ያለው ለእድገት ተገቢ የሆነ የትምህርት ተግባሮችን ለማቀድ እና ለማካሄድ ቀጣይነት ካለው ምዘና የተማሩትን ነገር መጠቀም አለባቸው።

ብዙ መመዘኛዎች (ደረጃቸውን የጠበቁ መመዘኛዎችን ጨምሮ) እንግሊዝኛን ከሚናገሩ ልጆች ጋር ብቻ ለመጠቀም የተነደፉ ናቸው። እነሱ የ DLLs እውቀት እና ክህሎቶችን ስፋትን እና ጥልቀትን አይመዝኑም። ቀጣይነት ያለው እውነተኛ የልጅ እድገት ምዘና (በሁሉም የልጁ ቋንቋዎች) ተገቢ ነው እና ልጁ የሚያውቀውን እና ሊያደርገው ስለሚችለው ነገር የበለጠ ተጨባጭ ምዘናን ይሰጣል። ይህ ቀጣይነት ያለው ምዘና የልጁን እድገት መመልከት እና መመዝገብን እንዲሁም የልጁን እድገት በጊዜ ሂደት ማነጻጸርን ያካትታል።

## የሁሉም ልጆች መካተት ድጋፍ

ከዚህ በላይ እንደተገለፀው *የመጀመርያ ትምህርት መስፈርቶች* ሥርዓተ ትምህርትን የመምረጥ እና የመተግበር እንዲሁም ሁሉም ልጆች እነዚህን መስፈርቶች ለማሟላት እድገት የሚያሳዩበትን ልምዶች እና ትምህርቶችን የሚያቅዱበት መመሪያ ይሰጣል። ይህም ሰፊ የግንዛቤ፣ ቋንቋ/ንግግር፣ አካላዊ፣ ማህበራዊ-ስሜታዊ እና የስሜት ልዩነቶችን የሚያሳዩ የልዩ ትምህርት ፍላጎቶች ያሉባቸውን ልጆች ያካትታል። ሁለንተናዊ የትምርህት ዲዛይን ዘዴ የአካል ጉዳተኛ ሕፃናትን ወይም ሌሎች ልዩ ፍላጎቶችን ጨምሮ ሁሉም ልጆች ስርአተትምህርቱን እንዲያገኙ የሚረዳ ድጋፍ ይሰጣል። ሁለንተናዊ የትምህርት ዲዛይን ዘዴ ለሁሉም ሕፃናት ድጋፍ የሚሰጥ፣ ሁሉንም የልጆችን የአካል ጉድለቶችን ወይም ልዩ ፍላጎቶችን ለማስተናገድ የሚችል ለፕሮግራሙ ወይም የትምህርት ቤት አካባቢ ተጨማሪ ልምዶችን፣ ቁሳቁሶችን እና የማስተማር ስልቶችን የሚሰጥ አስፈላጊ መሰረት ነው። እያንዳንዱ ልጅ የእሱን ወይም የሷን የመማር ስታይሎችን፣ ክህሎቶችን እና ምርጫዎችን በልዩ መንገዶች ስለሚያሳዩ፣ እንደዚህ አይነት ማስተካከያዎች በየግል በያንዳንዱ ልጅ የግል የቤተሰብ አገልግሎት እቅድ ወይም የግል የትምህርት ፕሮግራም የሚወሰኑ ናቸው። ማስተካከያዎች የእድገት መዘግየቶች እና ጉድለቶች ያለባቸውን ልጆች ጥንካሬያቸውን እንዲያስድጉ እና በ *መጀመርያ ትምህርት መስፈርቶች* ላይ ወዳሉ ውጤቶች እድገትን ሲያሳዩ የመማር ልዩነቶቻቸውን እንዲያሟሉ መንገዶችን ያቀርባሉ። አስተማሪዎች የእድገት መዘግየት እና የአካል ጉድለት ያለባቸው ልጆች ስኬታማ እንዲሆኑ የሚያችል በልጆች የግል ጥንካሬዎች እና ፍላጎቶች ላይ በማተኮር፣ የትምህርት እድሎችን ከስርአተትምህርት እና ከመስፈርቶቹ ጋር በማገናኘት፣በግል እቅዶች ላይ እንደተመለከተው ተገቢ ድጋፎች እና ማስተካከያዎችን በመስጠት እና የልጆችን እድገት ቀጣይነት ባለው ሁኔታ የሚመዝን ፕሮግራሞችን ማቀድ እና ማዋቀር ይችላሉ።

## ወደ መዋእለ ህጻናት መሸጋገር

ወደ መዋለ-ሕጻናት ደረጃ መሸጋገር ለትናንሽ ልጆች እና ለቤተሰቦቻቸው በጣም ወሳኝ ጊዜ ነው እና ደጋፊ እና እንከን የለሽ ሽግግር እንዲፈጠር ለማድረግ አስተማሪዎች ማገዛቸው አስፈላጊ ነው። ይህ በጣም ውጤታማ በሆነ ሁኔታ የሚከናወነው ከመዋዕለ ሕፃናት መምህራን እና ቤተሰቦች ስለ ሥርዓተ ትምህርት እና ስለ እያንዳንዱ የልጆች እድገት እና የትምህርት ጥንካሬዎች እና ፍላጎቶች ላይ መነጋገርን የሚያስችል በትብብር ሁኔታ ነው። የቅድመ ትምህርት ቤት እና የመዋእለህጻናት ልምዶች ሲጣጣሙ፣ ልጆች አስቀድመው የተማሩትን በቀላሉ ማሳደግ እና በቀጣይ ለሚማሩት መዘጋጀት ይችላሉ። ይህ ልጆችን በግንዛቤ፣ በአካዳሚክ እና በማህበራዊ ይጠቅማቸዋል። የተስተካከለ ሽግግርን ለምገንባት ውጤታማ ስልቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፣

- በልጆች፣ ወላጆች እና ትምህርት ቤቶች መካከል አወንታዊ የሆነ ግንኙነትን መገንባት፣
- በቅድመ ትምህርት ቤት እና በመዋእለ ህጻናት ደረጃዎች ያሉ መመዘኛዎችን፣ መስፈርቶችን እና ስርአተ ትምህርትን ማጣጣም፣
- የተጣመረ የባለሞያ እድገትን በቅድመ ትምህርት ቤት እና በመዋእለ ህጻናት አስተማሪዎች መካከል መመስረት፣ እና
- መረጃን ማጋራት፣ የልጆችን እና የቤተሰቦችን ፍላጎቶች መግለጽ እና የትምህርት ቤት ዝግጁነትን ማዘጋጀት።

## ባህላዊ እና ስነቋንቋዊ ምላሽ ሰጭ

ባህላዊ እና ስነቋንቋዊ ምላሽ ሰጭ ልምዶች የቤት ቋንቋቸውን ለማስተማር እና ለመማር ማካተትን ጨምሮ፣ የልጆችን ባህላዊ ታሪክን የማገናኘት አስፈላጊነት ይገነዛብሉ። የባህላዊ እውቀታቸውን፣ የኋላ ታሪካቸውን እና የመማሪያ ዘይቤዎችን እውቅና በመስጠት፣ በማክበር እና በማዋሃድ አስተማሪዎች ለሁሉም ህጻናት ትምህርት የበለጠ ጠቃሚ እና ትርጉም ያለው ያደርጋሉ።

ልጆች ከተወለዱ ጊዜ ጀምሮ (ከዚያ በፊትም ጀምሮ) የባህላቸው እና ቋንቋቸው እውቀት እያዳበሩ ነው። ቤተሰቦቻቸው የሚጠቀሙባቸውን ቋንቋ (ዎች) ድምጾች፣ እንዲሁም የቤተሰባቸውን ባህላዊ እሴቶች፣ ወጎች እና ልምዶች ይማራሉ። ከቤተሰቦች እና ከልጆች ጋር በሚኖሯቸው ግንኙነቶች አስተማሪዎች ስለልጆቹ ቋንቋ እና ባህላዊ ታሪክ ሊማሩ ይችላሉ። እነሱ ለልጆች የኋላ ታሪክ ባህላዊ እና ስነቋንቋዊ ምላሽ የሚሰጡ ደጋፊ ልምዶችን መጠቀም ይችላሉ። ከዚያ እነዚህ ልምዶች የልጆቻቸውን በቤተሰባቸው እና በባህላቸው ውስጥ በተዳበረው ነባር ዕውቀት እና ችሎታዎች ላይ መገንባት ይችላሉ። አስተማሪዎች ልጆችን ወደ አዳዲስ ችሎታዎች እና ሀሳቦች ለማስተዋወቅ የተለመዱ ቁሳቁሶችን፣ ቋንቋዎችን ወይም ልምዶችን ሊጠቀሙ ይችላሉ። በተጨማሪ ባህላዊ እና ስነቋንቋዊ ምላሽ የሚሰጡ ልምዶች የወጣት ልጆችን ማንነት እና በራስ የመተማመን ስሜትን ይደግፋሉ። አስተማሪዎች በቤት፣ በትምህርት ቤት እና በማህበረሰቡ መካከል ያሉትን ግንኙነቶች በማጠናከር ሁሉም ልጆች እንዲያድጉ እና እንዲማሩ የመርዳት እድል አላቸው። ከወጣት ልጆች እና ከቤተሰቦቻቸው ጋር እውነተኛ እና ትርጉም ያለው ግንኙነቶችን መገንባት ባህላዊ እና ስነቋንቋዊ ምላሽ የሚሰጡ ልምዶችን ለማቅረብ መሰረታዊ ነው።

## ሙያዊ እድገት እና ስልጠና

አዲስ እንዲሁም ልምድ ያላቸው የመጀመሪያ እንክብካቤ እና የትምህርት አስተዳዳሪዎች፣ አሰልጣኞች፣ አማካሪዎች፣ እና አስተማሪዎች ሥራቸውን እና ልምዶቻቸውን በመጀመሪያ ትምህርት መስፈርቶች የተገነቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ግላዊ ፍላጎታቸውን የሚያሟላ ቀጣይነት ያለው ድጋፍ፣ ስልጠና እና የሞያ እድገት ማግኘት አለባቸው። በመጀመሪያ የትምህርት መስፈርቶች ውስጥ የተገለጹትን አወንታዊ የትምህርት ውጤቶችን ለማሳካት ሁሉም ባለድርሻ አካላት (ለምሳሌ፣ መምህራን፣ ወላጆች፣ አሠልጣኞች፣ ወዘተ) ለተሟላ አፈፃፀማቸው ቁርጠኛ መሆን እና ይህንን አፈጻጸም ለመደገፍ ቀጣይነት ያለው ድጋፍ እና ተገቢ ሥልጠና ማግኘት አለባቸው።

## ለአስተማሪዎች መሪ መመሪያዎች

ከዚህ በታች አስተማሪዎች ትንንሽ ልጆችን በእድገታቸው እና በትምህርታቸው እንዲደግፉ የሚመከሩ ልምዶች ናቸው። እነዚህ መርሆዎች ፤*በመጀመሪያ ትምህርት መስፈርቶች* ውስጥ የመጀመሪያ እድገት እና ትምህርት የእድገት ሂደት ላይ ካለው እውቀት ጋር ባንድ ላይ ሲቀናጁ፣ በግንኙነት ላይ የተመሰረቱ ግንኙነቶችን ለመተግበር እና ውጤታማ የመማር ስልቶችን ለመገንባት የሚያስችሉ የአስተማሪውን ክህሎቶቹን ያጠነክራል።

1. **የእያንዳንዱን ልጅ ፍላጎቶች ፣ ጥንካሬዎች የሚደግፉ ደህንነቱ የተጠበቀ አካባቢን ማቅረብ**፣ በራስ ተነሳሽነት አሰሳ እና ልምዶችን በማዳበር ትርጉም ያለው ትምህርትን ያበረታታል።
2. **ሁለንተናዊ ዲዛይን ለትምህርት ፣** ሁሉም ተማሪዎች በጋራ ቅንብር ውስጥ ያላቸውን ፍላጎቶች ለማሟላት የሚያስችል ሥርዓተ ትምህርትን ለመተግበር እና የመጀመሪያ ትምህርት አካባቢዎችን ዲዛይን ለማድረግ የሚያስችል ጥንካሬን መሰረት ያደረገ ዘዴ ነው። ሁለንተናዊ ዲዛይን ለትምህርት በትምህርት ላይ በርካታ የመወከያ፣ የመግለጫ እና የመሳተፊያ መንገዶችን ያቀርባል።
3. **ከቤተሰብዎ ጋር ግንኙነቶች መገንባት** በፕሮግራምዎ ውስጥ ቤተሰቦች በልጆቻቸው ትምህርት ውስጥ የአሁን እና የወደፊት ተሳትፎ ላይ መሰረት ይጥላል።
4. **በግንኙነት ላይ የተመሠረተ እንክብካቤን መተግበር** የመጀመሪያ ደረጃ እንክብካቤን አስፈላጊ ፍሬ ነገሮችን፣ የእንክብካቤ ቀጣይነትን፣ ግላዊ እንክብካቤን፣ ባህልን ግምት ውስጥ የሚከት እንክብካቤ፣ ትናንሽ ቡድኖችን እና ማካተት ወጣት ልጆች የሚማሩበትን መንገድ ይደግፋል።
5. **ባህላዊ እና ስነቋንቋዊ ምላሽ በሚሰጥ መንገዶች መግባባት** በልጆች ውስጥ የማንነት እድገትን የሚደግፍ እና ሁሉም ድምጾች እና ሀሳቦች የሚሰሙበት ጠንካራ የመማሪያ ማህበረሰቦችን ይገነባል።
6. **ከቤተሰቦች፣ ከመዋእለ-ህፃናት አስተማሪዎች እና ከአከባቢው ትምህርት ቤት የአስተዳደር ባለሥልጣኖች ጋር በመተባበር መሥራት** ወደ መዋለ ህፃናት ለሚገቡ ልጆች እንከን የለሽ ሽግግርን ይፈጥራል።
7. **የእያንዳንዱን ልጅ ጥንካሬዎች መገንዘብ** በእድገት መነጽር መገንዘብ የእያንዳንዱን ልጅ ምልከታዎች እና በከፍተኛ የእያንዳንዱን ልጅ ምልከታ እና ለሁሉም ልጆች ጥሩ ትምህርት የማቀድ ችሎታን ያጠናክራል።
8. **ከሌሎች የመጀመሪያ ትምህርት ባለሙያዎች ጋር ሀሳብ መስጠትን የሚያሳትፍ ትብብር መኖር** የሞያ እድገትን የሚደግፍ ሲሆን ለልጆች እና ቤተሰቦች የጋራ እውቀትን እና ቀጣይነትን ይገነባል።
9. **ለታዳጊ ሕፃናት ውጤታማ ሥርዓተ-ትምህርት ማቀድ** በእያንዳንዱ ፕሮግራም ውስጥ ካሉ ቤተሰቦች እሴቶች እና ልምዶች ጋር ከተዛመዱ ከልጆች ችሎታዎች ምልከታ እና ምዝገባ ጋር የተገመደ ነው - ይህም የቤተሰብ ልምዶችን ከፕሮግራሙ ሥርዓተትምህርት እና ትምህርት ጋር እንዲካተት የሚያስችል ማእቀፍን ይሰጣል።
10. **ተገማች የሆነ ነገር ግን አስፈላጊ ሲሆን ሊለዋወጥ የሚችል ምላሽ የሚሰጡ፣ ወጥነት ያላቸውን መደበኛ አሰራሮችን እና ሽግግሮችን** መኖሩ የሁልንም ልጆች ከፍተኛ እድገት እና ትምህርት ይደግፋል እና በተለይም በአሰቃቂ ሁኔታ ወይም መርዘኛ የሆነ ጭንቀት ላጋጠማቸው ልጆች ጠቃሚ ሊሆነን ይችላሉ።
11. የተለያዩ ቁሳቁሶች ፣ የቤተሰቦችን የአገር ቤት ባህሎች እና የልጆችን ወቅታዊ ፍላጎቶች የሚያንፀባርቁ እና የመማር እድገትን የሚደግፉ አዲስ ወይም ተያያዥ ሀሳቦችን የሚሰጡ በ **ስሜት-የበለፀገ አካባቢን ዲዛይን ማድረግ** ።
12. **አስተማሪ ሰነድ የሚይዝበትን ፣ሀሳብ የሚያሰላስልበትን እና የሚያቅድበትን ቦታ መመደብ** ፣ የአነስተኛ ቡድን ትምህርት፣ መታየት ያለባቸው ስፍራዎች፣ የሚገኙ ቁሳቁሶች፣ እናየ ሁሉንም የልጆች የእንቅስቃሴ ችሎታዎች እና ድጋፍ መሣሪያዎች መኖር በአንድ ታዳጊ ልጅ የትምህርት አካባቢ አስፈላጊ ነው።

## እንደ መጀመሪያ እንክብካቤ እና ትምህርት አካል የጨዋታ አስፈላጊነት

አብዛኛው የታዳጊ ልጆች አስፈላጊ የግንዛቤ፣ ማህበራዊ-ስሜታዊ፣ የቋንቋ እና አካላዊ እድገት የሚፈጠረው በጨዋታ ማእቀፍ ውስጥ ነው። የማስመሰል ጨዋታ፣ ከባድ እና ልፍያ የሚጠይቅ ጨዋታ፣ ልጆች ህጎቹን የሚያወጡበት ጨዋታዎች እና ህጎች ያላቸው ጨዋታዎች እና መገንባት እና እቃዎችን መጠቀም የሚጠይቁ ጨዋታ አሉ። በተጨማሪም ከአዋቂዎች ጋር ጨዋታ እና ከሌሎች ልጆች ጋር ጨዋታ አለ። እነዚህ የተለያዩ ዓይነቶች ጨዋታዎች የልጁን ሁለንተናዊ ጤናማ እድገትን ያበረታታሉ።

ልጆች ነፃ የጨዋታ ጊዜ ቢያስፈልጋቸውም፣ እውቀት ያላቸው አስተማሪዎች የማስታወስ እድገትን፣ ስሜትን መቆጣጠር እና የግንዛቤ ቅልጥፍናን እንዲሁም የቋንቋ እና የአካል እድገትን በሚደግፍ ገንቢ እና ዓላማ ያለው ጨዋታ እንዲሳተፉ ሊያደርጓቸው ይችላሉ ። ልጆች ቁሳቁሶችን በፈለጉት መንገዶች የመጠቀም እድሎች ሲኖራቸው፣ የሚስቡ ርዕሶችን ለመመርመር፣ በእጅ-ዳሰሳ ላይ ሲሳተፉ እና ሞዴሎችን እና ምስሎችን ሲገነቡ፣ እነሱ አስፈላጊ ክህሎቶችን እና ፅንሰ ሀሳቦችን እየተማሩ ነው።

ውስብስብ ማህበራዊና ድራማዊ ጨዋታ በተለይ ለልጆች አስፈላጊ ክህሎቶችን እንዲያዳብሩ እድል በመስጠት ረገድ በጣም ጠቃሚ ነው። በእንደዚህ አይነቱ ጨዋታ፣ ልጆች ሚናቸውን መፍጠር ፣ ለሌሎች ባህርይ ምላሽ መስጠት፣ ጨዋታው ሲቀጥል ለውጦችን ለማድረግ ፍቃደኛ መሆን እና ከሚናው ጋር የተያያዘውን ቋንቋ ለመማር እና ለመጠቀም መቻል አለባቸው ። አስተማሪዎች እንደዚህ አይነት ውስብስብ ጨዋታን በማዳመጥ፣ እንደ አስፈላጊነቱ ቋንቋን ብመስጠት፣ አዲስ ቋንቋ፣ ሀሳቦች እና ግፊቶችን በማቅረብ ትምህርትን ማራዘም፣ እና ችግር መፍታት እንዲሁም የልጁን ምናብ በማስፋት መደገፍ ይችላሉ።

## የሰነዱ አደረጃጀት

ከዚህ በታች ያለው ሰንጠረዥ *የመጀመሪያ ትምህርት መስፈርቶችን* እንዴት እንደተደራጁ ያሳያል።

| | |
|---|---|
| **መስፈርቶች** | ከልደት እስከ አምስት ዓመት የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ልጆችን እድገት ለመግለጽ እንደ መመሪያ ሆነው ያገለግላል |
| ↓ | |
| **አመላካቾች** | በእያንዳንዱ መስፍረት ውስጥ ፅንሰ ሀሳቦችን ፣ እውቀቶችን እና ክህሎቶችን በማግኘት ረገድ የልጆችን እድገት ማሳየት |
| ↓ | |
| **ምሳሌዎች** | መስፈርቱ በተወሰነ ዕድሜ ወይም የእድገት ደረጃ ምን እንደሚመስል መግለጽ |
| ↓ | |
| **ድጋፍ ሰጭ ልምዶች** | አስተማሪዎች ልጆች የሚፈለጉትን ክህሎቶች እንዲማሩ የሚያግዙበትን መንገዶች ይጠቁማል |

### የመጀመሪያ ትምህርት መስፈርቶች ዘጠኝ የእድገት ስፍራዎችን እና ትምህርትን ያካተተ ነው፣

- ለመማር/ሎጂክ እና ምክንያታዊነት ዘዴዎች፣
- መግባባት እና ቋንቋ፣
- ማንበብ እና መጻፍ፣
- ሂሳብ፣
- ሳይንስ እና ኢንጂነሪንግ፣
- ማህበራዊ ሳይንሶች፣
- ዘ አርትስ፣
- ማህበራዊ እና ስሜታዊ እድገት፣ እና
- አካላዊ እድገት፣ ጤና እና ደህነነት።

### መስፈርቶቹ ለነዚህ የእድሜ/ክፍል ደረጃዎች “መለኪያዎች” አላቸው።

- ጨቅላ ህጻናቶች
- ታዳጊዎች
- ሁለት አመት ልጆች
- ቅድም ትምህርት ቤቶች
- ቅድመ መዋእለ ህጻናት ለመውጫ የሚጠበቁ ነገሮች
- የመዋእለህጻናት ለመውጫ የሚጠበቁ ነገሮች

እያንዳንዱ መለኪያ መስፈርቱ በዚያ እድሜ ወይም የክፍል ደረጃ ምን እንደሚመስል፣ እንዲሁም የሚያስፈልጉትን ክህሎቶች ልጆች እንዲማሩ የሚረዳቸውን አንድ ወይም ከዚያ በላይ ደጋፊ ልምዶችን ያካትታል። አብዛኛው በቅድመ መዋእለ ህጻናት ደረጃ ያሉ መስፈርቶች ተጨማሪ መልኪያዎችን ያካትታሉ (ለምሳሌ 5a፣ 5b ወዘተ በዚያ ደረጃ ያለውን መስፈርት ውስብስብነት ለማየት የሚያስችል)። መለኪያዎቹ፣ ምሳሌዎች እና ደጋፊ ልምድ(ዶች) “እነሱ” እና “የነሱ” የሚሉትን ገለልተኛ ጾታ የሆኑ ተውላጠ ስሞችን ሁሉንም ልጆችን የሚያካትተውን ይጠቀማሉ። ከታች ይህ ሰነድ እንዴት እንደተደራጀ የሚያሳይ ከ*መጀመሪያ ትምህርት መስፈርቶች* የወጣ ጽሁፍ ነው።

| **መግባባት እና ቋንቋ፣** | **ጨቅላ ህጻናቶች** | **ታዳጊዎች** | **ሁለት አመት ልጆች** | **ቅድም ትምህርት ቤት** |
|---|---|---|---|---|
| መስፈርቶች | አመላካቾች | አመላካቾች | አመላካቾች | አመላካቾች |
| 5. የንግግር ቋንቋን መረዳትን ማሳየት | 5a. የሌሎች ንግግር ላይ ፍላጎትን ማሳየት<br>*ለምሳሌ፣*<br>• የሚያወሩ ሰዎችን መመልከት።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• ልጆቹን ቀኑን ሙሉ ማዋራት፣ ምን እያደረጉ እና ምን እያጋጠማቸው መሆኑን በመግለጽ (ለምሳሌ፣ “You’re picking up green peas with your fingers.” [“እናንተ በጣቶቻቹ አረንጓዴ<1} አተሮችን እየለቀማቹ ነው።”] ይበሉ)። | 5a. ለሌሎች ንግግር እና የአካል እንቅስቃሴ ምላሽ መስጠት<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ጫማ የሚለውን ቃል ሲሰሙ ጫማቸውን መንካት<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• እቃዎችን እና ድርጊቶችን ስም መጥራት፣ አዳዲስ ቃላቶችን ማስተዋወቅ (ለምሳሌ፣ “Here’s your dinosaur blanket with the soft ribbon fringe.” [“ለስላሳ የሪባን ጠርዝ ያለው የዳይኖሰር ብርድልብስህ ይህውና።” ማለት] ማለት)። | 5a. ለቀላል አረፍተነገሮች፣ ጥያቄዎች እና ቀላል ጽሁፎች ምላሽ መስጠት ጮክ ብሎ ማንበብ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• የመጽሀፉን ሽፋኖች መግለጥ “Where’s Spot?” [“ ስፖት የት ነው?”] የሚለውን ተገቢ በሆነ ጊዜ መናገር።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• መረዳትን እና ቃላትን ለመጨመር መጽሀፎችን ማንበብ እና ደጋግሞ ማንበብ። በስእሎቹ እና ታሪኩ ላይ አስተያየት መስጠት። | 5a. በጣም ውስብስብ ለሆኑ ጥያቄዎች፣ አረፍተነገሮች ምላሽ መስጠት እና አዲስ ቃላት እና ሀሳቦችን የሚሰጡ ጽሁፎችን ጮክ ብሎ ማንበብ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• በሚያጣብቅ ወረቀት ከሰራቹ በኋላ እጆችን የመታጠብ እና የማድረቅ መመሪያዎችን መከተል።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ደረጃዎች መመሪያዎችን መስጠት። |

| **ቅድመ መዋእለ ህጻናት ለመውጫ የሚጠበቁ ነገሮች** | **መዋእለ ህጻናት የመውጫ ተስፋዎች** |
|---|---|
| አመላካቾች | የታወቁ ዋና የመንግስት መለኪያዎች |
| **መረዳት እና መተባበር**<br>5a. እርዳታ ለመጠየቅ እና ለመስጠት ጥያቄዎችን መጠየቅ እና መመለስ፣ መረጃ ማግኘት እና መስጠት ወይም ያልተረዱትን ነገር ማብራራት<br>*ለምሳሌ፣*<br>• አስተማሪውን ለምሳ ዶሮ የሚበሉ መሆኑን፣ ምን አይነት እና ሶስት ብዛት የሚወስዱ መሆኑን ይጠይቁ።<br><br>5b. በአግባቡ ምላሽ በመስጠት የንግግር ቋንቋን መረዳትን ማሳየት<br>*ለምሳሌ፣*<br>• አስተማሪው በመማሪያ ክፍል ውስጥ ልጆች እየሮጡ በመሆኑ ምክንያት ምልክት ማድረግ እንደሚያስፈልጋቸው ሲገልጹ ምልክት ለመስራት ወረቀት ያግኙ።<br>*ደጋፊ ልምዶች*<br>• የፖሊስ ባለሟሎች ለጉብኝት ሲመጡ ሊጠይቋቸው የሚፈልጓቸውን ጥያቄዎች እንዲያስቡ ልጆችን ያበረታቷቸው።<br>• ልጆች የሚናገሩትን እንዲረዱ፣ መልእክትዎን በተጨባጭ እቃዎች እና እንቅስቃሴዎች በማሳየት መልእክትዎን ያብራሩ (ለምሳሌ “Watch how I always keep this foot in front when I gallop.” [“ስጋልብ ይህን እግር ሁልጊዜ እንዴት እንደማደርግ ተመልከቱ።”]) | **መረዳት እና መተባበር**<br><br>SL.K.2. ቁልፍ ዝርዝሮችን በተመልከተ ጥያቄዎችን በመጠየቅ እና አንድ ነገር ያልተረዱ ከሆነ ማብራርያ በመጠየቅ ጮክ ተብሎ የተነበበ ጽሁፍ በቃል ወይም በሌሎች ሚዲያ የቀረበ መረጃን መረዳትን ማረጋገጥ።<br><br>SL.K.3. እርዳታ፣ መረጃ ለማግኘት ወይም ያልተረዱትን ነገር ለማብራራት ጥያቄዎችን መጠየቅ እና መመለስ። |

The Common Core State Standards for English Language Arts and Mathematics እና Next Generation Science Standards (NGSS) በዲሲ የተወሰዱ የይዘት መስፈርቶች ናቸው እና በመጀመሪያ ትምህርት መስፈርቶች አልተቀየሩም።

## የመማር/ሎጂክ እና ምክንያታዊነት ዘዴዎች

1. በጉጉት መከታተል እና መሳተፍ
2. ጽናትን ማሳየት
3. ተግባሮችን በተለዋዋጭነት ይቀበላል
4. ምልክቶችን መጠቀም እና የማስመሰል ሚናዎችን መውሰድ

## መግባባት እና ቋንቋ

5. የንግግር ቋንቋን መረዳትን ማሳየት
6. እራስን ለመግለጽ ቋንቋ መጠቀም
7. የተለመደው ሰዋሰው እና አገባብ ይጠቀማል
8. የተለመዱ ውይይቶችን እና ሌሎች ማህበራዊ ግንኙነት ችሎታን ይጠቀማል

## ማንበብ እና መጻፍ

9. የተጻፉ ሀሳቦችን መረዳትን ማሳየት
10. የተጻፉ ሰነዶች ጮክ ብለው ሲነበቡ መርዳትን ማሳየት
11. የእንግሊዘኛ እና/ወይም የአገር ቤት ቋንቋዎችን ድምጾች መስማት እና መለየት
12. ፊደሎችን እና ቃላትን መጻፍ
13. የመጻፍ እና የመሳል አላማን መረዳት

## ሂሳብ

14. እቃዎችን ማዛመድ፣ መቦደን እና መከፈል
15. ቁጥሮችን እና የመቁጠር እውቀትን ማሳየት
16. የመጠን፣ ቁመት፣ ክብደት እና ርዝመት እውቀትን ማሳየት
17. ቅርጾችን መለየት እና ምልክት ማድረግ
18. የአቅጣጫ ቃላት መረዳትን ማሳየት

## ሳይንስ እና ኢንጂነሪንግ

19. ህይወት ያላቸው ነገሮችን መመርመር
20. አካላዊ እቃዎችን መመርመር
21. የመሬት እና ህዋ ባህርዮችን መመርመር
22. ኢንጂነሪንግን መመርመር

## ማህበራዊ ጥናቶች

23. ራስን፣ ቤተሰብን እና የተለያዩ ማህበረሰብን መረዳትን ማሳየት
24. በሰዎች እና በሚኖሩበት አካባቢ መካከል ያለውን ግንኙነት መረዳትን ማሳየት
25. ጊዜን ከራስ፣ ቤተሰብ እና ማህበረሰብ ጋር በሚዛመድ መልኩ መረዳትን ማሳየት

## ዘ አርትስ

26. በሙዚቃ እና የእንቅስቃሴ ተግባሮች መሳተፍ
27. በድራማዊ እንቅስቃሴዎች መሳተፍ
28. የእይታ አርቶችን ማሰስ

## ማህበራዊ እና ስሜታዊ እድገት

29. የተለያዩ አይነት ስሜቶችን መግለጽ እና እነሱን መቆጣጠርን መማር
30. የሌሎችን ሰዎች ስሜቶች እና መብቶችን መገንዘብ እና ተገቢውን ምላሽ መስጠት
31. የራስን ባህርይ መቆጣጠር
32. ከአዋቂዎች ጋር አወንታዊ ግንኙነትን ማዳበር
33. ከአቻዎች ጋር መሳተፍ እና መጫወት
34. ከሌሎች ጋር ያለን ግጭት መፍታት

## አካላዊ እድገት፣ ጤና እና ደህንነት

35. የትላልቅ ጡንቻዎችን ጥንካሬ እና ቅንጅትን ማሳየት
36. የትናንሽ ጡንቻዎችን ጥንካሬ እና ቅንጅትን ማሳየት
37. ጤናን እና ደህነትን የሚያበረታቱ ባህርዮችን ማሳየት
38. አወንታዊ የአመጋገብ ባህርዮችን፣ ከፍተኛ የምግብ መቀበል ክህሎቶችን፣ የምግብ አወሳሰድን ራስ መቆጣጠርን፣ የታቀዱ የምግብ ምርጫዎችን እና አወንታዊ የሰውነት ምስልን በመጠበቅ ብቃት ያለው የአመጋገብ ባህርዮችን ማሳየት

የሚከተለው *በመጀመሪያ ትምህርት መስፈርቶች* ውስጥ የተካተቱ የእያንዳንዱ ስፍራ ወይም ጎራ አጭር ማጠቃለያ ነው።

**የመማር/ሎጂክ እና ምክንያታዊነት ዘዴዎች** ማለት ልጆች መረጃን እንዴት እንደሚቀበሉ እና እንደሚያካሂዱ እንዴት እንደሚማሩ የሚመለከት ነው። በዚህ የእድገት ስፍራ ያሉት ክህሎቶች ከማሰብ ጋር የተያያዙ፣ ከማስታወስ፣ ከችግር ፈቺነት እና ውሳኔ ሰጭነት ናቸው። ልጆች በዋነኛነት በትምህርት ቤት ውስጥ ስኬታማ እንዲሆኑ፣ እነሱ ምን ማደረግ እንዳለባቸው፣ እንዴት ማድረግ እንዳለባቸው እና ተግባሩን ለማከናወን የሚያስፈልጉትን ክህሎቶች እንዴት ማስተባበር እንዳለባቸው ማወቅ አለባቸው። ልጆች ግፊቶችን መቆጣጠር ፣ በርካታ ተግባራትን ማከናወን ፣ መመሪያዎችን መከተል እና ትኩረት ማድረግን መማር አለባቸው። ስለነዚህ የማስፈጸም ስራ ክሆሎቶች እና እነሱን እንዴት ማስተማር እንደሚቻል አስፈላጊነቱ ላይ ዛሬ ትልቅ ፍላጎት አለ። እነዚህን ክህሎቶች አስተማሪዎች እና የቤተሰብ አባሎች በሚይሳዩበት እና በሚያስተምሩበት ጊዜ ወጣት ልጆች ሊያድብሯቸው ይችላሉ። አስተማሪዎች ልጆች ትኩረት እንዲያደርጉ እና እንዲመርጡ በሚደግፍ መልኩ አከባቢውን በማደራጀት ልጆችን መርዳት ይችላሉ። አስተማሪዎች በርካታ ደረጃዎች ያሏቸውን መመሪያዎች መተግበርን እንዲለማመዱ ሆን ብለው መልመጃዎች መስጠት ይችላሉ። በተጨማሪ ልጆች አዲስ ነገሮች ለመማር አስቀድመው የሚያውቁትን በመጠቀም የሚፈልጉትን እና ትርጉም ያላቸውን አርእስቶችን እንዲያስሱ እና እንዲመረምሩ እድሎችን መስጠት ይችላሉ። እነሱ ልጆች ምን እየተማሩ እንደሆነ እና እንዴት እንደተማሩት እንዲያወሩ ማበረታታት ይችላሉ። እንዲሁም ልጆች አንድን ሥራ ለማከናወን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እንዴት እንደሚወስኑ የሚረዳ ከራስ ጋር የመነጋገር ሞዴል ማድረግ ይችላሉ ።

**መግባባት እና ቋንቋ** ሌሎችን ለመረዳት መማር እና ለመግባባት ቋንቋን መጠቀምን ያካትታል። በቅድመ መዋዕለ ሕጻናት እና በመዋእለ ህፃናት ደረጃዎች፣ ለበለጠ ግልጽነት መስፈርቶቹ በንኡስ ክፍሎች ተከፍለዋል፣ **መረዳትና መተባበር** ፣ **እውቀት እና ሃሳቦች ማቅረብ** ፣ **የቃላት እውቀት እና አጠቃቀም** እና **የመደበኛ እንግሊዝኛ ልምዶች** ።

የ **ማንበብና መጻፍ** መመዘኛዎች ትናንሽ ልጆችን ለመረጃዊ ፅሁፎች እና ሥነጽሑፎች ከልጅነታቸው ጀምሮ ተጋላጭ እንዲሆኑ የማድረግ ከፍተኛ ትኩረት ያመለክታሉ ፡፡ በተጨማሪ ከመሠረታዊ **የጽሁፍ ፅንሰ-ሀሳቦች** ፣ ልጆች በጽሑፎቹ ውስጥ ስላሉት **ቁልፍ ሀሳቦች እና ዝርዝሮች** እና በጽሁፎች ላይ ስላለው **ጥበብ እና አወቃቀር** እንዴት ማሰብ እንደሚችሉ መማር ይጠበቅባቸዋል። እነሱ ስላነበቧቸው እና ስለሚሰሙት ነገር በመናገር እና በመፃፍ ስለ **የእውቀት እና የሃሳቦች ውህደት** ይማራሉ። እነሱ በ **ፎኖሎጂካል ግንዛቤ / ፎኒክስ እና በቃላት መለያ** ልዩ ክህሎቶች እንዲያዳብሩ ይጠበቅባቸዋል። የ **ጽሑፍ ዝግጅት እና ስርጭት** አከባቢ የመፃፍ እና የመጻፍ እና የመሳል አላማን መረዳትን ሁለቱንም ያካትታል።
በመጨረሻም፣ ልጆች ስለሚማሩት ነገር ሲጽፉ እና ታሪኮችን ሲጽፉ ስለ ተለያዩ **የጽሑፍ ዓይነቶች እና ዓላማዎች** ይማራሉ።

የ **ሂሳብ** መመዘኛዎች ስለ **ምደባ** እና **ፓተርኖች** የሚጠበቁ ነገሮች ለመማር የሚያስፈልጉ ነገሮችን ያካትታሉ፣ ነገር ግን ለታዳጊ ሕፃናት በጣም አስፈላጊው አፅንኦት ሊሰጠው ነገር የቁጥርን ሀሳብ የማሳደግ ክህሎት ነው።

- **የቁጥር ስሞችን እና የቁጥሩን ቅደም ተከተል ያውቃል**
- **የእቃዎችን ብዛት ለመንገር ይቆጥራል**
- **ቁጥሮችን ያነፃፅራል**
- **መደመርን አንድ ላይ አስቀምጦ መደመርን አድርጎ መረዳት እና መቀነስን ደግሞ መለያየት እና ከዚያ ላይ መውሰድን አድርጎ መረዳት**
- **ልኬት በዚህ ግምት ተካትቷል፣ ሊለኩ የሚችሉ ባሕሪያትን ያገልጻል እና ያነፃፅራል**
- **ጂዮሜትሪ ከእነዚህ ግምቶች ተካትቷል ቅርጾችን እና የነገሮችን አንፃራዊ አቀማመጥ ይለያል እና ይገልጻል**

የ **ሳይንስ እና የኢንጂነሪንግ** መስፈርቶች የ **ህይወት ያላቸው ነገሮች** ፣ **አካላዊ እቃዎች**፣ **የምድር እና የቦታ ባህርዮች** እና **ኢኒጂነሪንግ** ጎራዎችን ያካትታሉ። የእያንዳንዱ ጎራ መለኪያዎች ልጆች በተገቢው አመት መጨረሻ ምን ማወቅ ፣ መረዳትና ማድረግ መቻል እንዳለባቸው በግልጽ ያሳያሉ። መለኪያዎች ለጨቅላ ህጻናቶች፣ ታዳጊዎች፣ ሁልት አመቶች፣ ቅድመትምህርት ቤት፣ ቅድመ መዋእለ ህጻናት እና መዋእለ ህጻናት አመታት ያሉትን ያካትታሉ። የመጀመሪያ እንክብካቤ እና ትምህርት የሰው ኃይል አባላት በጣም ትንንሽ ልጆችን ለሳይንሳዊ ዳሰሳ እንዲጋለጡ ማድረጋቸው አስፈላጊ ነው ፣ልጆች ህይወት ካላቸው ነገሮች፣እቃዎች እና አካባቢ ጋር ይገናኛሉ፣ ያስሳሉ ፣ይመለከታሉ፣ያስተውላሉ፣ይለያሉ እና ይገልጻሉ። በእያንዳንዱ ጎራ ውስጥ ያሉትን መለኪያዎች ለማሟላት የልጆችን የእድገት ሂደት ሲገልጹ እነዚህን ቃላት ሆን ብሎ መጠቀመም አስፈላጊ ነው። ከ NGSS የተገኙት ከአፈጻጸም የሚጠበቁ ነገሮ ለመዋለ ህፃናት አመት እንደ መለኪያዎች ተካተዋል። የእያንዳንዱ አመት መለኪያዎች "ሶስቱን ገጽታዎችን በጥልቀት ያቆራኛሉ -የሳይንስ እና የኢንጂነሪንግ ልምዶች ፣ የስነምግባር ዋና ሀሳቦች እና የተያያዙ-ጽንሰ-ሀሳቦች።" [9] ከዚህ በታች ያለው ሰንጠረዥ የእያንዳንዳቸውን የሶስት ገጽታዎች ክፍሎችን ያብራራል ።

| የሳይንስ እና የኢንጂነሪንግ ልምዶች | የስነምግባር ቁልፍ ሀሳቦች | የተያያዙ ጽንሰ ሀሳቦች |
|---|---|---|
| 1. ጥያቄዎችን መጠየቅ እና ችግሮችን መተርጎም<br>2. ሞዴሎችን መስራት እና መጠቀም<br>3. ምርመራዎችን ማቀድ እና ማካሄድ<br>4. ዳታን መመርመር እና መተርጎም<br>5. የሂሳብ እና የሂሳብ አስተሳሰብን በመጠቀም<br>6. ማብራሪያዎችን መገንባት እና መፍትሄዎችን መንደፍ<br>7. ከማስረጃ ተነስቶ ክርክር ላይ መሳተፍ<br>8. መረጃን ማግኘት፣ መመርመር እና መግለጽ | **ፊዚካል ሳይንስ**<br>• ማተር እና መስተጋብሮቹ<br>• እንቅስቃሴ እና እርጋታ፣ ሀይሎች እና መስተጋብሮች<br>• ሀይል<br>• ሞገዶች እና መተግበሪያዎቻቸው<br>**ላይፍ ሳይንስ**<br>• ከሞለኪዩሎች ወደ ተህዋስያን፣ መዋቅሮች እና ሂደቶች<br>• ሥነ ምህዳሮች፣ መስተጋብሮች፣ ኢነርጂ እና ዳይናሚክስ<br>• የዘር ውርስ፣ ውርስ እና የባህሪዎች ልዩነት<br>• ባዮሎጂካል ዝግመታዊ ለውጥ አንድነት እና ልዩነት<br>**የመሬት እና የህዋ ሳይንሶች**<br>• የመሬት ቦታ በዩኒቨርስ<br>• የመሬት ሲስተሞች<br>• መሬት እና ሰብዓዊ እንቅስቃሴ<br>**ኢንጂነሪንግ፣ ቴክኖሎጂ እና የሳይንስ ትግበራዎች**<br>• ኢንጂነሪንግ ዲዛይን<br>• በኢንጂነሪንግ፣ ቴክኖሎጂ፣ ሳይንስ እና ማህበረሰብ ያለ ግንኙነት | 1. ፓተርኖች<br>2. ምክንያት እና ውጤት<br>3. ሚዛን፣ ተመጣጣኝነት እና ብዛት<br>4. ሲስተሞች እና የሲስተም ሞዶሎች<br>5. ኃይል እና ቁስ አካል<br>6. አወቃቀር እና ተግባር<br>7. መረጋጋት እና ለውጥ |

**ማህበራዊ ጥናቶች** መስፈርቶች ከልደት እስከ ቅድመ መዋዕለ ሕፃናትን ይሸፍናሉ ፡፡ አስተማሪዎች የማህበራዊ ጥናቶች ትምህርትን ከታዳጊ ልጆች ጋር የሚገነቡት ራስን፣ ቤተሰብን እና የተለያዩ ማህበረሰብን በመረዳት ማእቀፍ ውስጥ ነው። በተጨማሪም ልጆች በሰዎች እና በሚኖሩበት አካባቢ መካከል ስላለው ግንኙነት ግንዛቤን ያዳብራሉ እንዲሁም ጊዜን ከራስ ፣ ከቤተሰብ እና ከማህበረሰብ ጋር ካለው ግንኙነት አንጻር ግንዛቤ እንዳላቸው ያሳያሉ። ልጆች ከቅድመ መዋዕለ ሕጻናት በሚወጡበት ጊዜ ፣ **የሰዎች ባሕርያትን ማወቅ ፣ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ያለን ህይወት እውቀት** እና ከሚታወቁ **ሰዎች እና ቦታዎች ጋር የተዛመደ ለውጥን አስመልክቶ እውቀታቸው ማደግ አለበት።**

**የሥነጥበብ** መመዘኛዎች ከልደት እስከ ቅድመ መዋዕለ ሕጻናት ይሸፍናሉ ፡፡ ምንም እንኳን መምህራን በመጀመሪያዎቹ ዓመታት ለታዳጊ ሕፃናት ብዙ ከኪነ-ጥበብ ጋር የተገናኙ ልምዶችን እንዲያወጡ ቢጠበቅባቸውም፣ ለሕፃናት የስነጥበብ ደረጃን የሚደግፉ ጠቋሚዎች ግን አልተገለጹም ፡፡ ሆኖም፣ የመጀምርያ እንክብካቤ እና ትምህርት ባለሞያዎችን በተከታዩ የእድሜ ቡድኖች ካሉት መስፈርቶች ጋር የተጣጣሙ ተግባሮችን ለመንደፍ የሚረዳ ደጋፊ ልምዶች ይቀርባሉ። የጥበብ ልምዶች **ሙዚቃ እና እንቅስቃሴ ፣ ድራማ** እና **የእይታ ጥበባት ጽንሰ-ሀሳቦችን እና መግለጫዎችን ያካትታሉ።**

**የህፃናት ማህበራዊ እና ስሜታዊ እድገት** ሁልንም የእድገት ቦታዎችን የሚነካ በመሆኑ የትምህርታቸው ዋና መሰረት ነው። ራስን የመቆጣጠር ክህሎቶች ቀደም ሲል የተጠቀሱትን የሥራ አፈፃፀም ክህሎቶችን ለማዳበር ወሳኝ ናቸው **የመማር/ሎጂክ እና አመክንዮ ዘዴዎች** ልጆች በማህበራዊ እና ስሜታዊ ሲያድጉ የሚማርዋቸው ናቸው። ልጆች ከሌሎች ጋር አወንታዊ ግንኙነቶች ለማሳደግ በሜረዱ መልኩ በሚደግፉ **ስሜቶች እና ባህሪዎች** እንዴት መግለፅ እንዳለባቸው መማር አለባቸው። እነሱ አዋቂዎች እየደገፏቸው ስሜቶችን ሲገነዘቡ እና ስሜቶችን ሲለዩ እና ህጎችን ማዘጋጀት እና ገደቦችን እና የሚጠበቁ ነገሮችን ሲያከብሩ፣ እነሱ በትምህርት ቤት እና በህይወታቸው በጣም ዋጋ ያለው ልምዶችን ያገኛሉ። **አዎንታዊ ግንኙነቶች** ለዚህ እድገት በጣም አስፈላጊ ናቸው እናም አስተማሪዎች እና ልጆች እርስበርስ አወንታዊ ግንኙነቶችን ማዳበራቸው በጣም አስፈላጊ ነው። የእነዚህ ግንኙነቶች አካል እንደመሆናቸው መጠን፣ አስተማሪዎች በመማሪያ ክፍል በመደበኛነት የሚፈጠሩ ማህበራዊ ችግሮችን የሚፈቱበትን መንገዶች ይመሯቸዋል። ከሌሎች ልጆች ጋር እንዴት መግባባት እና ግንኙነቶችን እንዴት ማዳበር እንደሚቻል ለታዳጊ ሕፃናት ቁልፍ የትምህርት ተሞክሮ ነው። አስተማሪዎች ልጆች አብረው እንዲሰሩ የሚያበረታቱ ትርጉም ያላቸው እና አሳታፊ የጨዋታ ልምዶችን ሲያቅዱ፣ ልጆች በስርዓተ ትምህርቱ ውስጥ አስፈላጊ ክህሎቶችን እና ፅንሰ ሀሳቦችን በሚማሩበት ጊዜ ልጆች ከሌሎች ጋር መግባባትና ጓደኝነትን ይማራሉ።

**አካላዊ እድገት ትልቅ-ጡንቻ ጥንካሬ እና ቅንጅት** እና **አነስተኛ የጡንቻ ጥንካሬ እና ቅንጅትን ያካትታል** ። በትምህርት ቤቱ ውስጥ የአካዳሚክ ትኩረቱ እየጨመረ ሲሄድ፣ አካላዊ ብቃት እና ቅንጅት ለልጅ ሁለንተናዊ እድገት አስፈላጊ መሆኑን ማስታወስ ጥሩ ነው። ስለራሳቸው አካል ጥሩ ስሜት የሚሰማቸው ልጆች አብዛኛውን ጊዜ በትምህርት ቤት ውስጥ የበለጠ ስኬታማ ናቸው። **ጤና እና ደህንነት** ስለ ህጎች ፣ ራስን ስለመግዛት ክህሎቶች፣ የአመጋገብ እና የአካላዊ ወሰኖችን መግልጽን ያካትታል።

## ልደት – ሶስተኛ ክፍል ቀጣይ የትምህርት መስፈርቶች

የሚከተለው ሠንጠረዥ ከ Head Start Early Learning Outcomes Framework ፣ [11] የ *የኮሎምቢያ ግዛት የመጀመርያ ትምህርት መስፈርቶች* የthe Common Core State Standards for English Language Arts and Mathematics[12] እና የ NGSS ጋር የተጣጣሙ ቀጣይነት ያለው ከእድገት እና ከትምህርት የሚጠበቁ ነገሮችን ያብራራል።

| | ጨቅላ ህጻናቶች | ታዳጊዎች | ሁለት አመት ልጆች | ቅድም ትምህ ርት ቤት | ቅድመ-መዋእለ ህጻናት መውጫ | K-3 መውጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የመማር/ሎጂክ እና ምክንያታዊነት ዘዴዎች | X | X | X | X | X | ተገቢነት የለውም |
| መግባባት እና ቋንቋ | X | X | X | X | X | የታወቁ ዋና የመንግስት መለኪያዎች |
| ማንበብ እና መጻፍ | X ከጥቂት የሚጀምሩ መስፍረቶች ጋር * | X | X | X | X | የታወቁ ዋና የመንግስት መለኪያዎች |
| ሂሳብ | X ከጥቂት የሚጀምሩ መስፍረቶች ጋር * | X | X | X | X | የታወቁ ዋና የመንግስት መለኪያዎች |
| ሳይንስ እና ኢንጂነሪንግ | X | X | X | X | X | NGSS |
| ማህበራዊ ጥናቶች | X | X | X | X | X | ተገቢነት የለውም |
| ዘ አርትስ | X ከጥቂት የሚጀምሩ መስፍረቶች ጋር * | X | X | X | X | ተገቢነት የለውም |
| ማህበራዊ እና ስሜታዊ እድገት | X ከጥቂት የሚጀምሩ መስፍረቶች ጋር * | X | X | X | X | ተገቢነት የለውም |
| የአካል እድገት / ጤና እና ደህንነት | X | X | X | X | X | ተገቢነት የለውም |

* “ጀማሪ” በዚህ አካባቢ የልጁ ክህሎቶች ማደግ እየጀመሩ መሆኑን ለመግለጽ የሚያገለግል ነው።

የታዩ ሙሉ የማጣቀሻዎች ዝርዝር ፣ ግብአቶችን ፣ የመመዘኛ መሳሪያዎችን እና የታዩ የመንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት መመዘኛዎችን ለማግኘት ፣ እባክዎን የ OSSE ድርጣቢያ ይጎብኙ በ https://osse.dc.gov/publication/district-columbia-common-core-early-learning-standards-dc-ccels።

## ምስጋናዎች

የመንግስት የትምህርት ዋና ተቆጣጣሪ ቢሮ (OSSE) የተሻሻለውን የኮሎምብያ ግዛት *የመጀመርያ ትምህርት መስፍረቶችን* ለማዘጋጀት እና ለመመርመር እውቀታቸውን እና ጊዜያቸውን ላበረከቱ ሰዎች እውነተኛ የሆነውን ምስጋና ያቀርባል። ልዩ ምስጋና ለ WestEd's Mid- Atlantic አጠቃላይ ማእከል እና የመስፈርቶች እና መመዘኛ አፈጻጸም ማእከል፣ ብሄራዊ የአየር እና የስፔስ ሙዚየም፣ ስሚዝሶኒያን ተቋም፣ ብሔራዊ የሥነ-እንስሳት ፓርክ ፣ የዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ፣ KIPP DC ፣ ቤርያ የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤት ፣ ትሪኒቲ ዋሺንግተን ዩኒቨርሲቲ ፣ ብሔራዊ የሥነ ጥበብ ማእከል ፣ ኢማጂኔሽን ስቴጅ፣ የባለሞያ እውቅና ሰጭ ካውንስል፣ የኮሎምቢያ ግዛት ዩኒቨርስቲ ኮሙኒቲ ኮሌጅ፣ የባይነም ቤተሰብ ፋውንዴሽን፣ የዲሲ የህጻን እድገት ተቋማት 2018–19 OSSE ተቀባዮች እና የ OSSE የስራ ባልደረቦችን ይህን ሰነድ ለማሻሻል ላልተቋረጠ ድጋፋቸው ። እነሱ በኮሎምቢያ ግዛት ውስጥ የመጀመርያ እንክብካቤ እና ትምህርት ጥራትን ለማሻሻል ፈጻሚዎች፣ የልጅ እና ቤተሰብ ተማጓቾች እና የሚመለከታቸው ዜጎች በመሆን አገልግለዋል ።

## ማስታወሻዎች

[1] Administration for Children and Families (2015). Head Start Early Learning Outcomes Framework. የተወሰደው ከ https://eclkc.ohs.acf.hhs.gov/sites/default/files/pdf/elof-ohs-framework.pdf

[2] U.S. Departments of Health and Human Services and Education (2017, January 5). Policy Statement on Supporting the Development of Children who are Dual Language Learners in Early Childhood Programs. የተወሰደው ከ /www.acf.hhs.gov/sites/defree/files/ecd/dll guidance document final.pdf

[3] U.S. Departments of Health and Human Services and Education (2017, January 5). Policy Statement on Supporting the Development of Children who are Dual Language Learners in Early Childhood Programs. የተወሰደው ከ www.acf.hhs.gov/sites/defree/files/ecd/dll guidance document final.pdf

[4] Ibid.

[5] Ibid.

[6] U.S. Department of Education (2015, December 10). Every Students Succeeds Act. የተወሰደው ከ www.congress.gov/114/plaws/publ95/PLAW-114publ95.htm

[7] National Association for the Education of Young Children (NAEYC) and the National Association of Early Childhood Specialists in State Departments of Education (NAECS/SDE) (2003, November). Building an Effective, Accountable System in Program for Children Birth through Age

[8] የተወሰደው ከ www.naeyc.org/sites/default/files/globally-shared/downloads/PDFs/resources/position-statements/pscape.pdf

[9] Vermont Agency of Education & Vermont Department for Children and Families (2015). Vermont Early Learning Standards. የተወሰደው ከ http://education.vermont.gov/sites/aoe/files/documents/edu-early-education-early-learning-standards.pdf

[10] Next Generation Science Standards Lead States (2013). Building an Effective, Accountable System in Program for Children Birth through Age 8. የተወሰደው ከ http://epsc.wustl.edu/seismology/book/presentations/2014 Promotion/NGSS 2013.pdf

[11] U.S. Department of Health and Human Services. (2015). Head Start early learning outcomes framework: Ages birth to five. Washington, DC: Administration for Children and Families, Office of Head Start. የተወሰደው ከ https://eclkc.ohs.acf.hhs.gov/sites/defree/files/pdf/elof-ohs-framework.pdf

[12] National Governors Association Center for Best Practices, & Council of Chief State School Officers (2010). Common core state standards for Mathematics, English language arts & literacy in history/social studies, science and technical subjects. Washington, DC. የተወሰደው ከ www.corestandards.org/read-the-standards/

| የትምህርት/ሎጂክ እና አመክን ዮ ዘዴዎች | ጨቅላ ህጻናቶች | ታዳጊዎች | ሁለት አመት ልጆች |
|---|---|---|---|
| መስፈርቶች | አመላካቾች | አመላካቾች | አመላካቾች |
| 1. በጉጉት መከታተል እና መሳተፍ | 1a. እቃዎችን እና አከባቢዎችን ለማሰስ ሁሉንም ስሜቶች ይጠቀማል<br><br>*ለምሳሌ፣*<br><br>• ለስላሳ መጫወቻን መመልከት፣ መያዝ እና እንዲቅጨለጨል ማወዛወዝ፣ ወደ አፍ ያስገቡ እና ይመጡታል ።<br><br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br><br>• ሕፃናት እንዲመረመሩ የሚያስችላቸው አስተማማኝ ቦታዎችን እና ቁሳቁሶችን ያቅርቡ።<br><br>• የታወቁ እና ያልታወቁ ነገሮችን (ለምሳሌ፣ መጽሐፍት፣ ማንኪያ ፣ የመጫወቻ ተሽከርካሪዎች፣ ወዘተ) በመጠቀም ስሜታዊ አሰሳ እንዲያደርጉ ዕድሎችን ይስጡ እና ለህጻናት እየሞከሩት ያለ ነገር ምን እንደሆነ ይግለጹላቸው (ስሜት፣ መስማት፣ መንካት፣ መቅመስ፣ ማሽተት፣ ማየት፣ ወዘተ ።)። | 1a. እቃዎችን ያንቀሳቅሳል፣ ሁሉንም ስሜቶች በመጠቀም አከባቢዎችን ይመለከታል እንዲሁም ይዳስሳል<br><br>*ለምሳሌ፣*<br><br>• የሚደረደሩ ኩባያዎችን መጣል፣ ዙሪያውን መበታተን እና በድጋሚ ለመደርደር መሞከር ።<br><br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br><br>• ታዳጊዎች በእቃዎች (ለምሳሌ፣ ኩባያ ወይም ስፖንጆች) ምን ሊደረግ እንደሚችል እንዲያስተውሉ ያበረታቱ፣ “I wonder what will happen when I put the cup in the water?” [“ኩባያውን ውሃው ውስጥ ስጨምረው ምን ሊሆን ሊሆን ይችላል?”]<br><br>• ለስሜታዊ ማነቃቂያ የሚሆኑ አስተማማኝ እቃዎችን እና የተለያዩ ቀለማት፣ ይዘት፣ ድምጾች፣ ቅርጾች ወይም ሽታዎች ያላቸውን ተሞክረዎች ማቅረብ (ለምሳሌ ኩባያዎችን መደርደር፣ ሳጥኖችን፣ ኳሶችን፣ የሙዚቃ መሳሪያዎችን፣ ወዘተ ቅርጽ ማስያዝ።)። | 1a. አዳዲስ ቦታዎችን እና እቃዎችን ይመረምራሉ፣ የተለያዩ ተግባሮችን በተለይም የአዋቂ ድጋፍ ያላቸውን ይመርጣሉ<br><br>*ለምሳሌ፣*<br><br>• በአሸዋው ውስጥ አንድ ጉድጓድ ቆፍሩ ፣ ደረቅ አሸዋው ወደ ጉድጓዱ ውስጥ ሲገባ ይመልከቱ እና ለማስተካከል እንዲያግዛቹ አስተማሪውን ጠይቁ ።<br><br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br><br>• ልጆች የሚመራመሩባቸው የተለያዩ የታወቁ እና ያልታወቁ ተሞክሮዎችን እና እቃዎችን (ለምሳሌ፣ ኩባያዎችን መደርድር፣ የሳጥን ቅርጾች፣ ኳሶች፣ የሙዚቃ መሳሪያዎች፣ ወዘተ) ያቅርቡ። |
| 2. ጽናትን ማሳየት | 2a. እይታዎችን እና ድምጾችን ይከታተላሉ<br><br>*ለምሳሌ፣*<br><br>• ለምሳሌ መጫወቻ ወይም እቃ ይጣሉ እና ይፈልጉት።<br><br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br><br>• ሕፃናት እቃዎችን እንዲመረምሩ (ለምሳሌ፣ መፅሀፍቶች፣ የድራማዊ ጨዋታ መጫወቻዎች፣ ወዘተ) ለማበረታታት አከባቢውን እና የእለተተለት ፕሮግራሙን ያስተካክሉ እና እነሱ እስከፍለጉ ጊዜ ድረስ ከሰዎች ጋር እንዲያወሩ ያድርጉ።<br><br>• ልጁ ፍላጎት ካሳየ ተግባሮችን እና ተሞክሮዎችን በተደጋጋሚ ያቅርቡ። | 2a. ውጤትን ለማግኘት በማቀድ ድርጊቶችን ይደግማል<br><br>*ምሳሌዎች፣*<br><br>• ጡቦችን በባልዲ ውስጥ ማስቀመጥና በተጋጋሚ መድፋት።<br><br>• የሚወዱትን መጽሀፍ አብዛኛውን ጊዜ የሚቀመጥበት ቦታ ላይ መፈለግ።<br><br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br><br>• ልጆች አዲስ ክህሎቶችን እንዲደግሙ እና እንዲለማመዱ የሚያበረታቱ እቃዎችን (ለምሳሌ፣ የሚደረደሩ ኩባያዎች፣ የሳጥን ቅርጾች፣ ኳሶች፣ የሙዚቃ መሳርያዎች፣ ወዘተ ) ማቅረብ። | 2a. በራስ በተመረጠ ተግባር መስራትን መቀጠል፣ በተለይም የአዋቂ ድጋፍ ታክሎበት<br><br>*ለምሳሌ፣*<br><br>• የራሳቸውን ያክል ቁመት እስኪያክሉ ደረስ ትልቅ የካርቶን ጡቦችን ለመደርደር ከአዋቂዎች ጋር ይሰራሉ።<br><br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br><br>• ያሉት ልምዶቻቸው ላይ እንዲያሳድጉ የሚረዱ ፈታኝ ነገር ግን ሊሳኩ የሚችሉ እንቅስቃሴዎችን እና ተግባሮችን ያቅርቡ (ለምሳሌ፣ የካርቶን ጡቦች መደርደር፣ተያያዥ መጫወቻዎች) |

| ቅድም ትምህርት ቤት | ቅድመ መዋእለ ህጻናት ለመውጫ የሚጠበቁ ነገሮች | መዋእለ ህጻናት የመውጫ ተስፋዎች |
|---|---|---|
| አመላካቾች | አመላካቾች | |
| 1a. የሚፈልጉትን ተግባሮችን ይመርጣሉ፣ ለአዋቂዎች ማበረታቻ ምላሽ ይሰጣሉ<br><br>*ለምሳሌ፣*<br><br>• ፍቃደኛ የሆነ ወላጅ ጥረታቸውን፣ “You turned it and now it fits.” [“ አሁን ገለበጥከው እና አሁን ይገጥማል”] እያሉ እያበረታቷቸው አዲስ ባለ አምስት ንጥል እንቆቅልሽን ይሰራሉ።<br><br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br><br>• በመማሪያ ክፍል ውስጥ እቃዎችን ማዞር (ለምሳሌ፣ በምርምር ቦታ፣ ማግኔቶችን እና መግነጢሳዊ እቃዎችን የሚመዝኑ ሚዛን ያስቀምጡ)። | **የመማር ዘዴዎች**<br><br>1a. የተለያየ ማእቀፍ ያላቸውን አርእስቶች ፣ ሀሳቦች እና ተግባራት ውስጥ ፍላጎት በማሳየት ለመማር ያላቸውን ጉጉት ያሳያሉ<br><br>*ለምሳሌ፣*<br><br>• በሚመጣው ጊዜ ወደ ቤተ-መጽሐፍቱ ስለሚደረገው ጉዞ ፣ ተማሪዎቹ እንዴት እንደሚሄዱ እና መጽሃፍትን ማየት ይችሉ እንደሆነ ጨምሮ ጥያቄዎችን ይጠይቁ።<br><br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br><br>• የጥናት ርዕሶችን ሲመርጡ የልጆችን ፍላጎት በመከተል የልጆችን ፍላጎቶች ማበረታታት። | |
| 2a. ፈታኝ ቢሆኑም ያለውን እንቅስቃሴ ይቀጥላሉ፣ሊያቆሙ እና መጨረሻ ላይ እራሳቸው ወደመረጡት እንቅስቃሴ ሊመለሱ ይችላሉ<br><br>*ለምሳሌ፣*<br><br>• ቀለሞች አንድ ላይ ሲሄዱ መሳል ያቁሙ። የስዕሉ የተወሰኑት ክፍሎች እስኪደርቁ ድረስ እንዲጠብቁ ከጠቆሙ በኋላ መሳል መቀጠል።<br><br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br><br>• የክፍል ጓደኛን እርዳታ እንዲጠይቁ በመጠየቅ ልጆች ብቻቸውን ማጠናቀቅ የማይችሉትን ተግባሮች እና እንቅስቃሴዎች እንዲያጠናቅቁ መደገፍ። | 2a. የሚያቋርጡ እና ሀሳብ የሚበታትኑ ነገሮች ቢኖሩም እንኳን፣ፈታኝ የሆነ፣እራሳቸው የመረጡትን እንቅስቃሴ ይረዳሉ እና ለማጠናቀቅ ይጥራሉ<br><br>*ለምሳሌ፣*<br><br>• ለበርካታ ቀናት በመስራት፣ ከተለያዩ የእቃዎች አይነት የተለያዩ መዋቅሮችን ይሰራል።<br><br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br><br>• ልጆች ረዘም ላለ ጊዜ በእንቅስቃሴዎች እንዲሳተፉ እና ከበርካታ ቀናት በኋላ ወደ ፕሮጀክቶቻቸው እንዲመለሱ እድል ይስጡ። | |

| የትምህርት/ሎጂክ እና አመክን ዮ ዘዴዎች | ጨቅላ ህጻናቶች | ታዳጊዎች | ሁለት አመት ልጆች |
| --- | --- | --- | --- |
| መስፈርቶች | አመላካቾች | አመላካቾች | አመላካቾች |
| 3. ተግባሮችን በተለዋዋጭነት ይቀበላል | 3a. ሌሎች አንድን ሥራ እንዴት እንደሚሰሩ ያስተውላሉ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• በጣት ጨዋታ ወቅት ጭንቅላትን ወደ አዋቂ ሰው ማዞር።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• በእንግሊዝኛ ወይም በሌሎች የአገር ቤት ቋንቋ(ዎች) በተደጋጋሚ መዝሙሮችን መዘመር፣ ታሪኮችን ማንበብ፣ መደነስ እና የጣት ጨዋታዎችን መለማመድ።<br>• የሚያነቃቁ መጫወቻዎችን ማስተዋወቅ እና መደጋገም፣ (ለምሳሌ፣ የሚንኮሻኮሽ ነገር፣ ጨርቆች) ጨዋታውፐች (ለምሳሌ፣ አየሁህ/ሽ ጨዋታ) እና ጉጉት እና ፈጠራን የሚያበረታቱ ድምጾች ። | 3a. ሌሎች አንድን ሥራ እንዴት እንደሚሠሩ ያስተውላሉ እና ድርጊታቸውን ይሞክራሉ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• አስተማሪው ከህፃን ልጅ ጋር አየሁህ ጨዋታ ሲጫወት መመልከት እና ጨዋታውን መቀላቀል።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• የተለያዩ የሙዚቃ ዓይነቶችን ይጫወቱ እና በሙዚቃው የተለያዩ አይነት ማእቀፍ ያላቸውን ውዝዋዜዎች ያሳዩ። | 3a. የሙከራ እና የስህተት አቀራረቦችን መጠቀም፣ እርዳታ ይጠይቃሉ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• መጫወቻን ለማምጣት መሰላል ላይ ይቆማሉ እና ሊደርሱበት ሳይችሉ ሲቀር እርዳታ ይጠይቃሉ ።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• ለአዳዲስ ፈተናዎች ስለ አማራጭ መፍትሔዎች ያውሩ (ለምሳሌ፣ “We don’t have any more dolls. [“እኛ ተጨማሪ ሌሎች አሻንጉሊቶች የሉንም]። Why don’t you take care of the baby bunny? [”ሕፃኑን ጥንቸል ለምን አትንከባከቡም? ”] በማለት ሀሳብ ያቅርቡ።) |
| 4. ምልክቶችን ይጠቀማል እና በማስመሰል ሚናዎችን ይወስዳል | 4a. የሌሎች ሰዎች ቁሳቁሶችን የመጠቀም ፍላጎት ያሳያል<br>*ለምሳሌ፣*<br>• አንድ አዋቂ ሰው በከረጢቱ ላይ ተንቀሳቃሽ ሲያስቀምጡ ይመልከቱ ፣ እግሮቹን ይንኳኩ፣ ፈገግ ይበሉ፣ ወዘተ።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ጨቅላ ሕፃናት እንዲንከባለሉ፣ እንዲቆሙ እና እንዲንቀሳቀሱ እድል የሚሰጥ ቦታ ማቅረብ።<br>• ሕፃናትን አፋቸውን ተጠቅመው ዕቃዎችን እንዲያስሱ፣ የተለያዩ ዕቃዎችን እና አሻንጉሊቶችን (ለምሳሌ፣ የሚቅጨለጨል እቃ፣ አሻንጉሊት መጫወቻዎችን፣ ወዘተ) በመጠቀም እንዲያንቀሳቅሱ ይፍቀዱ።<br>• በእድገቱ ተገቢ የሆኑ ቁሳቁሶችን እና ቁሳቁሶችን አጠቃቀም ይመለከቱ (ለምሳሌ፣ ኳስ ማንከባለል እና የመቀመጫ-መቆም ትምህርት መራመድ)። | 4a. የሌሎችን ሰዎች ድርጊቶች እና የእቃዎችን አጠቃቀም መመልከት፣በማስመሰል ጨዋታ የሚታመኑ እቃዎችን መጠቀም<br>*ለምሳሌ፣*<br>• የመጫወቻ ቁልፎችን በካቢኔት በር ቁልፍ ውስጥ እንደሚከቱ ያስመስሉ።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• ለአንድ እቃ አዲስ አጠቃቃምን ሞዴል ያድርጉ ፣ እንደ መሬት ላይ አንድ ብሎክ መሄድ እና “Beep-beep! Here comes a school bus!” [“ቢፕ-ቢፕ! የትምህርት ቤት አውቶብስ መጣ!”] ብሎ ማስታወቅ።<br>• ከድራማዊ ጨዋታ ጋር የተያያዙ መጫወቻዎችን ማስተዋወቅ ይጀምሩ ( ለምሳሌ፣ ኩሽና፣ እንስራዎች፣ መጥበሻዎች፣ ሳህኖች ፣ ኩባያዎች፣ ወዘተ)። | 4a. የተለመዱ ክስተቶችን በድጋሚ ለመስራት ማበረታቻዎችን ይጠቀማል እና ድርጊቶችን ያስመስላል<br>*ለምሳሌ፣*<br>• በድራማዊ የጨዋታ ስፍራ አሻንጉሊትን መዳበስ፣ “እንኩሽ፣ እንኩሽ” የማለት ሰዓት ነው ብለው ይንገሩት እና በመጫወቻ አልጋ ላይ ማስተኛት።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• ልጆች ቁሳቁሶችን በሚመረምሩበት ጊዜ እንደ ቤተሰቦች፣ ስለሚያውቋቸው ነገሮች እንዲነጋገሩ ያበረታቷቸው (ለምሳሌ ፣ ስለ ላስቲክ የተለያዩ መጠኖች ማውራት፣ “Which cow is the mother? [“የትኛው ላም እናት ናት?] How about the baby? [ስለ ሕፃኑስ?] Which is the biggest cow?” [ትልቁ ላም የትኛው ነው?”])። |

| ቅድም ትምህርት ቤት | ቅድመ መዋእለ ህጻናት ለመውጫ የሚጠበቁ ነገሮች | መዋእለ ህጻናት የመውጫ ተስፋዎች |
|---|---|---|
| አመላካቾች | አመላካቾች | |
| 3a. እያንዳንዱን አማራጭ መሞከር ሳያስፈልግ መፍትሄዎችን ማግኘት፣ ዘዴን ሊቀይር ይችላል<br><br>*ለምሳሌ፣*<br><br>• በእጃቸው ሶስት ኳሶችን መሸከም በማይችሉበት ጊዜ መኪና ያምጡ።<br><br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br><br>• ችግር ፈቺነትን ያሳዩ (ለምሳሌ፣ በጣም ብዙ ልጆች በመጫወቻ ቤት ውስጥ መሆን ሲፈልጉ፣ ጠረጴዛውን ጨርቅ ያልብሱ እና ይጠይቁ፣ እና "Who wants to play in the tent?" ["በድንኳን ውስጥ መጫወት የሚፈልግ ማን ነው?"])። | 3a. ችግሮችን ለመፍታት እና ተግባሮችን ለማጠናቀቅ ብዙ ስልቶችን ይጠቀማል<br><br>*ለምሳሌ፣*<br><br>• የሞዴል ተሽከርካሪ ከካርቶን ሳጥኖች ለመገንባት አብረው ከሚማሩ የክፍል ጓደኞች ጋር አብረው ይስሩ።<br><br>3b. ከእኩዮች ጋር የትብብር እንቅስቃሴዎችን ይጀምራል<br><br>*ለምሳሌ፣*<br><br>• ለሁለት ሌሎች ልጆች እንዲህ ይበሉ፣ "Let's make a school bus out of this box." ["በዚህ ሳጥን ውስጥ የትምህርት ቤት አውቶቡስ እንስራ።"]<br><br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br><br>• ችግሩን እስከሚፈቱ ደረስ የአማራጭ መፍትሄዎችን ጥቅሞች እና ጉዳቶችን መወያየት፣ ልጆች የተለያዩ አማራጮችን እንዲሞክሩ ማበራታታት።<br><br>• ለትብብር ተግባራት በቂ ጊዜ ይስጡ እና እንደ የትብብር ግንኙነቶች አካል መወሰድ እና ማጋራትን ያበረታቱ። | |
| 4a. ከአንድ ወይም ከአንድ በላይ ልጆች ጋር መጫወት ለማስመሰል ፕሮፖኖችን ይጠቀማል፣ አንዱን ነገር ለሌላው ይተካዋል ፤እንቅስቃሴ ብዙውን ጊዜ በጭብጥ ላይ የተመሠረተ ነው<br><br>*ለምሳሌ፣*<br><br>• ለሁለት ልጆች ይንገሯቸው፣ "I'm a dinosaur. ["እኔ ዳይኖሰር ነኝ።] You'd better run. [ቢትሮጡ ይሻላቿል።] I'm going to eat you!" [እኔ ልበላችሁ ነው! "]<br><br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br><br>• ለድራማዊ ጨዋታ ለልጆች የተለያየ አይነት እቃዎችን ያቅርቡላቸው (ለምሳሌ፣ ለድራማ ጨዋታው አካባቢ "የሀኪም ቢሮ" የሚል ጽሁፍ ያለውን ምልክት ሊሰሩ ይችላሉ)። | **ምሳሌያዊ አስተሳሰብ**<br><br>4a. ሌሎች እቃዎቹን የሚወክሉ እቃዎችን ፣ ድርጊቶችን እና ምስሎችን ይጠቀማሉ<br><br>*ለምሳሌ፣*<br><br>• ሞዴል የእንስሳት መኖርያ ስፍራ(ዞ) ለመስራት ጡቦችን እና የእንሳሳት ቅርጽ አሻንጉሊቶችን መጠቀም።<br><br>4b. ለ10 ደቂቃዎች ርዝመት ላለው ጊዜ ከጥቂት ሌሎች ልጆች ጋር፣ በሁኔታዎች እና ሚናዎች በመስማማት ይጫወታል<br><br>*ለምሳሌ፣*<br><br>• በአሻንጉሊት እንስሳቶች፣ የቢሮ እቃዎች እና "የቤት እንሥሳ ባለቤት" ከሆኑ ልጆች ጋር በመጫወት፣ የእንስሳ ሀኪም መሆንን ማስመሰል።<br><br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br><br>• በዛፎች ጥናት ወቅት የጽድ ፍሬዎችን በሚመረመሩበት ጊዜ የተመለከቱትን እንዲመዘግቡ ለልጆች እቃዎችን ማቅረብ ።<br><br>• ጠንካራ ኮፍያዎችን እና የልጅ መጠን ያላቸውን አካፋዎችን ለልጆች በማቅረብ ልጆች የተለያዩ አይነት ሚናዎችን እንዲመረምሩ ማበረታታት ። | |

| መግባባት እና ቋንቋ | ጨቅላ ህጻናቶች | ታዳጊዎች | ሁለት አመት ልጆች |
|---|---|---|---|
| መስፈርቶች | አመላካቾች | አመላካቾች | አመላካቾች |
| 5. የንግግር ቋንቋን መረዳትን ማሳየት | 5a. የሌሎች ንግግር ላይ ፍላጎትን ማሳየት<br><br>*ለምሳሌ፣*<br><br>• የሚያወሩ ሰዎችን መመልከት<br><br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br><br>• ልጆችን ቀኑን ሙሉ ያዋሯቸው፣ ምን እያደረጉ እና እየሞከሩ እንደሆነ እየገለጹላቸው (ለምሳሌ፣ እንዲህ በማለት “You’re picking up green peas with your fingers.” [“እናንተ አረንጓዴ አተር በጣቶቻቹ እያነሳቹ ነው።”])። | 5a. ለሌሎች ንግግር እና የአካል እንቅስቃሴ ምላሽ መስጠት<br><br>*ለምሳሌ፣*<br><br>• ጫማ የሚለውን ቃል ሲሰሙ ጫማቸውን መንካት<br><br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br><br>• አዳዲስ ቃላትን ለማስተዋወቅ ዕቃዎችን እና ድርጊቶችን መግለጽ (ለምሳሌ እንዲህ ማለት “Here’s your dinosaur blanket with the soft ribbon fringe.” [“ ለስላሳ የሪባን ጫፍ ያለው የዳይኖሰር ብርድ ልብሳቹ ይህውና።”])። | 5a. ጮክ ብለው ለተነበቡ ቀላል አረፍተነገሮች ፣ ጥያቄዎች እና ቀላል ጽሑፎች ምላሽ ይሰጣሉ<br><br>*ለምሳሌ፣*<br><br>• የመጽሀፍን ሽፋን መግለጥ እና ተገቢ በሆነ ጊዜ “Where’s Spot?” ["ስፖት የት አለ?"] ማለት።<br><br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br><br>• ግንዛቤን እና የቃላት እውቀትን ለመጨመር መፅሃፎችን ማንበበ እና እንደገና ማንበብ። በስዕሎቹ እና በ ታሪኩ ላይ አስተያየት ይስጡ። |



| ቅድም ትምህርት ቤት | ቅድመ መዋእለ ህጻናት ለመውጫ የሚጠበቁ ነገሮች | መዋእለ ህጻናት የመውጫ ተስፋዎች |
|---|---|---|
| አመላካቾች | አመላካቾች | የታወቁ ዋና የመንግስት መለኪያዎች |
| 5a. አዳዲስ ቃላት እና ሀሳቦችን የሚሰጡ ጮክ ብለው ለተነበቡ ይበልጥ ውስብስብ ለሆኑ ጥያቄዎች ፣ አረፍተነገሮች እና ጽሑፎች ምላሽ ይሰጣሉ<br><br>*ለምሳሌ፣*<br><br>• በሚያጣብቅ ወረቀት ከሰራቹ በኋላ እጆችን የመታጠብ እና የማድረቅ መመሪያዎችን መከተል።<br><br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br><br>• በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ደረጃዎች መመሪያዎችን መስጠት። | **መረዳት እና መተባባር**<br><br>5a. እርዳታ ለመጠየቅ እና ለመስጠት ጥያቄዎችን መጠየቅ እና መመለስ፣ መረጃ ማግኘት እና መስጠት ወይም ያልተረዱትን ነገር ማብራራት<br><br>*ለምሳሌ፣*<br><br>• አስተማሪውን ለምሳ ዶሮ የሚበሉ መሆኑን፣ ምን አይነት እና ሶስት ብዛት የሚወስዱ መሆኑን ይጠይቁ።<br><br>5b. በአግባቡ ምላሽ በመስጠት የንግግር ቋንቋን መረዳትን ማሳየት<br><br>*ለምሳሌ፣*<br><br>• አስተማሪው በመማሪያ ክፍል ውስጥ ልጆች እየሮጡ በመሆኑ ምክንያት ምልክት ማድረግ እንደሚያስፈልጋቸው ሲገልጹ ምልክት ለመስራት ወረቀት ያግኙ።<br><br>*ደጋፊ ልምዶች*<br><br>• የፖሊስ ባለሚሎች ለጉብኝት ሲመጡ ሊጠይቋቸው የሚፈልጓቸውን ጥያቄዎች እንዲያስቡ ልጆችን ያበረታቷቸው።<br><br>• ልጆች የሚናገሩትን እንዲረዱ፣ መልእክትዎን በተጨባጭ እቃዎች እና እንቅስቃሴዎች በማሳየት መልእክትዎን ያብራሩ (ለምሳሌ “Watch how I always keep this foot in front when I gallop.” [“ስጋልብ ይህን እግር ሁልጊዜ እንዴት እንደማደርግ ተመልከቱ።”]) | **መረዳት እና መተባባር**<br><br>SL.K.2. ቁልፍ ዝርዝሮችን በተመለከተ ጥያቄዎችን በመጠየቅ እና አንድ ነገር ያልተረዱ ከሆነ ማብራርያ በመጠየቅ ጮክ ተብሎ የተነበበ ጽሁፍ በቃል ወይም በሌሎች ሚዲያ የቀረበ መረጃን መረዳትን ማረጋገጥ።<br><br>SL.K.3. እርዳታ፣ መረጃ ለማግኘት ወይም ያልተረዱትን ነገር ለማብራራት ጥያቄዎችን መጠየቅ እና መመለስ። |



| መግባባት እና ቋንቋ | ጨቅላ ህጻናቶች | ታዳጊዎች | ሁለት አመት ልጆች |
|---|---|---|---|
| መስፈርቶች | አመላካቾች | አመላካቾች | አመላካቾች |
| 6. እራስን ለመግለጽ ቋንቋ መጠቀም | 6a. ለመግባባት ባላቸው ጥረት ድምጾችን እና ምልክቶችን ይጠቀማሉ<br><br>*ለምሳሌ፣*<br><br>• መነሳት ሲፈልጉ መጮህ እና ወደሚያምኑት አዋቂ መጠጋት።<br><br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br><br>• የጨቅላ ህጻናትን መንተባተብ እነሱን በማዋራት ምላሽ መስጥት ። | 6a. ፍላጎቶችን እና የሚያውቋቸውን ሰዎች እና እቃዎች ለመግለጽ ቋንቋ ይጠቀማሉ<br><br>*ምሳሌዎች፣*<br><br>• ጡጧቸውን ሲያዩ፣ “Baba me” [“ባባ እኔ”] ይላሉ።<br><br>• እራሳቸውን ለመግለጽ ምልክቶችን ይጠቀማሉ (ለምሳሌ ፣ ፍላጎትን ለመግለጽ ወደ መጫወቻ ይጠቁማሉ)።<br><br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br><br>• ቀላል ጥያቄዎችን ይጠይቁ እና ታዳጊው ምላሽ ካልሰጠ መልሱን ይንገሩ (ለምሳሌ፣ “Is that a cat? [“ያ ድመት ነው?] Yes, that is a cat.” [አዎ፣ ያ ድመት ነው። ”])። | 6a. እቃዎችን እና ሰዎችን ለመግለጽ ቋንቋ መጠቀም እና እርዳታ መጠየቅ<br><br>*ለምሳሌ፣*<br><br>• ከላይ ለሚበር አውሮፕላን “Grandma go bye-bye.” [“አያቴ ሂጂ ባይ ባይ”] ብሎ በመናገር ምላሽ ይስጡ።<br><br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br><br>• የልጆች ቋንቋን ይገንቡ፣ የተሟላ አረፍተነገሮችን ለማሳየት ቃላቶችን ይጨምሩ እና አስፈላጊ ሲሆን በድጋሚ ይዘዙ። |



| ቅድም ትምህርት ቤት | ቅድመ መዋእለ ህጻናት ለመውጫ የሚጠበቁ ነገሮች | መዋእለ ህጻናት የመውጫ ተስፋዎች |
|---|---|---|
| አመላካቾች | አመላካቾች | የታወቁ ዋና የመንግስት መለኪያዎች |
| **ቅርጾችን እና አንጻራዊ የእቃዎች አቀማመጥን ይለያሉ እና ይገልጻሉ**<br>17a. ባለ ሁለት ጎን ቅርጾችን በትክክል ይጠራሉ (ካሬዎች፣ ክቦች፣ ሶስት ማእዘኖች፣ አራት ማእዘኖች)፣ አቀማመጣቸው ወይም መጠናቸው ምንም አይነት ቢሆንም እንኳን<br>*ለምሳሌ፣*<br>• በመማሪያ ክፍሉ ዙሪያ ይመልከቱ እና በጠረጴዛው የላይኛው ክፍል ምክንያት ብዙ ክቦች እና ካሬዎች መኖራቸውን ይጠቁሙ።<br>17b. መሰረታዊ ባለ ሁለት እና ሶስት ጎኖች ቅርጾችን ይገልጻሉ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ይግለጹ፣ “It has three sides and three points. [“ሶስት ጎኖች እና ሶስት ነጥቦች አሉት]። It’s a triangle.” [ሶስት ማእዘን ነው። ”]<br>17c. መሠረታዊ ቅርጾች ያላቸውን እቃዎችን ይገነባሉ (ኳስ / ሉል ፣ ስኩዌር ሳጥን / ኪዩብ ፣ ቱቦ / ሲሊንደር) እንደ ጣውላዎች ፣ ጡቦች ፣ የቧንቧ ማጽጃዎች ፣ ሸክላ እና የመሳሰሉ የተለያዩ እቅዎችን በመጠቀም ይገነባሉ።<br>*ለምሳሌ፣*<br>• በሚያጣብቅ ጭቃ ኳሶችን መስራት እና እምነበረድ ብለው መጥራት።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• የቅርጽ ማዛመድ ጨዋታዎችን እየተጫወቱ ቅርጾችን መስራት፣ ባለሶስት ማእዘንን ከባለሶስት ማእዘን እንደማዛመድ ።<br>• በጣትዎን በአየር ላይ የሚስሉትን ቅርፅ ልጆች ስሙን እንዲጠሩ ያድርጉ፣ፍንጮችን ይስጡ “Round and round…” [“መዞር እና መዞር…” ]<br>• ባለ ሶስት አቅጣጫዊ ሞዴሎችን በ ኪነጥበብ ስፍራው ላይ በማስቀመጥ፣ ልጆች የተለያዩ ቅርጾችን እንዲሰሩ በቁ እቃዎችን ያቅርቡ። | **ቅርጾችን ይለያሉ እና ይገልጻሉ (ካሬዎች፣ ክቦች፣ ሶስት ማእዘኖች፣ አራት ማእዘኖች፣ ስድስት ጎኖች፣ ኪዮቦች፣ ኮኖች፣ ስሊንደሮች፣ ስፌሮች)።**<br>K.G.1. የቅርጾችን ስሞች በመጠቀም በአካባቢ ውስጥ ያሉ ነገሮችን ይግለጹ እንዲሁም የእነዚህ እቃዎች አንጻራዊ አቀማመጦችን ከላይ፣ ከታች፣ ከጎን፣ ከፊት፣ ከኋላ እና ቀጥሎ የሚሉ ካላቶችን በመጠቀም ይግለጹ።<br>K.G.2. አቅጣጫዎቻቸው ወይም አጠቃላይ መጠናቸው ምንም ይሁን ምን ቅርጾችን በትክክል ይጠራሉ።<br>K.G.3. ቅርጾችን እንደ ባለሁለት አቅጣጫ ይለያሉ (በአውሮፕላን ውስጥ መተኛት፣ “ጠፍጣፋ”) ወይም ባለሶስት አቅጣጫ (“ጠጣር”)።<br>**ቅርጾችን መተንተን፣ ማወዳደር፣ መፍጠር፣ ማገናኘት ።**<br>K.G.4. ባለ ሁለት እና ሶስት አቅጣጫ ቅርጾችን መመርመር እና ማወዳደር፣ በተለያየ መጠኖች እና አቀማመጦች፣ ተመሳሳይነታቸውን፣ ልዩነታቸውን፣ ክፍሎች (ለምሳሌ፣ የጎን እና የመዞሪያዎች / “ማእዘኖች” ቁጥር) እና ሌሎች ባህርያትን (ለምሳሌ፣ እኩል ርዝመት ያላቸው ጎኖች) በመጠቀም መደበኛ ያልሆነ ቋንቋን በመጠቀም መግለጽ።<br>K.G.5. ከእቃዎች ቅርፃ ቅርጾችን በመስራት በአለም ላይ ያሉ ቅርጾችን ሞዴል መስራት (ለምሳሌ፣ ዱላዎች እና የሸክላ ኳሶች) እና ቅርጾችን መሳል።<br>K.G.6. ትላልቅ ቅርጾችን ለመፍጠር ቀላል ቅርጾችን ማገናኘት። ለምሳሌ ፣ “Can you join these two triangles with full sides touching to make a rectangle?” [“አራት ማእዘን ለመስራት እነዚህን ሁለት ባለሶስት ማእዘኖችን በሙሉ ጎኖች ማገናኘት ትችላላቹ?”] |
| 18a. ከላይ፣ ከታች፣ ከፊት፣ ከኋላ ፣ በላይ፣ ከስር የሚሉ አይነት ተገቢኢ ቃላቶችን በመጠቀም የእቃዎችን አንጻራዊ አቀማመጥ ይለያሉ።<br>*ለምሳሌ፣*<br>• በአሻንጉሊት ጋራጅ ስትጫወቱ፣ መኪኖችን በተለያየ ቦታ ያስቀምጧቸው እና እንደዚህ ይበሉ፣ “Park this one next to that one. [“ይህንን መኪና ከዚያኛው አጠገብ ያቁሙ]። Move it over.” [አንቀሳቅሱት። ”]<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• “ሳይመን ያላል” ን ይጫወቱ። መመሪያዎችን ይስጡ (ለምሳሌ ፣ “Put your hand on your head” [“እጃቹን ጭንቅላታቹ ላይ አድርጉት”]) ልጆች አንጻራዊ ቦታዎችን የሚያመለክቱ ቃላትን እንዲሰሙ እና እንዲጠቀሙ ለማስቻል። | K.G.1. የቅርጾችን ስሞች በመጠቀም በአካባቢ ውስጥ ያሉ ነገሮችን ይግለጹ እንዲሁም የእነዚህ እቃዎች አንጻራዊ አቀማመጦችን ከላይ፣ ከታች፣ ከጎን፣ ከፊት፣ ከኋላ እና ቀጥሎ የሚሉ ካላቶችን በመጠቀም ይግለጹ። |

| ሳይንስ እና ኢንጂነሪንግ | ጨቅላ ህጻናቶች | ታዳጊዎች | ሁለት አመት ልጆች |
|---|---|---|---|
| መስፈርቶች | አመላካቾች | አመላካቾች | አመላካቾች |
| 19. ህይወት ያላቸው ነገሮችን መመርመር | 19a. የራስን ሰውነት ይመረምራሉ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• በጀርባቸው በሚተኙበት ጊዜ እግሮቻቸውን ለመንካት ይንጠራራሉ።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• በቤት ውስጥም ሆነ ከቤት ውጭ ልጆች እንዲተኙ፣እግራቸውን እንዲያንቀሳቅሱ እና እጆቻቸውን እንዲያውለበልቡ፣ እንዲንከባለሉ፣ እንዲቀመጡ፣ እንዲድሁ፣ እንዲቆሙ እና እንዲንሸራሸሩ የሚያስችል አስተማማኝ ቦታ ይስጡ።<br>• ከልጆች ጋር በሚነጋገሩበት ጊዜ፣ ልጆች እናንተን እንዲያስመስሉ የተለያዩ የፊት መግለጫዎችን እና ሌሎች የእጅ፣ የክንድ፣ እግር እንቅስቃሴዎችን ያድርጉ።<br><br>19b. በአከባቢው ውስጥ ከሰዎች (እና ሌሎች ህይወት ያላቸው ነገሮች) ጋር ይግባባሉ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ከቤት ውጭ ለመጫወት ምንጣፍ ላይ ሲቀመጡ፣ ወደ ምንጣፉ ጠርዝ ይድሁ እና ሳርዎን ደጋግመው ይነካካሉ።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ከልጆች ጋር ምላሽ በሚሰጡ እና ገንቢ በሆኑ መንገዶች ይግባቡ (ለምሳሌ፣ በአገር ቤት ቋንቋ የሚታወቅ የእሽሩሩ መዝሙር መዘመር፣ ከልጁ ጋር መጽሀፍ ወይም ተወዳጅ መጫወቻን ማጋራት)።<br>• ልጆች እርስ በእርስ እንዲተዋወቁ እድሎችን የሚሰጡ የቤት ውስጥ እና ከቤት ውጭ የመጫወቻ ቦታዎችን ይምረጡ (ለምሳሌ፣ ሁለት ሕፃናት በተመሳሳይ አካባቢ እንዲጫወቱ ማበረታታት) እና ከሌሎች ህይወት ያላቸው ነገሮች ጋር (ለምሳሌ፣ ለመመገቢያ ጊዜ ከቤት ውጭ ምንጣፍ ማዘጋጀት)። | 19a. የእራሳቸውን የሰውነት ክፍሎች ለይቶ ማወቅ ይጀምራሉ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ተንከባካቢው፣ "Where is your nose?" ["አፍንጫህ የት አለ?"] ብሎ ሲጠይቁ አፍንጫቸውን ይነካሉ።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• በጨዋታ እና የእለትተለት ተግባሮች ወቅት ቃላቶችን(በልጆች የአገር ቤት ቋንቋ ተገቢውን ቃል በመጠቀም) እና በምልክቶች የልጆችን የሰውነት ክፍሎችን መጥቀስ (ለምሳሌ፣ "Your hand picked up the grape and put it in your mouth." ["እጅህ ወይኑን አነሳ እና አፍህ ውስጥ ከተተው።"])።<br>• የልጆችን የሰውነት ክፍሎች በይበልጥ ለማስተዋወቅ፣ "ራስ፣ ትከሻ፣ ጉልበት እና ጣት" ወይም ሌላ መዝሙሮችን እና ዜማዎችን ከልጆች ጋር መዘመር።<br><br>19b. የሚታወቁ ሕይወት ያላቸውን ነገሮች ይመለከታሉ እና ይመረምራሉ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ከቤት ውጭ በእግር በሚጓዙበት ጊዜ የቅጠሎች ክምርን ማንቀሳቀስ እና ቅጠሎቹ ሲንሸዋሸዉ ማዳመጥ። አንዳንድ ቅጠሎችን መርገጥ እና ሲሰበሩ መስማት።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• በእለታዊ ከቤት ውጭ ጨዋታ ወይም በጋሪ ወይም በእግር ሽርሽር ወቅት፣ ልጆች በአካባቢው ያሉትን አትክልቶች እና እንስሶችን እንዲያስተውሉ ያድርጉ፣ የአትክልቶችን እና እንስሳቶችን ስም ይጥሩ።<br>• ልጆች የተለያየ አይነት ህይወት ያላቸው ነገሮችን እንዲያዩ ያድርጉ፣ ለምሳሌ በክፍል ውስጥ አትክልት ወይም ደግሞ የቤት ውስጥ እንስሳ በማኖር።<br>• የዕለትተዕለት እንክብካቤ ሥራዎችን ይግለጹ (ለምሳሌ ፣ "I am setting your snack on this tray. ["መክሰሳቹን በዚህ ትሪ ላይ እያቀርብኩ ነው።] You are ready to eat a snack because you are hungry!" [ስለራባቹ መክሰስ ለመብላት ዝግጁ ናቹ!"])።<br>• በመማሪያ ክፍሉ ውስጥ ህይወት ያላቸውን ነገሮች የሚወክሉ መጽሀፎች፣ ምስሎች ወይም ሌሎች እቃዎችን ያካቱ (ለምሳሌ እፅዋትን ፣ እንስሳትን)። | 19a. በሰዎች እና በሌሎች የሚያውቋቸው እንስሳት ውስጥ ያሉትን የሰውነት ክፍሎች መመልከት እና መለየት ይጀምራሉ።<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ይበሉ "Si! ["ሲ!] (አዎ!) " አስተማሪው እንዲህ ብለው ሲጠይቁ፣ "Does that dog have a tail?" [" ያ ውሻ ጅራት አለው? "] እና በስዕል መጽሐፉ ውስጥ የውሻውን ጅራት ሲያመለከቱ።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ሰዎችን እና ሌሎች የሚታወቁ እንስሳትን (ለምሳሌ ወፎችን፣ ድመቶችን፣ ውሾችን) የሚወክሉ ስዕሎች፣ መጽሐፍት ወይም መጫወቻዎች ያስቀምጡ።<br>• በጨዋታ እና በሌሎች እንቅስቃሴዎች ወቅት፣ ለምሳሌ ከልጆች ጋር መጽሐፍትን እንደ ማንበብ ባሉ ተግባራት ወቅት፣ የሰዎችን እና ሌሎች የሚታወቁ እንስሳት የሰውነት ክፍሎችን በቃላት እና ምልክቶች ያመላክቱ።<br><br>19b. የሚታወቁ ህይወት ያላቸው ነገሮች መሰረታዊ ባህርያትን መመርመር እና መለየት ይጀምራሉ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ድንጋዩን ይገልብጡ እና በስሩ ባለው እርጥብ አፈር ውስጥ ያሉትን የመሬት ትሎች ይመልከቱ። "What do you see?" ["ምን ታያላቹ?"] ተብለው ሲጠየቁ፣ ጣቶቻቸውን ያንቀሳቅሳሉ።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• በመማሪያ ክፍል ውስጥ፣ እንስሳትንና እፅዋትን በተፈጥሮ መኖሪያዎቻቸው ውስጥ የሚያሳዩ ስእሎችን ያካቱ።<br>• አነስተኛ የቤት እንስሳ ለማምጣት እና ተማሪዎች እንስሳውን በመንከባከብ እንዲሳተፉ ማድረግን ያስቡበት።<br>• በየእለቱ ከቤት ውጭ በሚጫወቱበት ጊ፣ የአካባቢውን ሁኔታ ማሰስን እና የእንስሳቶች እና የእጽዋቶች ተፍጥሯዊ መኖርያ ገጽታዎችን ማመልከትን፣ ለምሳሌ በዛፍ ላይ ያለ የወፍ ጎጆን በማመልከት ምርምርን ያበረታቱ። |

| ቅድም ትምህርት ቤት | ቅድመ መዋእለ ህጻናት ለመውጫ የሚጠበቁ ነገሮች | መዋእለ ህጻናት የመውጫ ተስፋዎች |
|---|---|---|
| አመላካቾች | አመላካቾች | ቀጣይ ትውልድ የሳይንስ መመዘኛዎች |
| 19a. የሚታወቁ እንስሳት ውጫዊ የሰውነት ክፍልን (ሰዎችን ጨምሮ) እና እጽዋትን ይለያሉ እና ይገጻሉ።<br>*ለምሳሌ፣*<br>• በአትክልት ስፍራ በእግር ስትጓዙ፣ “Birds have wings.” [“ወፎች ክንፎች አላቸው”] ይበሉ። ሌሎች ልጆች ተመልክተው፣ “And feathers!” [“እና ላባዎች!”] ይላሉ።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• የክፍል ውስጥ እጽዋት ወይም ለማዳ እንስሳ ለመንከባከብ የተለያዩ ሚናዎችን እና ለእያንዳንዱ ስራ የምስል ምልክቶች ያለውን የስራ ዝርዝር ማቅረብ።<br>• ወላጆች እንዲያቀርቡ ከሚበረታቱት ናሙናዎች ልጆች እንዲለይዋቸው፣ ህይወት ያላቸው እና ህይወት የሌላቸው የእውነተኛ ህይወት እቃዎችን (ትክክለኛ እቃዎች ወይም ስእል) በክፍል ውስጥ እንዲኖር ማድረግ።<br>• የሰውነት እንቅስቃሴዎችን በመጠቀም የእጽዋትን የሕይወት ዑደት እንዲያሳዩ ልጆችን ያበረታቷቸው።<br><br>19b. ሕይወት ያላቸው ነገሮች ከጊዜ በኋላ እንዴት እንደሚያድጉ እና እንደሚለወጡ ይመለከታሉ እና መግለጽ ይጀምራሉ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• አሁን የዛፉ ቅጠሎች ቀይ እና ቡናማ ስለ ሆኑ፣ ቅጠሎቹ ከዛፉ ላይ እንደሚረግፉ ይግለጹ።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ሁለት የክፍል እጽዋት ያኑሩ፣ ለአንዱ ውሃ እና የጸሀይ ብርሃን ከሰጡ እና ለሌላኛው ግን ካልሰጡ ምን እንደሚፈጠር ልጆችን ይጠይቁ እና ግምታቸውን ይመዝግቡ። በሂደቱ ሙሉ ምልከታዎችን እንዲያደርጉ እርዷቸው። ልጆች ከሁለት ሳምንት በኋላ፣ ውሃ እና የጸሀይ ብርሃን ባገኘው እና ባላገኘው እጽዋት መካከል ያለውን ልዩነት እንዲያስተውሉ ያበረታቷቸው። ልጆች ሁለቱንም እፅዋቶች እንዲያነፃፅሩ እና የትኛው ግምት ትክክል እንደነበረ እና ምክንያቱን እንዲገልጹ ያበረታቷቸው።<br>• አንድ ተክል በሕይወት እንዲኖር የሚያስፈልጉትን ነገሮች በዜማ/በመዝሙር አስተምሯቸው። ጮክ ብሎ ማንበብ።<br>• ቀላል የምስል ሠንጠረዦችን በማስተዋወቅ ልጆች በጊዜ ሂደት የሚኖሩ ለውጦችን እንዲከታተሉ ያሳትፉ። ለምሳሌ፣ ዓመቱን በሙሉ የልጆችን ቁመት ይከታተሉ ወይም የክፍል ውስጥ ተክል የሚያበቅለውን የቅጠል ብዛት መከታተል። | 19a. መግለጫዎችን እና ስዕሎችን በመጠቀም፣ የእንስሳት ውጫዊ የአካል ክፍሎች (ሰዎችን ጨምሮ) እና እፅዋትን ያወዳድራሉ እና የሚታዩ የሰውነት አካሎችን ተግባራት ይገልጻሉ።<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ህይወት ያላቸው ነገሮች የተለያዩ የሰውነት ክፍሎችን በመጠቀም በትክክል እንቆቅልሾችን ይገጣጥማሉ እና ፣ “What part helps them smell things?” [“የትኛው የሰውነት ክፍል ነገሮችን ለማሽተት ይረዳል?”] ተብለው ሲጠየቁ፣ የእያንዳንዱን እንስሳ አፍንጫን ይጠቁማሉ።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• የተለያዩ ህይወት ያላቸው ነገሮች የተለያየ የሰውነት አካሎችን የሚያሳዩ እንቆቅልሾች ወይም ቅርጻቅርጾች እንዲኖር ያድርጉ።<br>• የእንስሳን ውጫዊ የሰውነት አካል ክፍሎችን የቀለም ኮድ ይስጡ እና ልጆች የቀለም ኮዱን ተከትለው ከለር እንዲቀቡ ያበረታቱ።<br>• “ራስ፣ ትከሻዎች፣ ጉለበቶች፣ እና ጣቶች” የሚለውን መዝሙር እና እንቅስቃሴዎቹን ያስተምሩ። የሌሎች ህይወት ያላቸው ነገሮች ተጨማሪ ክፍሎችን ለማካተት መዝሙሩን ይሻሽሉ።<br><br>19b. የተለያዩ ህይወት ያላቸው ነገሮች በጊዜ ሂደት እንዴት እንደሚቀየሩ ለማነፃፀር ምልከታዎችን እና ሌሎች የመረጃ ምንጮች ይጠቀማሉ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ለሌሎች ልጆች ከቤት የህጻን ፎቶዎችን ያሳዩ እና እንዲህ ይበሉ፣ “I couldn’t walk or talk but now I can.” [“እኔ መራመድ ወይም ማውራት አልችልም ነበር አሁን ግን እችላለሁ።”]<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• የተለያዩ እፅዋትንና እንስሳትን የሕይወት ዑደት የሚገልፅ ታሪኮችን ያንብቡ እና ምስሎችን ያጋሩ።<br>• ዘሮችን ይተክሉ እና ልጆች እንዲመለከቱ እና የእፅዋቱን እድገት እንዲስሉ ያበረታቱ።<br>• በተለያዩ ህይወት ባላቸው ነገሮች በጊዜ ሂደት ያላቸውን ተመሳሳይነት እና ልዩነቶች ልጆች እንዲመለከቱ ያበረታቱ።<br>• የክፍል ውስጥ ለማዳ እንስሳን ልጆች እንዲንከባከቡ እና የህይወት ኡደቱን እንዲመልከቱ ያበረታቱ። ልጆች በጊዜ ሂደት የሚፈጠሩ ለውጦችን ሊስሉ ይችላሉ። | K-LS1-1 እፅዋቶች እና እንስሳት (ሰዎችን ጨምሮ) ለመኖር ምን እንደሚያስፈልጋቸው ለመግለጽ ምልከታዎችን መጠቀም። |

| ሳይንስ እና ኢንጂነሪንግ | ጨቅላ ህጻናቶች | ታዳጊዎች | ሁለት አመት ልጆች |
| --- | --- | --- | --- |
| መስፈርቶች | አመላካቾች | አመላካቾች | አመላካቾች |
| 19. ህይወት ያላቸው ነገሮችን መመርመር<br><br>(ቀጣይ) | 19c. ስለአለም ለመማር ስሜታዊ መረጃን ይጠቀማሉ<br><br>*ለምሳሌ፣*<br><br>• ጡጦ በቀስታ ጉንጫቸውን ሲዳስስ አፋቸውን ይከፍታሉ።<br><br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br><br>• ልጆች የሚመረምሯቸው የተለያዩ አይነት መጫወቻዎችን ማቅረብ (ለምሳሌ፣ የተለያየ ይዘት ያላቸው መጽሀፎች፣ ድምጽ የሚያሰሙ ቅጭልጭሎች)<br><br>• ልጆች ምን እንደሚመለከቱ ፣ እንደሚሰሙ እና እንደሚያደርጉ ይግለጹ (ለምሳሌ፣ “You are holding the brown Teddy bear. [“አንተ ቡናማውን ቴዲ ቢር ይዘሃል።] It feels so soft!” [በጣም ለስላሳ ነው! ”])። | 19c. አምስቱን የስሜት ሕዋሳት በመጠቀም በዙሪያቸው ያለውን ዓለም ይመለከታሉ እና ይመረምራሉ<br><br>*ለምሳሌ፣*<br><br>• ድምጽ የሚያወጣ መሆኑን ለማወቅ አዲስ መጫወቻን መነቅነቅ።<br><br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br><br>• ልጆች እንዲመረምሯቸው የተለያየ አይነት መጫወቻዎችን ማቅረብ (ለምሳሌ፣ የተለያየ ገጾች ያላቸው መጽሀፍ፣ ድምጽ የሚያወጡ ሳጥኖች)<br><br>• ልጆች ምን እንደሚያዩ ፣ እንደሚሰሙ እና እንደሚያደርጉ ይግለጹ (ለምሳሌ፣ “You are crawling toward the speaker. [“አንተ ወደሚናገረው ሰው እየተሳብክ ነው።] You like to hear the deep voice singing.” [ጥልቅ ድምፅ ያለውን ዝማሬ መስማት ትወዳለህ።”])። | 19c. በዙሪያቸው ስላለው ዓለም ለመማር የስሜት ህዋሶቻቸውን እንዴት እንደሚጠቀሙ መመርመር እና መለየት ይጀምራሉ።<br><br>*ለምሳሌ፣*<br><br>• አዲስ ምግብ እንዲቀምሱ ሲሰጣቸው በአፍንጫቸው በጥልቀት ይተነፍሳሉ። ተንከባካቢው“Does it smell good?” [ “ጥሩ ሽታ አለው?”[ በማለት ሲጠይቁ፣ “Smell good!” [“ጥሩ ይሸታል!”] ብሎ ምላሽ መስጠት።<br><br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br><br>• አምስቱን የስሜት ሕዋሳት በመጠቀም ምርመራን ያበረታቱ (ለምሳሌ፣ የተለያዩ ቀለሞች እና ይዘቶች እና ድምጽ ያላቸው የተለያዩ አይነቶች መጫወቻዎችን ማቅረብ)።<br><br>• ወቅታዊ ነገርን ሲጠቀ፣ የስሜት ህዋሳቶቻቸውን በመጠቀም ልጆች ሊመርምሯቸው የሚችሉ እቃዎችን ይሰብስቡ፣ እንደ የዛፍ ፍሬዎች፣ ደረቅ እና የሚንሸዋሸው ቅጠሎች እና እርጥብ ሽታ ያላቸው ቅጠሎች። |



| ቅድም ትምህርት ቤት | ቅድመ መዋእለ ህጻናት ለመውጫ የሚጠበቁ ነገሮች | መዋእለ ህጻናት የመውጫ ተስፋዎች |
|---|---|---|
| አመላካቾች | አመላካቾች | ቀጣይ ትውልድ የሳይንስ መመዘኛዎች |
| 19c. የሚታወቁ እጽዋት እና እንስሳት (ሰዎችን ጨምሮ) መሰረታዊ ፍላጎቶችን ይለያሉ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• የመማሪያ ክፍል ውስጥ ያለን ተክል አስተማሪ ውሃ ሲያጠጣ ተመልክተው፣ "I want water, too. ["እኔም ውሃ እፈልጋለሁ።] I'm thirsty!" [ጠምቶኛል!"] ይላሉ።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• የልጆች እና በክፍል ውስጥ ያሉ ማንኛወም ተክሎች ወይም እንስሳዎች የእንክብካቤ መደበኛ ተግባሮችን ይግለጹ። መደበኛ ተግባሮቹን ደረጃዎቹን በስእሎች ያሳዩ።<br><br>19d. በዙሪያቸው ስላለው ዓለም መረጃን ለመሰብሰብ እንስሳት (ሰዎችን ጨምሮ) የግል ስሜቶቻቸውን እንዴት እንደሚጠቀሙ መለየት ይጀምራሉ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• በመጽሐፉ ገጽ ላይ ወዳለው የውሻ አፍንጫ ያመልከቱ እና፣ "This dog smells food!" ["ይህ ውሻ ምግብ ያሸታል!"] በማለት ይግለጹ።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ልጆች እና ሌሎች (ለምሳሌ፣ በማስመሰል ጨዋታ ጊዜ እንስሳትን የሚወክሉ፣ በመጽሐፎች ውስጥ ያሉ ገጸባህሪዎች) ምን እንደሚያዩ፣ እንደሚሰሙ ወይም እንደሚያደርጉ ይግለጹ እና እነዚያ ስሜታዊ ገጠመኞቹን እነዚያን ስሜታዊ መረጃ ከሚሰበስቡ ውጫዊ የሰውነት አካሎች ጋር ያገናኙ።<br>• ልጆች እንስሳዎችን እና ሰዎችን እንዲስሉ ይርዷቸው፣ ለስሜት ሃላፊነት ያላባቸውን የሰነት አካሎች እንደ አይኖች፣ አፍንጫዎች፣ ጆሮዎች፣ ወዘተ ላይ ትኩረት በመስጠት።<br>• እንስሳት ምግብን ለማግኘት ወይም ለመግባባት ድምጽ እና/ወይም ጠረን እንዴት እንደሚጠቀሙ የሚገልጹ መጽሀፎችን ይመርምሩ።<br><br>19e. የሚታወቁ እፅዋትና እንስሳት መሰረታዊ ፍላጎቶችን ያውቃል (ሰዎችን ጨምሮ)<br>*ለምሳሌ፣*<br>• የእንስሳትን ስዕሎች፣ የትኞቹ እንስሶች በውሃ ላይ እንደሚኖሩ፣ የትኞቹ መሬት ላይ እና የትኞቹ እንስሶች በሁለቱም ቦታዎች እንደሚኖሩ በመለየት በቡድን ይለዩ።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• እንስሳትን እና መኖሪያዎቻቸውን የሚወክሉ መጽሐፍት እና መጫወቻዎች ይኑሮት።<br>• ብሔራዊ የእንስሳት መኖርያን (ዞ) ሲመረምሩ፣ የእንስሳትን ልምዶች ልዩነት እንዲያስተውሉ እንዲህ ብለው ይጠይቁ ፣ "Is it hotter in here? ["እዚህ የበለጠ ሙቀት አለ?] Look at all this water where this frog lives. [ይህ እንቁራሪት የሚኖርበት ውሃ ሁሉ ብዛት ተመልከቱ።] Where do you think it sleeps?" [የት ይተኛል ብለቹ ታስባላቹ ? "]<br>• የአካባቢያቸውን የእንስሳት መጠለያ ወይም የክፍል ጓደኛን፣ እንስሳ እንዲያመጡ እና እነሱን እንዴት እንደሚንከባከቡ እንዲያወሩ ይጋብዙ።<br><br>19f. በሚታወቁ አትክልቶች እና እንስሳዎች፣ ሰዎችን ጨምሮ ያለውን መመሳሳል እና ልዩነቶች መመልከት እና መግለጽ ይጀምራሉ።<br>*ለምሳሌ፣*<br>• "Tigers have stripes. ["ነብሮች መስመሮች አላቸው።] Lions are just brown." [አንበሶች ቡናማ ብቻ ናቸው ።"] ይበሉ መጽሀፍ ሲገልጡ።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• የአንበሳ ግልገሎችን እና የአዋቂ አንበሶችን የሚያካትቱ፣ ትንሽ እና ትልቅ አትክልቶች እና እንስሶች ባንድ ላይ የሚያሳዩ ምስሎችን እና መጫወቻዎችን ያቅርቡ።<br>• በክፍል ውስጥ የልጆችን ቤተሰቦች ፎቶግራፎችን ያካቱ እና ፎቶው ላይ ያሉ የቤተሰብ አባሎች ስም ይጥሩ እና ይግለጹ። | 19c. የሚታወቁ እፅዋትንና እንስሳትን (ሰዎችን ጨምሮ) ይመለከታሉ እና ለመኖር ምን እንደሚያስፈልጋቸው ይገልጻሉ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• በአትክልት ቦታ ሲንሸራሸሩ መንገድ ላይ ያለ ትል ያንሱ እና ወደ ሳሩ ያስቀምጡት እና እንዲይ ይበሉ፣ "The worm needs plants to eat and dirt to live in." ["ትሉ ለመኖር የሚበላው ተክል እና የሚኖርበት አፈር ያስፈልገዋል።" ]<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• ዘሮችን ለመትከል፣ እፅዋትን ለመንከባከብ እና እፅዋቱ ለመኖር እና ለማደግ ስለሚያስፈልጋቸው ነገር ለማውራት እድሎችን ያቅርቡ።<br><br>19d. እንስሳት (ሰዎችን ጨምሮ) በዙሪያቸው ስላለው ዓለም መረጃን ለመሰብሰብ አምስቱን የስሜት ህዋሳታቸውን እንዴት እንደሚጠቀሙ በመረጃ ላይ የተመሰረተ ማብራርያ ለመስጠት ምልከታዎችን ማድረግ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ሳያዩ በሳጥኑ ውስጥ ያለውን ነገር ለመለየት እጃቸውን መጠቀም እና እንዲህ ማለት፣ "I can feel that it's a toy car because it has four wheels." [" አራት ጎማዎች ስላሉት የመጫወቻ መኪና መሆኑን መዳሰስ ችያለሁ።"]<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ልጆች የማየት፣ የመስማት፣ የመንካት እና የማሽተት ስሜቶችን በመጠቀም ስሜቶችን እንዲመረምሩ የተለያየ አይነት የስሜት እቃዎችን ያቅርቡላቸው።<br>• የክፍል ተጋባዥ እንግዳ የማየት ወይም የመስማት የአካል ጉድለትን እና ስለሚያስፈልጉት ድጋፎች እንዲያወሩ ይጋብዙ። ልጆች የድምፅ ቋንቋን ወይም ብሬይልን ይመረምራሉ።<br><br>19e. መሰረታዊ የሆኑ ፍላጎቶቻቸውን ለማሟላት እንስሳት እና እፅዋት እርስ በእርስ እንዴት ጥገኛ እንደሆኑ ለማሳየት ከአካባቢው ምሳሌዎችን ያቅርቡ።<br>*ለምሳሌ፣*<br>• እንዲህ ይበሉ፣ "The squirrel buries acorns from the tree for food but sometimes the acorn grows into a tree." ["ሽኮኮዎ ለምግብ ከዛፉ ላይ ያሉትን ፍሬዎች ይቀብራል ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ ፍሬዎቹ ወደ ዛፍ ያድጋሉ።"]<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ተማሪዎች ከመማሪያ ክፍል ውጭ ወይም ከቤተሰቦቻቸው ጋር በእግር ሲጓዙ ምልከታዎችን እንዲያደርጉ ያበረታቱ።<br>• በአካባቢው ያሉ እጽዋቶችን ወይም እንስሶችን ለመግለጽ የአገር ቤት ቋንቋን እንዲጠቀሙ ያበረታቱ።<br><br>19f. ትናንሽ እጽዋቶች እና እንስሶች እንደወላጆቻቸው መሆናቸውን ነገር ግን አንድ አይነት አለመሆናቸውን ለመግለጽ ምልከታዎችን ይጠቀማሉ።<br>*ለምሳሌ፣*<br>• የሕፃን እንስሳትን ስዕሎች ከወላጅ እንስሳ ሥዕሎች ጋር ያዛምዱ።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ልጆች የአካባቢውን ሙዚየም፣ የእንስሳ መኖርያ (ዞ) ወይም የእጽዋት ስፍራዎችን እንዲጎበኙ በማድረግ የተለያዩ አይነቶች እጽዋቶች እና እንስሶችን እንዲመለከቱ እድሎችን ያቅርቡ። | |

| ሳይንስ እና ኢንጂነሪንግ | ጨቅላ ህጻናቶች | ታዳጊዎች | ሁለት አመት ልጆች |
|---|---|---|---|
| መስፈርቶች | አመላካቾች | አመላካቾች | አመላካቾች |
| 20. አካላዊ እቃዎችን መመርመር | 20a. በአከባቢው ውስጥ ባሉ እቃዎች ይግባባል<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ከረጅም ወንበር ላይ የፕላስቲክ ሳህን ይጥሉ እና መሬት ላይ ሲንጫጫ ይሰማሉ።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ሕፃናት ሊያንቀሳቅሷቸው ወይም ሊነቀንቋቸው የሚችሉ የተለያዩ አይነቶች የሚሰቡ እቃዎችን ያቅርቡ (ለምሳሌ፣ ቅጭልጭሎች፣ ከፍ ባለ ወንበር ላይ ሊመቷቸው የሚችሉ ማንኪያዎች፣ ወዘተ)። በዕለትተዕለት መደበኛ ተግባሮች ላይ እቃዎችን ይግለጹ፣ እንደ፣ “You like the sound your rattle makes!” [“ቅጭልጭላቹ የሚያወጣውን ድምጽ ትወዳለህ!”]<br>• በዕለትተዕለት መደበኛ ተግባሮች ላይ ድምጾችን ይወያዩ፣ እንደ የበር ደወል ሲደውል፣ “The doorbell rang! [“የበሩ ደወል ተደወለ!] This means someone is at the door. [ይህ ማለት አንድ ሰው በር ላይ ነው ማለት ነው።] Who could it be?” [ማን ሊሆን ይችላል? ”]<br>• እንደ ቅጭልጭሎች እና ከበሮዎች አይነቶች ድምጽ የሚያወጡ መጫወቻዎችን ያቅርቡ እና ልጆች በነዚያ ድምጽ እንዲሰሩ አግዟቸው። ህጻናቶች ድምጽ ለመፍጠር እቃዎችን ሲነካኩ አስተያየቶችን በመስጠት በንቃት ምላሽ ይስጡ (ለምሳሌ፣ ቅጭልጭሉ የሚያወጣውን ድምጽ በመድገም እና እንዲህ በማለት፣ “What a noisy rattle!” [“ምን አይነት ረባሽ ቅጭልጭል ነው!”]<br>• ጨቅላ ሕፃናትን ለማሳተፍ የጥላ ጨዋታ ይጠቀሙ። | 20a. የተለያዩ ጠጣሮች እና ፈሳሾችን ጨምሮ፣ ዕቃዎችን ይመለከታሉ እና ይመረምራሉ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• እንደ ዶቃዎች ፣ ባለቀለም ውሃ ፣ አሸዋ ፣ የወይራ ዘይት ፣ የእቃ ማጠቢያ ሳሙና ፣ ወዘተ የተሞሉ ጠርሙሶችን ይያዙ እና ይነቅንቁ።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• በእንግሊዝኛ እና በሌሎች የአገር ቤት ቋንቋዎች ገላጭ ቃላትን በመጠቀም (ለምሳሌ ፣ ከባድ ፣ ቀላል ፣ ወፍራም ፣ ቀጭን ፣ ቀጫጫ) ለተለያዩ እቃዎች ባህርዩች ትኩርትን ይሳቡ።<br>20b. እቃዎች እንዲንቀሳቀሱ ለማድረግ የታቀዱ ድርጊቶችን ያደርጋሉ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• የመጫወቻ መኪና፣ ባቡር ወይም ኳስ ወለሉ ጋር ይግፉት፣ ሲንቀሳቀስ ይመልከቱ።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• በመዳሰስ ላይ ያተኮረ ጨዋታን ማቅረብ (ለምሳሌ፣ የጂኦሜትሪክ መጫወቻዎች፣ አራት ማእዘኖች/ኳሶች፣ የፎም ቅርጾች)።<br>• የሚንቀሳቀሱ እቃዎችን ይስጡ እንደ የእንጨት መኪኖች፣ የተለያዩ መጠን ያላቸው ኳሶች፣ ወዘተ። ስለልጆች ምርምር ያብራሩ እና ጥያቄዎችን ይጠይቁ (ለምሳሌ፣ “That ball rolled so far away! [“ያ ኳስ በጣም በርቀት ተሽከረከረ!] Here is a smaller ball. [እዚህ ትንሽ ኳስ አለ።] Where will this ball go?”). [ይህ ኳስ የት ይሄዳል?።] | 20a. የፈሳሾች እና የጠጣሮችን መሰረታዊ ባህሪያትን ይመለከታሉ እና መለየት ይጀምራሉ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• በውሃ ጠረጴዛው ላይ በጀክ፣መቆንጠጫዎች እና ስፖንጆች መጫወት። እርጥብ ስፖንጅ ይጭመቁ እና በደስታ፣ “Water!” [“ውሃ!”] ይበሉ።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• የጠረጴዛ ጨዋታን ለማሳለጥ፣ የተለያየ አይነት ጠጣር እቃዎችን፣ የሚንሳፈፉ እና የሚስምጡ ጨምሮ ማቅረብ።<br>• ውጪ በአሸዋ ጠረጴዛ ላይ ልጆች ድብልቆችን እንዲሰሩ ያስትፏቸው (ለምሳሌ፣ ድንጋዮችን ፣ ዱላዎችን ፣ ቅጠሎችን እና ሣሮችን በጎድጓዳ ሳህን ወይም ማሰሮ ላይ መደባለቅ)፣ በድብልቁ ውስጥ ስላሉት የተለያዩ ነገሮች ቅርጽ፣ይዘት እና መጠን፣ ጥያቄዎችን በመጠየቅ እና አስተያየቶችን በመስጥት ትኩረትን በመስጠት (ለምሳሌ፣ “What a round, smooth acorn!” [“ምን አይነት ክብ፣ ለስላሳ ዘንግ ነው!”])።<br>20b. ዕቃዎችን እንዲያንቀሳቅሱ የሚያደርጉዋቸው ሙከራዎች እና የእርምጃዎች ውጤቶችን ይጠብቃሉ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ኳሱ ትንሽ ርቀት ላይ ያለ ሳጥን ውስጥ እንዲገባ በሃይል ይግፉር እና ሲገባ በደስታ ይስቃሉ።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• መንቀሳቀስ የሚችሉ እና መንቀሳቀስ የማይችሉ እቃዎችን ጨምሮ፣ በክፍል ውስጥ የተልያዩ እቃዎችን አይነት ያቅርቡ (ለምሳሌ፣ የሚሽከረከሩ ክብ ጡቦች እና የማይሽከረከሩ ስኩዌር ጡቦች)።<br>• የዕለት ተዕለት እቃዎች እንዴት እንደሚንቀሳቀሱ ለመመርመር ምናባዊ ጨዋታ ይጠቀሙ። የልጆችን ሙከራ በማሳየት፣ ጥያቄዎችን በመጠየቅ እና ትንበያዎችን በመስጠት ያግዙ። |



| ቅድም ትምህርት ቤት | ቅድመ መዋእለ ህጻናት ለመውጫ የሚጠበቁ ነገሮች | መዋእለ ህጻናት የመውጫ ተስፋዎች |
|---|---|---|
| አመላካቾች | አመላካቾች | ቀጣይ ትውልድ የሳይንስ መመዘኛዎች |
| 20a. በልጆች ዕለታዊ አከባቢ ውስጥ የሚገኙትን የፈሳሾች እና የጠጣሮችን ባህሪዎች ይመረምራሉ፣ ያብራራሉ እና ያነፃፅራሉ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ከእንጨት የተሠራ ጡብ እና ከካርቶን የተሰራት ጡብ ያምጡ። የበለጠ ከባድ የትኛው እንደሆነ ሲጠየቁ ከእንጨት የተሰራውን ጡብ ይስጡ።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• በጨዋታ እና የምግብ ሰዓቶች ልጆች ከእለትተለት ፈሳሾች እና ጠጣሮች ጋር ያላቸውን ግንኙነቶች ያስተባብሩ። ጥያቄዎችን በመጠየቅ እና ልጆች ንብረታቸውን እንዲያነፃፁ በመጋበዝ ልጆች ስለ ፈሳሾች እና ጠጣሮች ያላቸውን አስተሳሰብ ይደግፉ (ለምሳሌ ፣ “Which container will hold more water?” [“የትኛው የውሃ መያዣ የበለጠ ውሃ ይይዛል?”])<br>• የውሃ ሰንጠረዥ ጨዋታን ለማስተባበር የተለያዩ አይነቶች የውሃ መያዣዎችን ማቅረብ እና መጠናቸውን እና አቅማቸውን ለማወዳደር መጠቀም።<br><br>20b. እቃዎች ሊንቀሳቀሱ የሚችሉባቸውን የተለያዩ መንገዶች ይመረምራሉ እና ይገልጻሉ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• በጡቦች መወጣጫ ስር ትንሽ ኳስ ማንከባለል። ኳሱን ከዚህ በፊት ከነበረው በተሻለ ሁኔታ እንዲሽከረከር ከፍ ያለ መወጣጫ መገንባት።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• እንደ የሚሽከረከሩ መጫወቻዎች እና ኳሶች ያሉ ሊንቀሳቀሱ የሚችሉ የተለያዩ እቃዎችን በክፍል ውስጥ ያቅርቡ።<br>• ልጆች በእቃዎች በሚጫወቱበት ጊዜ እቃዎች ምን ያህል ርቀት ወይም በምን ያህል ፍጥነት እንደሚንቀሳቀሱ ጥያቄዎችን ይጠይቁ (ለምሳሌ ፣ “This ramp is so much higher than before. [“ይህ መወጣጫ ከመጀመርያው በጣም ከፍ ያለ ነው።] What do you think will happen when you put the ball on it?” [ኳሱን በላዩ ላይ ሲያደርጉ ምን ይከሰታል ብላቹ ታስባላቹ?”])። | 20a. በፈሳሾች እና በጠጣሮች መካከል ያለው ልዩነት ይመረምራሉ እና ስለልዩነቶች ዳታ ይሰበስባሉ እና አንድ ፈሳሽ ጠጣር እንዲሆን እንዲሁም ጠጣሩ ፈሳሽ እንዲሆን የሚያደርገውን ነገር አስመልክቶ ጥያቄዎችን ይጠይቃሉ።<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ከምግብ በኋላ በኩባያቸው ላይ የተረፈውን በረዶ በክፍሉ መስኮት ጠርዝ ላይ እንዲያስቀምጡት መጠየቅ እና፣ አፈሩ ሞቃታማ ስለሆነ በረዶው ቀልጦ አትክልቶቹን እንደሚያጠጣ ይግለጹላቸው።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• በየእለቱ ከፈሳሾች እና ከጠጣሮች ጋር ያሉትን አጋጣሚዎችን አስመልክቶ ምርምራዎችን ያድርጉ (ለምሳሌ ፣ “Does the snow in a shady area of the playground or in direct sunlight melt first?” [“በመጫወቻ ስፍራው ጥላ ላይ ያለው ነው ወይስ በቀጥታ የጸሀይ ብርሃን የሚያገኘው በረዶ ነው መጀመርያ የሚቀልጠው?”]) ።<br>• የልጆችን ምልከታ ለመመዝገብ፣ እንደ ግራፎች እና የድር አደራጆች፣ ያሉ ምስሎችን ይጠቀሙ። ልጆች የራሳቸውን ምልከታ እንዲመዘግቡ ያበረታቷቸው (ለምሳሌ ፣ በመሳል)።<br>• ልጆች ስለፈሳሾች እና ጠጣሮች ግምቶቻቸውን እንዲናገሩ እድል ይስጡ እና በቀዝቃዛ ሁኔታዎች በረዶ የሚሆኑ/ጠጣር የሚሆኑ መሆኑን ወይም በሞቃታማ ሁኔታዎች የሚቀልጡ/ፈሳሽ ይሆኑ እንደሆነ ግምቶቻቸውን እንዲናገሩ እድል ይስጧቸው።<br><br>20b. አንድ እቃ እንቅስቃሴውን እንዲለውጥ የሚያደርግ መሣሪያ ለመቅረጽ መሣሪያዎችን እና ቁሳቁሶችን ይጠቀማሉ (ለምሳሌ፣ በፍጥነት እንዲንቀሳቀሱ፣ ቀስ ብለው እንዲንቀሳቀሱ፣ ርቀው እንዲንቀሳቀሱ፣ አቅጣጫውን ይቀይሩ)<br>*ለምሳሌ፣*<br>• በሚሽከረከር መኪና መንገድ ላይ አንድ ባዶ የፕላስቲክ ጡብ በማስቀመጥ ለማስቆም መሞከር። መኪናውን ጡቡን ሲገፋ ነገር ግን ሳይቆም ከተመለከቱ በኋላ ፣ ባዶ ጡቡን በሶስት ከባድ ባለእንጨት ጡቦች ይተኩ እና መኪናውን ያቁሙ።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• በጨዋታ ጊዜ ልጆች የመኪናዎች ፣ የድንጋዮች ወይም የሌሎች እቃዎችን እንቅስቃሴ ለመገደብ እንዲመራመሩ ያበረታቱ።<br>• አንድ ትንሽ ሮቦት በመጠቀም ልጆች በትንሽ ቡድን በመሆን እንቆቅልሾች እንዲፈጥሩ እና እንዲፈቱ ያሳትፏቸው።<br>• የእቃዎችን እንቅስቃሴ ላይ ተጽእኖ የሚፈጥሩ ነገሮችን፣ እንደ ለስላሳ ወይም ሻካራ ቦታዎች ወይም መወጣጫዎች፣ ለመመርመር እንቅስቃሴዎችን ማቀድ። | K-PS2-1 የተለያዩ ጥንካሬዎች ወይም የተለያዩ የግፊት እና የስበት አቅጣጫዎች በአንድ እቃ እንቅስቃሴ ላይ ያለውን ተጽእኖዎች ለመመርመር እና ለማወዳደር ማቀድ።<br><br>K-PS2-2 የታቀደው መፍትሄ የአንድን እቃ ፍጥነት ወይም አቅጣጫ በመግፋት ወይም በመጎተት ሊቀየር እንደሚችል ለመወሰን ዳታ መተንተን።<br><br>K-PS3-1 የፀሐይ ብርሃን በምድር ገጽታ ላይ ያለውን ውጤት ለማወቅ ምልከታ ያድርጉ።<br><br>K-PS3-2 በአካባቢያ ላይ ያለውን የጸሀይ የሙቀት መጠን ለመቀነስ የሚያስችለውን መዋቅር ለመንደፍ እና ለመገንባት መሳሪያዎችን እና ቁሳቁሶችን ይጠቀሙ። |

| ሳይንስ እና ኢንጂነሪንግ | ጨቅላ ህጻናቶች | ታዳጊዎች | ሁለት አመት ልጆች |
|---|---|---|---|
| መስፈርቶች | አመላካቾች | አመላካቾች | አመላካቾች |
| 20. አካላዊ እቃዎችን መመርመር<br>(ቀጣይ) |  | 20c. የተለያዩ ድምጾችን ጨምሮ፣ ዕቃዎችን ይመለከታሉ እና ይመረምራሉ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• የተለያዩ ድምጾችን ለመስራት የተለያዩ እቃዎችን (ለምሳሌ፣ ቅጭልጭሎችን፣ ማራካስ፣ የተሞሉ ጠርሙሶች) ይነቅንቁ።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• በሙዚቃ እንቅስቃሴዎች ወቅት የተለያዩ መሳሪያዎችን ይጠቀሙ።<br>• በእቃዎች ስለሚፈጥሯቸው ድምጾች ከልጆች ጋር ያዉሩ (ለምሳሌ፣ እንዲህ ይበሉ “Tapping hard on that drum makes such a loud sound! [“ከበሮውን በሃይል መምታት ጮክ ያለ ድምጽ ይፈጥራል!] What if you tap lightly?” [ቀስ ብላቹ ብትመቱጽ?”] ድምጻቹን ጮክ ካለ ወደ ቀስ ወዳለ ድምጽ እየቀይራቹ)።<br>20d. የብርሃን ምንጮችን ጨምሮ፣ ዕቃዎችን ይመለከታሉ እና ይመረምራሉ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• በመጫወቻ ላይ ያለውን ቁልፎች በመጫን መብራት እንዲበራ እና እንዲጠፋ ማድረግ።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ብርሃንን የሚያካትቱ ዕለታዊ ተግባሮችን ይግለጹ (ለምሳሌ፣ “It’s sunny outside. [“ውጭ ፀሀያማ ነው።] Let’s makes sure we put on our hats” [ኮፍያዎቻችንን ማድረጋችንን እናረጋግጥ”]፣ “It is dark in here. [“እዚህ ጨለማ ነው።] We should turn on the light with this switch.” [በዚህ ማብሪያና ማጥፍያ መብራቱን ማብራት አለብን።”])።<br>• በጥላ ጨዋታ ጊዜ በእጃቹ የተለያዩ እንስሶችን በመስራት ልጆች እንዲሳተፉ ያድርጉ። | 20c. የድምፅን ባህሪዎች መመልከት እና መለየት ይጀምራሉ (ለምሳሌ፣ የድምጽ፣ ቅላጼ)<br>*ለምሳሌ፣*<br>• በምናባዊ ጨዋታ ጊዜ የተለያዩ የድምጽ መጠን እና ቅላጼ ያላቸውን ድምጾች ይጠቀማሉ (ለምሳሌ፣ ለሳይረን ጮክ ያለ ድምጽ እና ለእሽሩሩ ቀስ ለስለስ ያለ ድምጽ)።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• በሙዚቃ እና የጨዋታ ጊዜያት የድምጽ ጨዋታን ይድግፉ ይህም የተለያየ የድምጽ መጠን እና ቅላጼ ያላቸውን ያካትታል። ተገቢ የሆኑ ቃላቶችን በመጠቀም ስለ ድምጾች መወያየት (ለምሳሌ፣ የሚጮህ፣ ለስላሳ)።<br>• መዝሙሮችን መዘመር እና መዝሙሮችን ከእንቅስቃሴ ጋር ማዛመድ (ለምሳሌ፣ “The wheels on the bus . . .” [“ዘ ዊልስ ኦን ዘ ባስ...”] ወይም “We’re going on a Bear Hunt” [“ዊ አር ጎይንግ ኦን ኤ ቢር ሀንት”] የሚሉትን እየዘመራቹ መንቀሳቀስ)።<br>20d. የብርሃን ባህርያቶችን መመርምር<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ብርሃን ባለው ጠረጴዛ መጫወት፣ የተወሰኑ እቃዎች ሲበሩ እና ሌሎች እቃዎች ደግሞ ብርሃኑን ሲከልሉት ማስተዋል።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ብርሃን የሚቀይሩ ወይም የሚያንጸባርቁ መሃል ላይ ያሉ እቃዎችን ማስተዋወቅ (ለምሳሌ፣ ለህጻናት ደህነነት አስተማማኝ የሆኑ መስታወቶች፣ ፕሪዝም፣ ግልጽ ቀለም ያላቸው ጡቦች)።<br>• ልጆች ብርሃን ባለው ጠረጴዛ ላይ ባሉ ወይም ሪሳይክል በደረጉ እቃዎች ቅርጾች፣ ፊደሎች እና ቁጥሮችን እንዲፈጥሩ ማበራታታት (ለምሳሌ፣ በአንጸባራቂ እና ወይ በጠጣር እቃዎች)።<br>• የጥላ ጨዋታን በመጠቀም ጥላውን እንዴት ማተለቅ ወይም ማሳነስ እንደሚቻል ማሳየት። |

| ቅድም ትምህርት ቤት | ቅድመ መዋእለ ህጻናት ለመውጫ የሚጠበቁ ነገሮች | መዋእለ ህጻናት የመውጫ ተስፋዎች |
|---|---|---|
| አመላካቾች | አመላካቾች | ቀጣይ ትውልድ የሳይንስ መመዘኛዎች |
| 20c. በተለያዩ እቃዎች የተሰሩ ድምጾች መመርመር እና ድምጾችን የሚፈጥረው ምን እንደሆነ የሚቀርበው ማብራርያ ላይ መሳተፍ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ድምጾችን የሚፈጥሩ የተለያዩ እቃዎችን ለልጆች መስጠት እና ከእቃዎቹ ጋር የሚያደርጉት ግንኙነት ድምጾችን እንዴት እንደሚፈጥር መወያየት (ለምሳሌ፣ የሚቅጨለጨል ነገር ወይም ድራም በተለያዩ እቃዎች መፍጠር)።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ተማሪዎች በድምጾች እና እንቅስቃሴዎች መካከል ዝምድና እንዲፈጥሩ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።<br>• ልጆች ድምጾችን የሚፈጥሩት ምን እንደሆኑ የሚሰጡትን ማብራርያዎችን ሪከርድ ለማድረግ የምስሎች/ሀሳብ ድሮችን መጠቀም።<br><br>20d. በብርሃን መቀየር ምክንያት በጥላዎች ላይ የሚፈጠሩ ለውጦችን ምልከታ ማድረግ።<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ከታሪኩ ጋር የሚሄድ የቡችላ ጥላ መፍጠር እና የቡችላው ጥላ እንዲያንስ ወይም እንዲተልቅ የእጅ ባርትሪውን ያንቀሳቅሱ።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ጥላዎችን፣ የሚፈጥሩትን ቅርጾች እና መጠኖችን አስመልክቶ ምርምር ለማድረግ እና ምልከታዎችን ሪከርድ ለማድረግ እድሎችን መፍጠር።<br>• በመስኮት የሚገባ የብርሃን ጨረሮችን መመልከት እና መመዝገብ (ለምሳሌ፣ በቀን ውስጥ በተለያየ ጊዜ በመስኮት የሚገባውን ብርሃን መከታተል)። | 20c. በጨዋታ እና ምርምሮች፣ የድምጽን መጠን እና የድምጽ ቃና የሚቀይሩ የተለያዩ እቃዎችን የሚያንቀሳቅሱበት መንገዶችን ይለያሉ።<br>*ለምሳሌ፣*<br>• በጫማ ሳጥን እና የላስቲክ ማሰሪያዎች የመጫወቻ ጊታር መስራት። አስተማሪው “How will you make music?” [“ሙዚቃ እንዴት ትሰራላቹ?”] ብለው ሲጠይቁ፣ “Pull the string.” [“ገመዱን መነተት”] በማለት ምላሽ መስጠት። አስተማሪው እንዲህ በማለት ያክላል፣ “Yes, pulling the string to make it move will make a sound. [“አዎ፣ ገመዱ እንዲንቀሳቀስ መነተት ድምጽ ይፈጥራል።] The farther back you pull the rubber band, the louder the sound will be!” [የላስቲኩን ገመድ በጣም በሳባቹት መጠን፣ ድምጹ በጣም ይጮሃል!”]<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• እንደ ኢንሱሌተሮች አይነት ሀሳቦችን የሚያስተዋውቁ ተግባሮችን ያቅዱ (ለምሳሌ፣ ልጆች የፕላስቲክ፣ የወረቀት ወይም የፎም ሳህኖችን በመጠቀም የሚጮህ ወይም ለስላሳ ድምጾችን የሚሰሩ የመነቅነቂያ መሳርያን መስራት ይችላሉ)።<br>• የድምጽ ውይይቶችን ከመግለጫ ጋር ማጣመር እና የንጽጽር ቃላቶችን መጠቀም።<br>• የክፍሉን ተጋባዥ እንግዳ ስለ መስሚያ መሳርያዎች ወይም የድምጽ ሲስተም እንዲያወሩ መጋበዝ።<br><br>20d. ጥላዎችን በሚፈጥሩ እቃዎች፣ በጥላዎች መጠን እና ቅርጽ እና የብርሃን ምንጭ መካከል ያለውን ግንኙነቶች ለመወሰን ምልከታዎችን ማድረግ።<br>*ለምሳሌ፣*<br>• በግድግዳው ላይ ያለውን ጥላ ትልቅ ለማድረግ የእንስሳ ቅርጽ ያለውን ወደ ኩራዝ ማስጠጋት<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ጥላዎችን ለማግኘት እና ጥላዎችን የሚፈጥሩትን እቃዎች እንደ ህንጻዎች፣ ዛፎች ወይም ሰዎች ለማግኘት ለጨዋታ ወደ ውጭ በምትሄዱበት ጊዜ “የጥላ እርምጃ” ያድርጉ።<br>• ልጆች የብርሃን ምንጮች እና ጥላዎችን የሚያካትቱ፣ እንደ እቃው ወደ ብርሃን ምንጩ ሲጠጋ እና ሲርቅ ያለውን የእቃን ጥላ ቁመት መለካት የመሳሰሉ ምርምሮችን እንዲያደርጉ እና ግኝቶችን ሪከርድ እንዲያደርጉ እድሎችን መፍጠር። | |

| ሳይንስ እና ኢንጂነሪንግ | ጨቅላ ህጻናቶች | ታዳጊዎች | ሁለት አመት ልጆች |
|---|---|---|---|
| መስፈርቶች | አመላካቾች | አመላካቾች | አመላካቾች |
| 21. የመሬት እና ህዋ ባህርዮችን መመርመር | 21a. በአቅራቢያው ካለ አከባቢ ጋር ይገናኛል<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ወደ ጸሀይ ብርሃን ጨረር መጠጋት<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ወደ ውጭ በመውጣት እንዲያስሱ እና በአካባቢው ያሉ እቃዎችን እንዲያመለክቱ እድል መስጠት።<br>• ጨቅላ ህጻናት ህይወት ካላቸው ነገሮች ጋር፣ አትክልቶች እና እንስሳቶችን ጨምሮ ደህንነታቸውን በጠበቀ መልኩ እንዲግባቡ የሚችሉበትን መንገዶች ማቅረብ። ልጆች ህይወት ያላቸው ነገሮች ላይ ያላቸውን ፍላጎት የሚያዩትን እና የሚያደርጉትን ነገር በመግለጽ ምላሽ መስጠት (ለምሳሌ፣ “You are pulling up that grass!” [“እናንተ ያንን ሳር እየሳባቹ ነው!”])።<br>• በተለያየ አይነቶች አስተማማኝ፣ ተገቢ የአየር ሁኔታ ላይ ጨቅላ ህጻናት ውጭውን እንዲያስሱ እድል መስጠት (ለምሳሌ፣ ቀላል ዝናብ በሞቃታማ ቀን፣ ቀዝቃዛ እና ጸሀያማ ቀን)።<br>• አስተማማኝ የሆኑ የተለያየ አይነት የተፈጥሮ እቃዎችን ማቅረብ። | 21a. በሰማይ ላይ ያሉትን እቃዎች መመልከት መጀምር<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ወደ ማታ አከባቢ ጨረቃዎን ያመልክቱ።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ልጆች ወደ ሰማይ ላይ እንዲያዩ መምራት። በሰማይ ላይ ያሉ እቃዎች ላይ ልጆች ላላቸው ፍላጎት እቃዎቹን በእንግሊዘኛ እና በሌላ የአገር ቤት ቋንቋዎች በመለየት ምላሽ መስጠት።<br>• ባህላቸውን የሚወክሉ እና በሰማይ ላይ ባሉ እቃዎች ላይ ትኩረት የሚያደርጉ መዝሙሮችን ለመለየት እና ለመዘመር (ለምሳሌ፣ “ድንቅነሽ፣ ድንቅነሽ፣ አንቺ ኮከብ”) ከወላጆች እና ልጆች ጋር መተባበር።<br>21b. የቅርብ አካባቢን፣ ህይወት ያላቸው ነገሮችን ጨምሮ መመልከት እና መዳሰስ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ድምጾችን በማስተዋል ቅጠሎችን ያንሱ ወይም ደግሞ ይርገጡ።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ከቤት ውጭ ጨዋታ ወይም በጋሪ ውጭ ሲንሸራሸሩ ወይም በእግር ሲራመዱ ልጆች በአካባቢያቸው ያሉትን አትክልቶች እና እንሥሳቶችን እንዲያስተዉሉ ያድርጉ፣ አትክሎቹን እና እንስሳቶችን በእንግሊዘኛ እና በአገር ቤት ቋንቋዎች መጥራት።<br>21c. የአካባቢውን የአየር ሁኔታ ክስተት መመልከት እና መመርመር (ለምሳሌ፣ ዝናብ፣ የጸሀይ ብርሃን፣ ንፋስ፣ በረዶ)<br>*ለምሳሌ፣*<br>• በንፋስ ላይ ጃኬት ወደ ላይ ከፍ አድርጎ መያዝ፣ እና ሲርገበገብ መመልከት።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ከልጁ ጋር በመሆን የአየር ሁኔታውን መመርመር። ከቤት ውጭ በሚወጡበት ጊዜ ልጆች በተለያዩ የአይር ሁኔታ አይነቶች የአየር ሁኔታውን እንዲያስሱ ይርዷቸው (ለምሳሌ፣ በረዶ እና ዝናብ መንካት)። | 21a. እቃዎችን በቀን እና የምሽታ ሰማይ መመልከት እና መለየት፣ ጸሀይን፣ ደመናዎችን፣ ጨረቃ እና ኮከቦችን ጨምሮ።<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ደመናዎችን ያመልክቱ እና በደመናማ ቀን “cloud” [“ደመና”] ይበሉ። የጸሀይን ስእል መሳል እና ጸሀይን በስም መለየት።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ልጆች በሰማይ ላይ ያሉ እቃዎችን በተለያየ አይነት የአየር ሁኔታ እና በቀን ውስጥ በተለያየ ጊዜ እንዲያስተውሉ እና ስማቸውን እንዲጠሩ ያበረታቷቸው። ስእል ያላቸውን መጽሀፎች እና በእንግሊዘኛ እና በሌሎች የአገር ቤት ቋንቋዎች ያሉ በሰማይ ላይ ስላሉ እቃዎች የሚያሳዩ መጽሀፎችን ማጋራት።<br>21b. የሚታወቁ ህይወት ያላቸው ነገሮች መሰረታዊ ባህርያትን መመርመር እና መለየት ይጀምራሉ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ጉንዳን ሆነ ብሎ መሬት ላይ ወደ ኮረብታው ስትንፏቀቅ በጥንቃቄ መመልከት። በሌሎች ኮረብታ ላይ ያሉ ጉንዳኖችን ይመልከቱ።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• በድራማዊ ጨዋታ ጊዜ በአካባቢው ያሉ እንስሳቶችን የሚወክሉ እውነተኛ የሚመስሉ የአሻንጉሊት እንስሳቶችን ማቅረብ።<br>• በክፍል ውስጥ እና በአካባቢው ላይ ያሉ ህይወት ያላቸውን እንስሳቶች መወያየት እና መለየት (ለምሳሌ፣ አሳ በውሃ ውስጥ መዋኘት እና መኖር ይችላል፣ ወፎች መብረር ይችላሉ እና ክንፎች አላቸው)።<br>21c. መሰረታዊ የአካባቢውን የአየር ሁኔታ ክስተት መመርመር እና መለየት መጀመር (ለምሳሌ፣ ዝናብ፣ የጸሀይ ብርሃን፣ ንፋስ፣ በረዶ)<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ውጭ ዝናብ ሲያዩ፣ “rain” [“ዝናብ”] በማለት ለአዋቂዎች ወይም ለአቻዎች መግለጽ እና የዝናብ ጃኬት ወይም ቦቲ ይያዛሉ።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• የአካባቢውን የአየር ሁኔታን መወያየት፣ ሰዎችን ምን እንዲሰማቸው እንደሚያደርግ ጨምሮ (ለምሳሌ፣ ቀዝቃዛ እና በረዷማ ነው፣ እርጥብ እና ዝናባማ ነው።) ለአየር ሁኔታው ተገቢነት ያለው ልብስ ለምን እንደለበሱ መወያየት (ለምሳሌ፣ በዝናብ ጊዜ የዝናብ ቦቲ፣ ለብርድ ጊዜ ጥጥ ያላቸው ጃኬቶች)።<br>• ባህላቸውን የሚወክሉ እና በአየር ሁኔታው ላይ የሚያተኩሩ መዝሙሮችን ለመለየት እና ለመዘመር ከወላጆች እና ከልጆች ጋር መተባበር። ልጆች ስለ አየር ሁኔታው ጥያቄዎችን እንዲጠይቁ ማገዝ። |

| ቅድም ትምህርት ቤት | ቅድመ መዋእለ ህጻናት ለመውጫ የሚጠበቁ ነገሮች | መዋእለ ህጻናት የመውጫ ተስፋዎች |
|---|---|---|
| አመላካቾች | አመላካቾች | ቀጣይ ትውልድ የሳይንስ መመዘኛዎች |
| 21a. የጸሀይ፣ ጨረቃ፣ ኮከቦች እና ደመናዎችን ባህርያትን እና የሚታይ እንቅስቃሴን አስመልክቶ ቀላል ምልከታዎች ማድረግ።<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ወደ ሰማይ ማመልከት እና ምን እንደሚያዩ ለመለየት የአገር ቤት ቋንቋ መጠቀም እንዲህ በማለት፣ “Look! [“ተመልከቱ!] The Sun is in the sky!” [ጸሀይዋ ሰማይ ላይ ናት!”]<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ደመና ሲሸፍናት ጸሀይዋ ሰማይ ላይ እንደምትቆይ ለማስረዳት እንደ አየሁህ አይነት ጨዋታዎችን መጫወት።<br>• በእንግሊዘኛ እና በሌሎች የአገር ውስጥ ቋንቋዎች ምልክት ያላቸውን የጸሀይ፣ ጨረቃ፣ ኮከቦች እና ደመናዎች እውነተኛ የሚመስሉ ምስሎች እና/ወይም ስእሎችን በመማርያ ክፍል ውስጥ ማካተት።<br>21b. በአቅራቢያ አካባቢ ያሉትን ህይወት ያላቸው ነገሮች መኖርያ ቦታን መመልከት እና መለየት መጀምር።<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ስለ አሳ ሲያወሩ ወደ ኩሬ ያመልክቱ። አስተማሪው የወፍ ጎጆ ሲያሳዩ፣ “Where is the bird?” [“ ወፏ የት ነች?”] ይበሉ።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ልጆች ህይወት ስላላቸው ነገሮች እና የት እንደሚኖሩ አስመልክቶ ያላቸውን የማወቅ ፍላጎት ያበረታቱ። ልጆች ህይወት ያላቸውን ነገሮች እንዲንከባከቡ እድሎችን ይስጡ (አትክልቶችን እና እንስሳቶችን ጨምሮ)።<br>• ስለ እንስሳት እና መኖርያቸው ታሪኮችን እና መረጃ ሰጭ ጽሁፎችን በእንግሊዘኛ እና በሌሎች የአገር ውስጥ ቋንቋዎች ያንብቡ።<br>21c. የአካባቢውን የአየር ሁኔታ እና ወቅቶች ለውጦችን መወያየት፣ የተለመዱ ከአየር ሁኔታ ጋር የተያያዙ ቃላቶችን በመጠቀም (ለምሳሌ፣ ዝናባማ፣ ጸሀያማ፣ ነፋሻማ)<br>*ለምሳሌ፣*<br>• የአየር ሁኔታውን ምልከታዎች ማከናወን እና የዝናብ ነጠብጣቦችን የሚያሳይ ስእል መሳል። ስለ ስእሉ ሲጠየቁ የአየር ሁኔታውን ለመግለጽ የእጅ ምልክቶችን መጠቀም።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ልጆች ለተለያዩ አይነት የአየር ሁኔታዎች ሊለብሱ የሚችሉትን ልብሶች ለማሳየት ስእሎችን እንዲመርጡ ልጆችን ማበረታታት።<br>• ወላጆች ስለ አየር ሁኔታ በእንግሊዘኛ እና በሌሎች የአገር ቤት ቋንቋዎች ምሳሌዎች እንዲያቀርቡ መጠየቅ እና መዝሙሮቹን ወላጆች ለተማሪዎች እንዲያብራሩ ይጠይቁ።<br>• የወቅቱን የአየር ሁኔታ ስእል ባለው ካርድ ላይ መለየት እና ከትላንት የአየር ሁኔታ ጋር ማወዳደር። | 21a. የጸሀይን ፣ የጨረቃ እና ኮከቦችን የሚታይ እንቅስቃሴዎች አስመልክቶ ምልከታዎችን ያደርጋሉ እና ተገማች ፓተርኖቹን ይገልጻል።<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ለአስተማሪው ይንገሩ፣ “Last night the moon was a circle but sometimes it’s only part of a circle.” [“ትላንት ማታ ጨረቃዋ ክብ ነበረች ነገር ግን አንዳንዴ የክብ ክፋይ ብቻ ናት።”]<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ለልጆች ስለጸሀይ፣ ጨረቃ እና ኮከቦች መረጃ የሚያካትት መጽሀፍን ያንቡላቸው።<br>• ልጆች ስለጸሀይ የሚታይ እንቅስቃሴ ወይም የጨረቃ ቅርጽ ለውጦችን የሚያሳይ ቻርት እንዲሰሩ ማበረታታት።<br>• ወላጆች ስለጸሀይ እና ስለጨረቃ የአገር ቤት ታሪክ ካላቸው እንዲያጋሩ መጋበዝ።<br>21b. ጥያቄዎቹን ማንሳት እና የተለያዩ አይነቶች የአካባቢው ሁኔታዎች(ውሃን ጨምሮ) ለተለያዩ አይነቶች ህይወት ያላቸው ነገሮች መጠለያን እንደሚሰጡ በውይይቶች ላይ ማሳተፍ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• የአሳ ስእል መሳል እና እንዲህ ማለት፣ “Fish live in the water because that’s where their food is.” [“አሳ ውሃ ውስጥ ይኖራል ምክንያቱም ምግባቸው እዚያ ስለሆነ።”]<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• ልጆች ውጭ ስለሚያዩት ነገር ጥያቄዎች እንዲጠይቁ እና ህይወት ስላላቸው ነገሮች እና የት እንደሚኖሩ የማወቅ ጉጉትን ማሳየት።<br>21c. በአመት ውስጥ በተለያዩ ጊዜያቶች ባሉ ምልከታዎች የተገኙትን ዳታ በመመርመር የአካባቢውን የአየር ሁኔታ ለውጥ እለታዊ እና ወቅታዊ ፓተርኖችን መግለጽ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• በክፍል ውስጥ በቻርት ላይ ያለውን የ እለታዊ የአየር ሁኔታ ዘገባዎችን መመልከት እና እንዲህ ማለት ፣ “Last week we had sunshine every day.” [“ባለፈው ሳምንት በየቀኑ የጸሀይ ብርሃን ነበረን።”]<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• በአመት ውስጥ ስላሉ ስለተለያዩ አይነቶች የአየር ሁኔታ መጽሀፍ ማንበብ። ሰዎች ለተለያዩ የአየር ሁኔታ አይነቶች የሚያደርጉትን ዝግጅት መወያየት።<br>• ልጆች በመደበኝነት የአየር ሁኔታ ቻርት እንዲሰሩ እና እንዲያሻሽሉ ማበረታታት።<br>• ልጆች ስለአየር ሁኔታ ድራማዊ ጨዋታ እንዲያዘጋጁ እና ለቤተሰቦቻቸው እንዲያቀርቡ ማበረታታት። | K-ESS2-1 የአየር ሁኔታ ምልከታዎችን በጊዜ ብዛት ያለውን ፓተርኖች ለመግለጽ መጠቀም እና ማጋራት።<br>K-ESS2-2 አትክልቶች እና እንስሳቶች (ሰዎችን ጨምሮ) ፍላጎታቸውን ለማሟላት አከባቢያቸውን እንዴት ሊቀይሩ እንደሚችሉ በመረጃ ላይ የተደገፈ ክርክር ማዘጋጀት።<br>K-ESS3-1 የተለያዩ አትክሎትች ወይም እንስሳቶች (ሰዎችን ጨምሮ) በፍላጎቶቻቸው እና በሚኖሩበት ቦታዎች ላይ ያለውን ግንኙነት የሚያሳይ ሞዴል መጠቀም።<br>K-ESS3-2 ስለ አየር ትንበያ አላማ መረጃ ለማግኘት ጥያቄዎችን መጠየቅ፣ ለከፋ የአየር ሁኔታ ለመዘጋጀት እና ምላሽ ለመስጠት።<br>K-ESS3-3 ሰዎች በመሬት፣ ውሃ፣ አየር እና/ወይም በአካባቢው ላይ ያሉ ሌሎች ህይወት ያላቸው ነገሮች ላይ ያልቸውን ተጽእኖ ለመቀነስ መፍትሄዎችን መግለጽ። |

| ሳይንስ እና ኢንጂነሪንግ | ጨቅላ ህጻናቶች | ታዳጊዎች | ሁለት አመት ልጆች |
|---|---|---|---|
| መስፈርቶች | አመላካቾች | አመላካቾች | አመላካቾች |
| 21. የመሬት እና ህዋ ባህርዮችን መመርመር<br>(ቀጣይ) | | 21d. በአካባቢ ያሉ የተፈጥሮ እቃዎችን መመልከት እና መመርመር (ለምሳሌ፣ አሸዋ፣ ውሃ፣ በረዶ)<br>*ለምሳሌ፣*<br>• የተለያዩ አይነቶች የተፈጥሮ እቃዎችን መመርመር አሸዋ በመቆፈር፣ ውሃ በመርጨት እና ዱላዎችን በመደርደር።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ከተፈጥሮ እቃዎችን ጋር ደህንነቱ የተጠበቀ አሰሳን ማበረታታት (ለምሳሌ፣ ውሃ፣ አሸዋ፣ ቅጠሎች፣ ጭቃ)። የተፈጥሮ እቃዎችን እና ተገቢ መሳርያዎችን እንዲያገኙ ማድረግ (ለምሳሌ፣ ቅሎች፣ ባልዲዎች)። ከልጁ ጋር የተፈጥሮ ነገሮችን መመርመር። | 21d. በአካባቢው የተፈጥሮ ሀብቶችን መሰረታዊ ባህርያትን መመልከት እና መለየት (ለምሳሌ፣ ዛፎች፣ አትክልቶች፣ የውሃ አካላት፣ እንስሳት )<br>*ለምሳሌ፣*<br>• በሚያዉቁት መንገድ ላይ ሲንሸራሸሩ ተወዳጅ የተፈጥሮ ሀብቶችን ዛፍ፣ የአበባ ቁጥቋጦ እና ወፎችን ጨምሮ ይለያሉ።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• የተለያዩ የቤት ውጭ ልምዶችን፣ በተፈጥሯዊ አካባቢዎች በእግር መጓዝ፣ ወደ መናፈሻዎች፣ ዛፎች እና ሙዚየሞችን መጓዝን ጨምሮ ማቅረብ። ስለተፈጥሮ ሀብቶች እና እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውሉ የማወቅ ፍላጎት ማሳየት። ልጆች የተፈጥሮ እቃዎችን እንዲሰበስቡ ማገዝ (ለምሳሌ፣ የጽድ ፍሬዎችን፣ ድንጋዮችን ወይም የዛፍ ፍሬዎች)።<br>21e. በአካባቢው ከቤት ውጭ ባሉ የተፈጥሮ እቃዎችን መመርምር እና ከነሱ ጋር የሚጋባቡበትን መንገዶችን መለየት መጀመር።<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ዱላዎችን ምንጭ ላይ መጣል እና ምንጩ ውሃውን ሲወስደው መመልከት።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• ከተፈጥሯዊ ሀብቶች ጋር እንዲግባቡ እድሎችን መስጠት። ልጆች በተፈጥሯዊ አለም ላይ ባላቸው ግንኙነት የምክንያት እና የውጤት ዝምድናን እንዲመርመርሙ ማበረታታት (ለምሳሌ፣ አንድ ድርጊት ሲያደርጉ ምን እንደሚፈጠር በማውራት )። |



| ቅድም ትምህርት ቤት | ቅድመ መዋእለ ህጻናት ለመውጫ የሚጠበቁ ነገሮች | መዋእለ ህጻናት የመውጫ ተስፋዎች |
| --- | --- | --- |
| አመላካቾች | አመላካቾች | ቀጣይ ትውልድ የሳይንስ መመዘኛዎች |
| 21d. ሰዎች ፍላጎታቸውን ለማሟላት የተፈጥሮ ሀብቶችን እንዴት እንደሚጠቀሙ መመልከት እና መለየት መጀመር (ለምሳሌ፣ ውሃ፣ አትክልቶች፣ እንስሳዎች)<br>*ለምሳሌ፣*<br>• የውሃ የተለያዩ ለመጠጣት፣ ለመዋኘት፣ ለመታጠብ እና አትክልቶችን ለማጠጣት ጨምሮ ያለውን ጥቅም ቋንቋ፣ስእሎች እና/ወይም ድርጊቶችን በመጠቀም መግለጽ።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ስለተፈጥሮ ሀብቶች የተለያዩ ጥቅሞች ፍላጎትን ማሳየት (ለምሳሌ፣ "I wonder what else we could use these trees for?" ["እነዚህን ዛፎች ለምን አገልግሎት ልንጠቀምባቸው እንደምንችል እደነቃለሁ?"])። ሰዎች የተፈጥሮ ሀብቶችን እንዴት እንደሚጠቀሙ በእንግሊዘኛ እና በአገር ቤት ቋንቋዎች ታሪኮችን እና መረጃ ሰጭ መጽሀፎችን ማንበብ።<br>• ልጆች ፍላጎታቸውን ለማሟላት የተፈጥሮ ሀብቶችን እንዴት እንደሚጠቀሙ መወያየት (ለምሳሌ፣ "We are thirsty so we need some clean water to drink. ["እኛ ውሃ ስለጠማን የምንጠጣው ንጹህ ውሃ እንፈልጋለን።] Would we drink water from the stream?" [የምንጭ ውሃ ልንጠጣ እንችላለን?"])።<br><br>21e. ሰዎች አካባቢያቸውን እንዴት እንደሚቀይሩ መመልከት እና መለየት መጀመር።<br>*ለምሳሌ፣*<br>• በመማሪያ ክፍል ውስጥ ያሉ አትክልቶችን ውሃ ማጠጣትን ማገዝ።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• ልጆች የቤት ውስጥ እና የውጭ አከባቢያቸውን የሚንከባከቡበት እድል ያቅርቡ። የሰዎች ድርጊት በአካባቢ ላይ ያለውን ተጽእኖ አስመልክቶ ታሪኮችን እና መረጃ ሰጭ ጽሁፎችን ያጋሩ። ሰዎች አካባቢያቸውን ሊጠብቁ የሚችሉባቸውን ዘዴዎች አስመልክቶ ከልጆች ጋር መወያየት። | 21d. ከውጭ አካባቢ በተደረጉ ምልከታዎች የተገኙትን መረጃዎች ሰዎች ፍላጎታቸውን ለማሟላት የተፈጥሮ ሀብቶችን ስለሚጠቀሙበት የተለያዩ ዘዴዎች መረጃ ላይ የተመሰረተ ሀሳብ ለማቅረብ መጠቀም<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ጥቅም ላይ የዋለ ወረቀትን በሪሳይክል ሳጥን ላይ ማስቀመጥ እና እንዲህ በማለት ማብራራት ፣ "Paper comes from trees so we have to recycle it." ["ወረቀት የሚመጣው ከዛፎች ስለሆን ሪሳይክል ማድረግ አለብን።"]<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• የክፍል ውስጥ የሪሳይክሊንግ ጣቢያ ማዘጋጀት እና ልጆች የተጠቀሙባቸውን ወረቀቶች እና ሌሎች ቆሻሻዎች በትክክለኛው ስፍራ እንዲያስቀምጡ ማስደረግ።<br>• ወላጆችን እና ልጆችን ወደ ሪሳይክሊንግ ጣቢያ አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ማሳተፍ።<br>• ሰዎች እቃዎችን በድጋሚ እንዴት እንደሚጠቀሙ ዘዴዎችን ማሳየት እንደ አርት፣ አፕሳይክሊንግ ወይም ደግሞ ማፈግ። |  |



| ሳይንስ እና ኢንጂነሪንግ | ጨቅላ ህጻናቶች | ታዳጊዎች | ሁለት አመት ልጆች |
|---|---|---|---|
| መስፈርቶች | አመላካቾች | አመላካቾች | አመላካቾች |
| 22. ኢንጂነሪንግን መመርመር | 22a. በአቅራቢያ አካባቢ ያሉ እቃዎችን መመርመር<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ራትል ይነቅንቁ እና ድምጽ ሲሰሙ ማቆም። ራትሉን በድጋሚ ይነቅንቁ እና ድምጹን በድጋሚ ሲሰሙ ማቆም። ይህንን ይደጋግሙ፣ ራትሉን በተደጋጋሚ መነቅነቅ።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ለልጆች በአስተማማኝ ሁኔታ ሊዳሰሱ የሚችሉ እቃዎችን ይስጧቸው።<br>• ከልጆች ጋር ከእቃዎች ጋር ያደረጉትን ዳሰሳ አስመልክቶ ማውራት (ለምሳሌ፣ “Yes, the rattle makes a sound! [“አዎ፣ ቅጭልጭሉ ድምጽ ያሰማል!] Oh, you stopped it!” [ኦህ፣ አስቆማቹት!”] ወይም “Where did the ball go? [“ኳሱ ወዴት ሄደ?] Oh, it rolled under the chair!” [ኦህ፣ በወንበር ስር ተንከባለለ!”])።<br><br>22b. ስሜቶች እና ፍላጎቶች በፊት መግለጫዎች እና ባህርይ መግለጽ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ተወዳጅ መጫወቻ ሲወሰድ ማልቀስ።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ልጆች ለሚገልጿቸው ነገሮች በገንቢ ሁኔታ ምላሽ መስጠት(ለምሳሌ፣ ብስጭትን ለሚገልጽ ልጅ ማጽናናት)። | 22a. እቃዎችን ሲመለከቱ እና ሲዳስሱ ጉጉት እና ፍላጎትን ማሳይት<br>*ለምሳሌ፣*<br>• በውሃ ጠረጴዛው ላይ የመጫወቻ ጀልባን መግፋት እና ጀልባው ወደላይ ሲወጣ በደስታ መመልከት።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ልጆች በአስተማማኝ ሁኔታ ሊያስሷቸው የሚችሏቸውን የተለያዩ እቃዎችን መስጠት እና እቃዎችን በተለያዩ መንገዶች እንዲያስሷቸው ጊዜ መስጠት።<br>• ስለ እቃዎች በማውራት እና ለመዳሰስ በመሞከር የልጆችን ጉጉት ይጨምሩ (ለምሳሌ፣ “Wow, the boat popped right back up after you pushed it down! [“ዋው፣ ጀልባው ከገፉቹት በኋላ መልሶ ብቅ አለ!] Will it stay up?” [እንደተነሳ ይቀራል?”[)።<br><br>22b. ስለሚፈልጉት ችግሮች ያላቸውን ስሜቶች መግለጽ (ለምሳሌ፣ ችግሩን ሲፈቱ መደሰት ወይም ችግሩን መፍታት ሳይችሉ ሲቀር መበሳጨት)<br>*ለምሳሌ፣*<br>• አራት ማእዘን የሆን ጡብ ያይዙ፣ በተጨናነቀ ሳጥን ውስጥ ባሉ ቀዳዳዎች ወይም በቅርጽ መለያ ውስጥ ለመክተት መሞከር እና በቀዳዳው ውስጥ ሲገባ በደስታ መጮህ።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• ልጆች ትኩረታቸውን የሚወስዱ ችግሮችን ለመፍታት ሲሞክሩ ስለችግር አፈታት ማሳየት እና ማውራት (ለምሳሌ፣ “Wow, that block is stuck in that tube. [“ዋው፣ ያ ጡብ በቱቦ ውስጥ ተለጥፏል።] I think we can push it out. [እኔ መግፋት እንደምንችል አስባለሁ።] Which block do you think we can push through the tube?” [በቱቦ ውስጥ ልንገፋው የምንችለው ጡብ የትኛው ይመስላቿል?”])።<br><br>22c. እቃዎችን ለማንቀሳቀስ እና ትኩረታቸውን የሚወስዱ ችግሮች ለመፍታት በመሞከር እና በመሳሳት ተግባራት መሳተፍ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• በድራም ሙዚቃ ለመስራት መሞከር፣ የሚፈልጉትን ድምጽ እስኪሰጥ ድረስ የእቃውን የተለያየ ክፍል በዱላ መምታት።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• በእቃዎች የፈጠራ ጨዋታን ማበረታታት። ትኩረት የሚስቡ ችግሮችን መፍታትን ማሳየት እና ስለዚያ ማውራት (ለምሳሌ፣ “How does this toy make noise? [“ይህ መጫወቻ ድምጽ እንዴት ነው የሚያወጣው?] Let’s try shaking it! [ለመነቅነቅ እንሞክር!] Oh, now you are tapping it! [ኦ፣ አሁን እየመታችሁት ነው!] Now we’ll try squeezing it!” [አሁን ለመጭመቅ እንሞክራለን!”])። | 22a. በታወቁ፣ ቀላል ችግሮች የማወቅ ጉጉት እና የማያቋርጥ ፍላጎት ማሳየት<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ጡቦች ምን ያክል ከፍታ ያለው ፎቅ ሊሆን እንደሚችል ለማየት እስኪደረመስ ድረስ መደርደር።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• ከእቃዎች ጋር የማያቋርጥ ተሳትፎ እንዲኖራቸው እድሎችን መስጠት። መረጃን ለመሰብሰብ የሚጠቅሙ ጥያቄዎችን ያሳዩ (ለምሳሌ፣ “Will the tower fall if put we put this big block on top of the small block?” [“ይህን ትልቅ ጡብ በትንሹ ጡብ ብናስቀምጠው ፎቁ ይወድቃል?”])<br><br>22b. በቃል እና ከቃል ውጪ በሆነ መንገድ ለታወቁ፣ ቀላል ችግሮች ቀላል መፍትሄዎች ማምጣት።<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ከአዋቂ ከትትል ጋር፣ መሰላል ማምጣት እና እቃውን ለማውረድ ደረጃው ላይ መውጣት። ሌላ ልጅ አንድን እቃ ሊደርስበት ሲቸገር፣ መሰላል ወደነሱ ማምጣት።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• ለስምምነት፣ ላለመስማማት ወዘተ የእጅ ምልክቶችን ማሳየት። የልጆችን መግባባት መጨመር፣ አስተያየት በመስጠት ወይም ጥያቄዎችን በማቅረብ (ለምሳሌ፣ ልጆች ምን ያክል ትልቅ የሆነ ፎቅ እንደገነቡ ለማሳየት አዋቂውን ይዘው ሲመጡ፣ አዋቂው ፣ “Wow, you built such a tall tower! [“ዋው፣ በጣም ረጅም ፎቅ ገንብታችኋል!] I wonder if we can add one more block.” [አንድ ተጨማሪ ጡብ መጨመር የምንችል እንደሆነ ብየ አስባለሁ።”] ብሎ ምላሽ መስጠት።)።<br><br>22c. እቃዎችን ሲመረምሩ የታወቁ፣ ቀላል ችግሮችን ለመፍታት የተለያዩ አማራጮችን ማሰስ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• በአካፋ ውሃ በመውሰድ ባልዲውን መሙላት መፈለግ። ከአካፋው ውሃ ሲንጠባጠብ፣ ሌላ የተለየ መሳሪያ ይፈልጉ እና ኩባያ ያግኙ። በመጨረሻ፣ ባልዲውን እራሱን ወደ ውሃው ምንጭ ያስጠጉ።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ልጆችን የተለያዩ የሚስቡ እቃዎችን ይስጧቸው እና እነሱን ፈጠራ በታከለበት ሁኔታ እንዲጠቀሙበት እድል ይስጧቸው።<br>• ልጆች ችግሮችን የመፍታት ሙከራቸውን ይወያዩ (ለምሳሌ፣ ልጆችን ሲከታተሉ እንዲህ ይበሉ፣ “You could not reach the sink, so you are standing on a big block, but you still can’t reach. [“ገንዳው ላይ ልትደርሱ አትችሉም፣ ስለዚህ ትልቅ ጡብ ላይ ቆማችኋል፣ ነገር ግን አሁንም ልትደርሱበት አትችሉም።] What could you step on that would make you even taller?” [የበለጠ ረጅም ሊያደርጋቹ የሚችል ምን እርምጃ መውሰደ ትችላላቹ?”]) |

| ቅድም ትምህርት ቤት | ቅድመ መዋእለ ህጻናት ለመውጫ የሚጠበቁ ነገሮች | መዋእለ ህጻናት የመውጫ ተስፋዎች |
|---|---|---|
| አመላካቾች | አመላካቾች | ቀጣይ ትውልድ የሳይንስ መመዘኛዎች |
| 22a. ጥያቄዎችን መጠየቅ፣ ምልከታዎችን ማድረግ እና ስለታወቁ፣ ቀላል ችግሮች መረጃ መሰብሰብ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• በጠፍጣፋ ሸርተቴ መኪና በፍጥነት እንዲንቀሳቀስ መፈለግ። ሸርተቴውን በጣም ሾጣጣ ለማድረግ ይሞክሩ እና መኪናው በሸርተቴው በጣም በፍጥነት ሲሄድ ይመልከቱ።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ለማያቋርጥ ጨዋታ እና እቃዎችን ለመመርመር የተለያየ አይነት እቃዎችን ያቅርቡ። ለመለካት መሳሪያዎን መጠቀም ያሳዩ። መረጃን ለመጠየቅ ወይም በዚያ ላይ ሀሳብ ለመስጠት ጥያቄዎችን መጠየቅ (ለምሳሌ፣ "What happened to the car when we changed the ramp? ["ሸረተቴውን ስንቀይረው መኪናው ምን ሆነ?] It moves more quickly when the ramp is steeper!" [ሸርተቴው በጣም ሾጣጣ ሲሆን በጣም በፍጥነት ይንቀሳቀሳል!"]<br>• የተማሪዎችን ምልከታ ለመመዝገብ የመመዝገቢያ ሰሌዳ መጠቀም (ለምሳሌ፣ ቅጠል፣ ህንጻ እና የትላትል ስእሎች)። | 22a. ስለሚታወቁ፣ ቀላል ችግሮች ጥያቄዎችን ይጠይቃሉ፣ ምልከታዎችን ያደርጋሉ እና መረጃ ይሰበስባሉ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• እንዲህ ማለት፣ "The small block stays on top of my tower better than the big block." ["ትንሹ ጡብ ከትልቁ ጡብ ይልቅ በፎቁ ላይኛው ክፍል ይቆያል።"]<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ልጆች ፎቆችን ስለመገንባት ያላቸውን ሀሳቦች ያዋርዋቸው፣ በተለይም በፎቆቹ ላይ እና ታች ላይ ያሉ የጡቦች አይነት ምን እንደሆኑ በማተኮር። ልጆች ሀሳብቻውን በምልከቶች፣ በስእሎች ወይም በእንግሊዘኛ ወይም ሌሎች የአገር ውስጥ ቋንቋዎች እንዲያጋሩ ያበረታቱ።<br>• ጡቦችን እና ሌሎች እቃዎችን በባህርያቸው መለየት እንደ መጠን፣ ቀለም ወይም ክብደት።<br>• ልጆችን መሳርያዎችን ስጧቸው እና መሳርያዎችን በመጠቀም መረጃ እንዴት መሰብሰብ እንደሚችሉ ማሳየት (ለምሳሌ፣ ማስመርያ፣ ሚዛን፣ ውሃልክ)። | K-2-ETS1-1 በአዲስ ወይም በተሻሻለ እቃ ወይም መሳሪያ ሊፈታ የሚችል አንድን ችግር ለመግለጽ ሰዎች ለመቀየር የሚፈልጉትን ሁኔታ ጥያቄዎችን መጠየቅ፣ ምልከታዎችን ማድረግ እና መረጃን መሰብሰብ።<br>K-2-ETS1-2 የአንድ እቃ ቅርጽ የአንድን ችግር ለመፍታት እንዴት እንደሚሰራ ለማብራራት ቀላል ስኬች፣ ስእል ወይም ግዙፍ ሞዴልን ማዘጋጀት።<br>K-2-ETS1-3 ተመሳሳይ ችግርን ለመፍታት የተሰሩ ከሁለት እቃዎች ሙከራዎች የተገኙ ዳታን የእያንዳንዱን አፈጻጸም ጥንካሬዎች እና ድክመቶች ለማወዳደር መመርመር |
| 22b. የሚታወቅ ቀላል ችግርን ለመፍታት ሀሳብን መግለጽ፣ በቃላት ወይም ከቃል ውጭ በሆነ መግባቢያ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• አስተማሪውን በእጅ መያዝ እና አስተማሪውን ወደ ጠርጴዛው ላይ በመጎተት ከመጽሀፍ መደርደሪያው ስር አንድ እቃ ለማውጣት መሳርያን እንዴት እንደተጠቀሙ ማሳየት።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ለመሳል እቃዎችን ማቅረብ፣ ልጆች ምን እንደሳሉ መጠየቅ ተጨማሪ ዝርዝሮችን፣ ተከታይ ጥያቄዎችን በመጠየቅ፣ ወዘተ ገለጻቸውን ማርዘም<br>• ከልጆች ጋር በቃል ከመግባባት በተጨማሪ የአካል እንቅስቃሴዎችን እና ምስሎችን መጠቀም እና መምርያዎችን መስጠት (ለምስሌ፣ ልጆች ሊሞክሩት የሚችሉትን ድርጊት ማስየት እና ማብራራት)።<br>• የተለያዩ ቴክኒኮችን በመጠቀም ችግሮችን በመፍታት ስኬታማ የሆኑ ልጆችን መጠቆም፣ እና ምሳሌዎችን መስጠት።<br>• የተማሪዎችን ሀሳቦች ለማጉላት የመመዝገቢያ ሰነዶችን መጠቀም። | 22b. የታወቀ፣ ቀላል ችግርን ቃላቶችን፣ ስእሎችን፣ ገለጻዎችን፣ ሞዴሎችን ወይም ሌሎች ከቃል ውጭ በሆኑ መግባቢያዎች ሀሳቦችን ይገልጻሉ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ቀስቶችን በመጠቀም አንድ ሮቦት ወደ አንድ የተወሰነ ቦታ እንዲሄድ የሚያሳይ ፕሮግራም መሳል።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• የራሳቸውን ስእሎች ወይም ፎቶግራፎችን በመጠቀም ልጆች የራሳቸውን መጽሀፎች እንዲሰሩ እቃዎችን ማቅረብ እና ማገዝ።<br>• ስለሳይንቲስቶች የስእል እቅዶች፣ ማስታወሻ ደብተር ስለመያዝ፣ ወዘተ መጽሀፍ ማንበብ።<br>• ያልተገደበ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የልጆችን የመግለጽ ችሎታ ማስፋት። | |
| 22c. ሲታወቅ፣ ቀላል ችግር መፍትሄን ይሞክራል እና የሙከራውን ውጤቶች መፍትሄው ውጤታማ መሆኑን ለመወሰን ይጠቀመዋል<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ሸርተቴ ይገንቡ እና እንዲህ ይበሉ፣ "My car didn't go because the ramp slips off the block." ["መኪናየ አልሄደም ምክንያቱም ሸረተቴው ከጡብ እየተንሸራተተ ነው።"]<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• እንደገና መሞከርን ማሳየት፣ ልጁ ሌሎች መፍትሄዎችን እንዲያስብ ወደ ሌሎች እቃዎች ወይም መሳሪያዎች መጠቆም።<br>• ልጆቹ ከፈለጉ፣ እየጠቆሙ ወይም በአካል እንቅሳቃሴ እያመለከቱ ድርጊቱን መቀጠል።<br>• ስለመስራት እና ስለፈጠራዊ የችግር አፈታት መጽሀፎችን ማቅረብ። የተማሪዎችን ሀሳቦች ለማጉላት የመመዝገቢያ ሰነዶችን መጠቀም።<br>• ለማወዳደር እና ለማነጻጸር ቻርቶችን እና ግራፎችን መጠቀም። | 22c. መፍትሄዎችን ለሚታወቁ፣ ቀላል ችግር ላይ መሞከር እና ውጤቶቹን የትኛው መፍትሄ በጣም ውጤታማ መሆኑን ለመወሰን ለሌሎች ውጤቶች ጋር ማወዳደር፣ አስፈላጊ ሲሆን ከአዋቂ እርዳታ ጋር<br>*ለምሳሌ፣*<br>• እቃን ወረቀት በመጠቀም መገንባት እና በግንባታው ላይ ሙጫ፣ ፕላስተር ፣ ስቴፕላር፣ ቀዳዳ መብሻ እና ክር መጠቀም። እንዲህ ይበሉ፣ "Tape works better than glue." ["ፕላስተር ከሙጫ የተሻለ ይሰራል።"]<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• አውደ ራእይ እንዲሮር ማድረግ እና ለአንድ ችግር የልጆችን የተለያዩ መፍትሄዎችን ተናገሩ።<br>• ልጆች ሀሳባቸውን እርስ በርስ እንዲጋሩ እና ያደረጉትን በቃላቶች ወይም በአካል እንቅስቃሴ እንዲያብራሩ ያድርጉ።<br>• የክፍል ተጋባዥ እንግዳ ጥያቄዎችን ስለመጠየቅ፣ መሳሪያዎችን ስለመጠቀም እና መፍትሄዎችን ስለመፈለግ አስፈላጊነት እንዲያወራ ይጋብዙ (ለምሳሌ፣ ጸሀፊ፣ ሪፖርተር፣ ጋጋሪ፣ቧምባ ሰሪ፣ አናጢ፣ወዘተ)። | |

| ማህበራዊ ጥናቶች | ጨቅላ ህጻናቶች | ታዳጊዎች | ሁለት አመት ልጆች |
|---|---|---|---|
| መስፈርቶች | አመላካቾች | አመላካቾች | አመላካቾች |
| 23. እራስን፣ ቤተሰብን እና የተለያዩ ማህበረሠብን መረዳትን ማሳየት | 23a. እራስን እና ሌሎችን መለየትን መጀመር<br>*ለምሳሌ፣*<br>• የታወቀ ድምጽ ሲሰሙ እና/ወይም የታወቀ አዋቂን ሲያዩ ማልቀስ ማቆም (ለምሳሌ ተንከባካቢ፣ ማሚ፣ ዳዲ፣ አስተማሪ፣ ወዘተ)።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ለጨቅላ ህጻን አስተማማኝ የሆን መስታወትን በመጠቀም ጨቅላ ህጻናቶች እራሳቸውን እንዲለዩ መርዳት።<br>• የጨቅላ ህጻናቶች የቤተሰብ ፎቶዎችን መጠቀም እና የቤተሰብ አባሎቻቸውን እንዲለዩ/ስለነሱ እንዲያወሩ ማድረግ። | 23a. ከሌሎች ሰዎች ጋር ያለውን ግንኙነቶችን እና ህብረትን መረዳት መጀመር<br>*ለምሳሌ፣*<br>• በመማሪያ ክፍል ውስጥ ያሉትን ተንከባካቢዎችን ማስታወስ/ስማቸውን መጥራት።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ስለራስ እና ስለሌሎች በትንሽ እና ትልቅ የቡድን እንቅስቃሴዎች ወቅት መዘመር (ለምሳሌ “Guess Who Came to School Today?” [“ዛሬ ወደ ትምህርት ቤት የመጣው ሰው ማን እንደሆነ ገምቱ?”] የሚለውን መዘመር)።<br>• ለታዳጊዎች ስለቤተሰባቸው እና ስለክፍላቸው አባሎቻቸው ያዋሯቸው። | 23a. የራስ እና የሌሎችን የአካል ባህርያቶችን የተወሰነ መመሳሳል እና ልዩነቶችን መለየት<br>*ለምሳሌ፣*<br>• የአካል ልዩነቶችን ማስተዋል (ለምሳሌ ለአቻዎች እንዲህ ማለት፣ “Your hair is short, my hair is long.” [“የእናንተ ጸጉር አጭር ነው፣ የኔ ጸጉር ረጅም ነው።”])<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ተመሳሳይ እና የተላያዩ የአካል ባህርያቶችን እና መግለጫዎቻቸውን ለመለየት ከልጆች ጋር መጫወት (ለምሳሌ፣ “ሳይመን እንዲህ ይላል” የሚለውን መጫወት)።<br>• በሰዎች መካከል ያለውን ልዮነቶች እና ስምምነቶች የሚያሳዩ የተለያዩ እቃዎችን እንደ እንቆቅልሾች፣ ወዘተ በመጠቀም በጣም የተለያዩ አይነት አካባቢን መፍጠር እና ከልጆች ጋር ስለነዚህ መመሳሳሎች እና ልዩነቶች ማውራት። |
| 24. በሰዎች እና በሚኖሩበት አካባቢ መካከል ያለውን ግንኙነት በተመለከተ ግንዛቤ ያሳያሉ | 24a. በአካባቢያቸው ያሉትን የሚታወቁ ሰዎችን ያስተውላሉ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ወላጅ ሲመጣ ወደ ራሳቸው ወላጅ መጮህ እና መሳብ።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ጨቅላ ህጻናቶችን ያዙ፣ አዋሯቸው እና ለምላሾቻቸው እውቅና ይስጡ።<br>• ስለቤተሰብ እና ማህበረሰብ መጽሀፎችን ያንቡ።<br>• ልጆችን በአካባቢያቸው በእግር አንሸራሽሯቸው እና ስለ ሰዎች (ለምሳሌ፣ ስለሚያቋርጠው ጥበቃ፣ ባለ ሱቆች፣ ወዘተ) እና ስለ አካባቢያቸው (ለምሳሌ፣ ዛፍ፣ የትምህርት ቤት ህንጻዎች፣ ፖስታ ቤት፣ የውሻ ፓርኮች፣ ወዘተ) ያዋሯቸው።<br><br>24b. ጀማሪ<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• በክፍሉ ውስጥ ስለጨቅላ ህጻናት አልጋዎች ወይም ጡጧቸው ስለሚቀመጥበት ቦታ ማውራት። | 24a. እራስን ከሌሎች የተለየ መሆኑን ማስተዋል መጀመር<br>*ለምሳሌ፣*<br>• አዋቂ፣ “Where is Mikel?” [“ሚኬል የታለ?”] ብለው ሲጠይቁ፣ወደ ሌላ ልጅ ይጠቁሙ(ለምሳሌ፣ ወደ ሚኬል ይጠቁሙ)<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• በክፍሉ ውስጥ ያሉ ሌሎች ልጆችን እና ሰዎችን እንዲያስተውሉ የሚረዳ መዝሙሮችን መዘመር (ለምሳሌ፣ “Guess Who Came to School Today” [“ዛሬ ትምህርት ቤት የመጣውን ሰው ገምቱ”])።<br><br>24b. ለሰዎች እና እቃዎች በተለያየ ሁኔታ ምላሽ መስጠት<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ለእርዳታ፣ ለምሪት እና ለደህንነት ወደ ተንከባካቢዎች ማየት።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ቀኑን ለልጆች እና ለቤተሰቦቻቸው በአወንታዊ ሰላምታዎች መጀመር እና መጨረስ።<br>• በትይዩ ጨዋታ ብዙ ለእድሜያቸው ተመጣጣኝ የሆኑ እቃዎችን በመስጠት ልጆችን መርዳት። | 24a. ለሌሎች ፍላጎቶች ምላሽ መስጠት<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ሌላ ልጅ ሲያለቅስ ሲያዩ ሌላ መጫወቻ መስጠት።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• ልጆች ስለሌሎች ያላቸውን ስጋት እውቅና መስጠት እና ሌሎችን ለመርዳት ወይም ለማረጋጋት መስራት።<br><br>24b. የራሳቸውን የግል ቦታ ማስተዋል መጀመር።<br>*ለምሳሌ፣*<br>• የግል ቦታን እንደ አልጋ መለየት።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• አዘውትረው ስለታዳጊዎች የግል ቦታ እንደ አልጋ አይነት ማውራት። |

| ቅድም ትምህርት ቤት | ቅድመ መዋእለ ህጻናት ለመውጫ የሚጠበቁ ነገሮች | መዋእለ ህጻናት የመውጫ ተስፋዎች |
|---|---|---|
| አመላካቾች | አመላካቾች | |
| 23a. የቡድን አባላትን እንደ የክፍል ወይም የቤተሰብ መለየት።<br>*ምሳሌዎች፣*<br>• የቤተሰብ ፎቶን ሲያዩ እራስን እና ሌሎች የቤተሰብ ወይም የክፍል አባሎችን መለየት።<br>• የቤት፣ ትምህርት ቤት ወይም ማህበረሰብን የሚገልጹ ስእሎች ወይም የጡብ ግንባታዎች መፍጠር።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• የቤተሰብ/ ክፍል ስእሎችን ማሳየት እና በፎቶ ውስጥ የተካተቱትን የተለያዩ ሰዎች ማውራት። | **የሰው ባህርዮችን እውቀት**<br>23a. የቡድን አባል በመሆን ያሉትን ሚናዎች መግለጽ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• እንዲህ ይበሉ፣ “I have three little brothers and I am the oldest.” [“እኔ ሶስት ታናናሽ ወንድሞች አሉን እና እኔ የሁሉም ታላቅ ነኝ።”]<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• በክፍል ውስጥ የስራ ሰንጠረዥ ያዘጋጁ እና ስለእያንዳንዱ ሚና ያሉትን ሃላፊነቶች ያውሩ።<br>• ልጆችን በክፍል ስብሰባዎች እና ውሳኔዎች ላይ ማሳተፍ።<br>• ለልጆች የክፍል ስራዎች እና ሃላፊነቶችን ይስጧቸው። |  |
| 24a. የግል ቦታ ከአካባቢው ጋር ያለውን ግንኙነት ያስተውላሉ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• በክብ ጊዜ በምንጣፉ ላይ በተጻፈ ፊደል ላይ መቀመጥ።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• የተለያዩ እቃዎችን በመጠቀም ከሌሎች ጋር የመግባቢያ ዘዴዎችን ማሳየት (ለምሳሌ፣ በምግብ ጊዜ፣እንዲህ ማለት፣ “Can you pass me the water pitcher please?” [“የውሃ ጆኩን ታቀብሉኛላቹ እባካቹ?”])።<br>24b. የራሳቸውን አካባቢ እና ሌሎች ስፍራዎችን ይለያሉ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• የራሳቸው ክፍል በትምህርት ቤት ውስጥ የት እንደሚገኝ ለአዋቂዎች መንገር።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• ልጆችን ወደ ማህበረሰብ የእግር ሽርሽር ይውሰዷቸው እና ስላዩት ነገር እንዲያወሩ እድል ይስጧቸው። | **በማህበረሰብ ውስጥ ያለውን ህይወት እውቀት**<br>24a. በራስ እና በአካባቢው ባሉ ሌሎች ሰዎች መካከል ያለውን ግንኙነቶን ያስተውላሉ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ራስን ከሌሎች ጋር ባለ ግንኙነት ይለያሉ (ለምሳሌ፣ እህት፣ ወንድም፣ የክፍል ልጅ፣ ጎረቤት፣ ወዘተ)።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• ልጆች በትብብር እንዲጫወቱ እድል ይስጧቸው (ለምሳሌ፣ የቦርድ ጨዋታ፣ እንቆቅልሾች፣ የትልቅ ቡድን ስእሎች፣ ወዘተ)።<br>24b. የግል ነጻነትን፣ በራስ እና በአካባቢዎች ያለውን ግንኙነት ያስተውላሉ።<br>*ለምሳሌ፣*<br>• እቃዎችን ከተለመደው ጂኦግራፊክ ስፍራ ጋር ማዛመድ (ለምሳሌ፣ ማንደጃ የሚቀመጠው ኩሽና፣ አልጋቹ የሚቀመጠው በመኝታ ቤታቹ ነው በመጫወቻ ቦታ አይደለም)።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• የመማርያ ክፍሎች፣ የመጫወቻ ስፍራ እና የቅርብ አካባቢን ካርታ መፍጠር።<br>• እቃዎች በተለመደ ቦታቸው ላይ ስለመሆናቸው ማስተዋልን የሚያበረታቱ ጨዋታዎች መጫወት (ለምሳሌ፣ የተሻሻሉ እንቆቅልሾችን)። | |

| ማህበራዊ ጥናቶች | ጨቅላ ህጻናቶች | ታዳጊዎች | ሁለት አመት ልጆች |
|---|---|---|---|
| መስፈርቶች | አመላካቾች | አመላካቾች | አመላካቾች |
| 25. ጊዜ ከራስ፣ ቤተሰብ እና ማህበረሰብ ጋር ባለው ግንኙነት ግንዛቤን ማሳየት | 25a. ለመደበኛ ተግባሮች/የክስተቶች ቅደም ተከተል/ልምዶች ምላሽ መስጠት መጀመር<br>*ለምሳሌ፣*<br>• በመምጫ ሰዓት ወይም በመሄጃ ሰዓት ማልቀስ።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• የሽግግር ጊዜን ጨምሮ የእለትተለት የጊዜ ሰሌዳ ወይም የቀን ውሎ ማዘጋጀት (ለምሳሌ፣ ዳይፐር ማድረጊያ፣ መመገቢያ፣ መተኛ ሰዓት፣ መልበሻ፣ ውጭ የመጫወቻ ጊዜ፣ ወዘተ)።<br>25b. ጀማሪ<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• የተለያዩ የእድሜ ክልሎችን የሚገልጽ መጽሀፎች/የስእል መጽሀፎችን ማንበብ (ለምሳሌ፣ የቤተሰብ አባላት የስእል መጽሀፎች_።<br>• ስለእለትተለት መደበኛ ተግባሮች እና ሽግግሮች ጨቅላ ህጻናቶችን ማዋራት። | 25a. መደበኛ ተግባሮች/ የክስተቶች ቅደም ተከተሎች/ልምዶች ማስተዋል።<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ከምሳ በኋላ ለመተኛት ወደ አልጋቸው መሄድ።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• ለምግብ ሰዓት፣ ለመምጫ እና መሄጃ፣ ዳይፐር እና ሽንት ቤት፣ የእንቅልፍ ሰዓት፣ የእንቅስቃሴ ሰዓት እና ሽግግሮችን መደበኛ ጊዜ ማዘጋጀት።<br>25b. ለለውጦች ምላሽ መስጠት መጀመር ሰዎች/ቦታዎች/ክስተቶች<br>*ለምሳሌ፣*<br>• በታወቀ የእንቅልፍ ጊዜ (ሁልጊዜ ወጥ ላይሆን ይችላል) አልጋቸው ላይ መተኛት።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• በሽግግሮች ጊዜ ታዳጊዎችን ማዋራት።<br>• ልጆች በአካባቢያቸው ስላሉ ለውጦች እንዲላመዱ የሚያስችል አስተማማኝ ቦታ መፍጠር። | 25a. ክስተቶችን በቅደም ተከተል ማስቀመጥ መጀመር<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ከአንድ እንቅስቃሴ በኋላ ምን እንደሚፈጠር መግለጽ።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• ልጆችን፣ በቡድን እና በግል በሁለቱም መልኩ፣ ከአንድ እንቅስቃሴ በኋላ ወይም ተረት ከተነበበ በኋላ ስለሚመጣው ክስተት እንዲያወሩ ማሳተፍ።<br>25b. በመደበኛ የእለትተለት ተግባሮች ላይ ስላሉ ለውጦች ምላሽ መስጠት ሰዎች/ቦታዎች/ክስተቶች<br>*ለምሳሌ፣*<br>• በክፍል ውስጥ ካለ ከአዲስ አዋቂ ጋር መጫወት (ምትክ አስተማሪ/ ተንከባካቢ)።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ምትክ አስተማሪ የሚመጣ ከሆነ ልጆችን ማዋራት።<br>• በየእለት መደበኛ ተግባሮች/ልምዶች ስለሚኖሩ ማንኛውም ለውጦች ከልጆች ጋር ያለማቋረጥ መወያየት። |



| ቅድም ትምህርት ቤት | ቅድመ መዋእለ ህጻናት ለመውጫ የሚጠበቁ ነገሮች | መዋእለ ህጻናት የመውጫ ተስፋዎች |
| --- | --- | --- |
| አመላካቾች | አመላካቾች | |
| 25a. የክስተቶችን ቅደም ተከተል በማስተዋል የስርአት እና የጊዜ ግንዛቤን መመስረት<br>*ለምሳሌ፣*<br>• የእለቱን ፕሮግራም መመልከት እና ቀጥሎ ምን እንደሚፈጠር መናገር (ለምሳሌ፣ የመክሰስ ሰዓት ከውጭ ሰዓት በኋላ ማስተዋል)።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• የእለቱን ክስተቶች በቻርት ወረቀት ላይ መመርመር፣ የጊዜ ክስተቶችን በማረጋገጥ፣ ልጆች በእግር ከተንሸራሸሩ በኋላ እንዴት ቀለም እንደቀቡ በማረጋገጥ።<br>• ከቃላቶች በሚተልቁ ስእሎችን በመጠቀም ምስላዊ የፕሮግራም ዝርዝር መፍጠር።<br><br>25b. በሰዎች /ቦታዎች/ በእለታዊ መደበኛ ክስተቶች/ የክስተቶች ቅደምተከተል/ ልምዶች ላይ በጊዜ ብዛት ያለውን ለውጦች መመርመር<br>*ምሳሌዎች፣*<br>• የክፍል ልጆችን እንዲህ ብለው ይንገሯቸው “The tree we planted is almost as tall as me now.” [“የተከልነው አትክልት ቁመቱ አሁን እኔን ሊያክል ነው።”]<br>• የቢራቢሮ የህይወት ኡደት ፎቶዎችን በቅደም ተከተል ማስቀመጥ።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• በጊዜ ብዛት የሚቀየሩ ነገሮችን ፎቶ ያንሱ እና በመማሪያ ክፍሉ ውስጥ እንዲታይ ያድርጉ (ለምሳሌ፣ የቢራቢሮ የህይወት ኡደት፣ ዘሮችን ማሳደግ፣ ወዘተ)<br>• አትክሎቶች እንዴት በጊዜ ሂደት እንደሚያድጉ እና እንደሚለወጡ ለማየት አዘውትሮ የትምህርት ቤት/የአካባቢን የጓሮ አትክልት መጎብኘት። | **ከታወቁ ሰዎች እና ቦታዎች ጋር የተያያዘ ለውጦች**<br>25a. የእለት ተእለት መደበኛ ተግባሮች/ የዝግጅቶች ቅደም ተከተሎች/ልምዶች፣ ከጊዜ ጋር የተያያዙ ቃላቶችን (ዛሬ/ነገ፣ አሁን/በኋላ) እና ያለፈ/የአሁን/ የወደፊት ጽንሰ ሀሳቦችን በጊዜ ማእቀፍ መረዳት<br>*ምሳሌዎች፣*<br>• መደበኛ ቀጠሮ የተያዘላቸውን ዝግጅቶችን በተመለከተ ጉጉትን ማሳየት።<br>• መደበኛ ተግባር/እንቅስቃሴ የተፈጠረበትን ጊዜ ለመግለጽ ቃላቶችን መጠቀም (ለምሳሌ እንዲህ ማለት፣ “Yesterday was my brother’s birthday.” [“ትላንት የወንድሜ ልደት ነበር።”])።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• በክብ ጊዜ ወይም በትንሽ ቡድን ጊዜ የቅደም ተከተል ጨዋታዎችን መጫወት (ለምሳሌ፣ እንዲህ ማለት “First touch your toes, then tap your nose.” [“መጀመሪያ የእግሮቻቹን ጣቶች ንኩ፣ ከዚያ አፍንጫዎን ይምቱ።”])።<br>• ለልጆች በቀን እና በሳምንት ምን እንደሚፈጠር ንገሯቸው።<br><br>25b. በአቅራቢያቸው ባለው አከባቢ የሚከሰቱ ለውጦችን ይመለከታሉ እና ያስተውላሉ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• የእለተተለት መደበኛ ተግባርን መግለጽ (ለምሳሌ፣ መጽሀፍ ጮክ ብሎ ከተነበበ በኋላ ምን ይፈጠራል፣ ከምሳ በኋላ እና በእለቱ የመጨረሻ ሰዓት)።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• በልጆች አካባቢ የሚከሰቱ ለውጦችን ለመግለጽ ክስተቶችን እና መደበኛ ተግባሮችን ለመለየት ቃላቶችን መጠቀም።<br>• ልጆች በህይወታቸው ስላሉ ስለተለያዩ ጊዜያቶች፣ ለምሳሌ ህጻን እያሉ ስለነበረው እንዲያወሩ ያበረታቱ። ከልጆች ጋር ሲያወሩ፣ ከዚያ እና አሁን የሚሉ ቃላቶችን ይጠቀሙ። | |



| ዘ አርትስ | ጨቅላ ህጻናቶች | ታዳጊዎች | ሁለት አመት ልጆች |
|---|---|---|---|
| መስፈርቶች | አመላካቾች | አመላካቾች | አመላካቾች |
| 26. በሙዚቃ እና የእንቅስቃሴ ተግባሮች መሳተፍ | 26a. ጀማሪ<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• በተለያዩ መንገዶች የሙዚቃ ልምዶችን ማቅረብ።<br>• አዳዲስ መዝሙሮችን በመደበኛነት ማስተዋወቅ እና ተወዳጅ የሆኑትን አዘውትረው መደጋገም።<br>• በየእለት መደበኛ ተግባሮች ላይ፣ መያዝ እና ከልጁ ጋር እንደመደነስ አይነት እንቅስቃሴዎችን ማካተት። | 26a. ለተለያዩ የሙዚቃ አይነቶች፣ የተለያዩ ባህላዊ እና ስነቋንቋዊ ሙዚቃ አይነቶችን ጨምሮ ምላሽ መስጠት<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ጭንቅላታቸውን ወደ ሙዚቃው ምንጭ ማዞር፣ መንቀሳቀስ፣ መደነስ፣ ማጨብጨብ (እንቅስቃሴዎች ከዜማው ጋር ላይጣጣሙ ይችላሉ)።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• በተለያዩ መንገዶች የሙዚቃ ልምዶችን ማቅረብ።<br>• አዳዲስ መዝሙሮችን በመደበኛነት ማስተዋወቅ እና ተወዳጅ የሆኑትን አዘውትረው መደጋገም።<br>• በእለታዊ መደበኛ ተግባሮች ላይ እንቅስቃሴዎችን ማካተት። | 26a. ለሙዚቃ እና እንቅስቃሴ ምላሽ መስጠት፣ የተለያዩ ባህላዊ እና ስነቋንቋዊ ሙዚቃ እና የእንቅስቃሴ ተግባሮችን ጨምሮ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ሰውነትን በማንቀሳቀስ፣ በመደነስ፣ በማጨብጨብ፣ በመወዛወዝ (እንቅስቃሴዎቹ ከዜማው ጋር ላይጣጣሙ ይችላሉ) ለሙዚቃ ምላሽ መስጠት ፣ለመዘመር መሞከር።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• የሙዚቃ ልምዶችን በተለያዩ መንገዶች ማቅረብ።<br>• አዳዲስ ሙዚቃዎችን በመደበኛነት ማስተዋወቅ፣ በእለታዊ መደበኛ ተግባሮች ሙዚቃ ላይ እንቅስቃሴን ያካቱ።<br>• አብረው እንዲዘምሩ መገፋፋት።<br>• የሙዚቃ የመርህ ቃላቶችን በግልጽ መጠቀም፣ እንደ፣ ምት፣ ቴምፖ፣ ዜማ፣ የድምጽ ቃና። |
| 27. በድራማዊ እንቅስቃሴዎች መሳተፍ | 27a. ጀማሪ<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• የገጸ ባህርይን የድምጽ ቃናዎች እና የፊት መግለጫዎችን በተረት ማንበብ ጊዜ ማሳየት።<br>• ከተለያዩ የባህል አይነቶች ታሪኮችን ማንበብ እና መናገር። | 27a. የታወቁ ትእይንቶችን መስራት።<br>*ለምሳሌ፣*<br>• የታወቁ ድርጊቶችን፣ እንደ ስልክን ወደ ጆሮ ማስጠጋት፣ ማንኪያን ወደ አፍ ማስጠጋት፣ ወዘተ ማስመሰል።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• የተለያዩ ባህሎችን የሚይሳዩ የእውነተኛ ህይወት እቃዎችን በሁሉም የመማርያ ክፍል ውስጥ ማቅረብ።<br>• ልጆች የእውነተኛ ህይወት አጋጣሚዎችን ለማስመሰል የሚያደርጓቸውን ሙከራዎች እውቅና መስጠት።<br>• የልጆች ጨዋታ ላይ መቀላቀል እና ጨዋታውን ለማርዘም ጥያቄዎችን መጠየቅ።<br>• የገጸ ባህርይ የድምጽ ቅላጼዎችን እና የፊት መግለጫዎችን በተረት ማንበቢያ ጊዜ ማሳየት።<br>• ከተለያዩ የባህል አይነቶች ታሪኮችን ማንበበ እና መንገር።<br>• ለማስመሰል ድራማ ሀሳቦችን መስጠት። | 27a. በማስመሰል ድራማ እውነተኛ ወይም ምናባዊ ትእይንቶችን መመርመር<br>*ለምሳሌ፣*<br>• እቃዎችን (ለምሳሌ፣ ማራካስ ሙዚቃ ለመጫወት) ለታለመላቸው አላማ መጠቀም።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• የተለያዩ ባህሎችን የሚይሳዩ የእውነተኛ ህይወት እቃዎችን በሁሉም የመማርያ ክፍል ውስጥ ማቅረብ።<br>• ልጆች የእውነተኛ ህይወት አጋጣሚዎችን ለማስመሰል የሚያደርጓቸውን ሙከራዎች እውቅና መስጠት።<br>• የልጆች ጨዋታ ላይ መቀላቀል እና ጨዋታውን ለማርዘም ጥያቄዎችን መጠየቅ።<br>• ልጆች በእውነተኛ ህይወት ያሉ እቃዎችን ለማስመስል እንዲበረታቱ የተለያዩ አይነት እቃዎችን ማቅረብ።<br>• ልጆች ቤት ውስጥ እና ከቤት ውጭ ሁለቱም ላይ የድራማ ጨዋታ እንዲጫወቱ ለማበረታታት እቃዎችን ማቅረብ።<br>• የገጸ ባህርይ የድምጽ ቅላጼዎችን እና የፊት መግለጫዎችን በተረት ማንበቢያ ጊዜ ማሳየት።<br>• ከተለያዩ የባህል አይነቶች ታሪኮችን ማንበበ እና መንገር።<br>• ለማስመሰል ድራማ ሀሳቦችን እና እድሎችን ማቅረብ።<br>• ለድራማ መርሆች ግልጽ ቃላቶችን መጠቀም፣ እንደ መድረክ፣ ጽሁፍ፣ ድጋፍ፣ አጭመ ታሪክ፣ ገጸ ባህርይ፣ ወዘተ። |

| ቅድም ትምህርት ቤት | ቅድመ መዋእለ ህጻናት ለመውጫ የሚጠበቁ ነገሮች | መዋእለ ህጻናት የመውጫ ተስፋዎች |
|---|---|---|
| አመላካቾች | አመላካቾች | |
| 26a. ስለሙዚቃ እና እንቅስቃሴ ምላሽ ይሰጣሉ፣ የተለያየ አይነት ባህላዊ እና ስነቋንቋዊ ሙዚቃ እና የእንቅስቃሴ ተግባሮችን ጨምሮ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ከፍ ባለ የሰውነት እንቅስቃሴ ለሙዚቃ ምላሽ መስጠት፣ አስተያየቶችን መጠቀም፣ መዘመር እና የሙዚቃ ፓተርኖችን ማስመሰል፣ የሙዚቃ መሳርያዎችን መሞከር።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ሆን ብለው ለሙዚቃ ምላሽ ይስጡ።<br>• ልጆች መዝሙሮች እና ጨዋታዎችን እንዲመርጡ ይጠይቁ።<br>• ልጆች በመዝሙር እና በዳንስ ላይ ፍላጎታቸውን እና ተሳትፏቸውን ያበረታቱ።<br>• ልጆች ለሙዚቃ ሲንቀሳቀሱ በግልጽ እውቅና ይስጡ።<br>• የሙዚቃ መሳርያዎችን እና የእውነተኛ ህይወት እቃዎችን እንዲመረምሩ እድሎችን ይስጡ።<br>• የሙዚቃ መርህ ቃላቶችን በግልጽ ይጠቀሙ፣ እንደ ምት፣ቴምፖ፣ ዜማ፣ የድምጽ ቃና። | 26a. በሙዚቃ እና እንቅስቃሴ ተግባሮች ላይ መሳተፍ፣ ለተለያዩ የሙዚቃ እና የውዝዋዜ አይነቶች፣ የተለያዩ ባህሎችን ሙዚቃ እና ዳንስን ጨምሮ ምላሽ መስጠት<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ደጋግሞ በመዘመር አስቂኝ የውዝዋዜ ስልት እና ዳንሶችን መፍጠር።<br>26b. ሙዚቃን ለማጀብ ወይም ለመፍጠር መሳርያዎችን እና ድምጽን ይጠቀማሉ።<br>*ለምሳሌ፣*<br>• በገንዳው ላይ ተራ እየጠበቃቹ የጥርስ መፋቅ መዝሙር መዘመር እና መስራት።<br>26c. ሀሳቦችን፣ ስሜቶችን እና አጋጣሚዎችን በሙዚቃ እና በእንቅስቃሴ መግለጽ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• አስተማሪ መዝሙር እንዲያዳምጥ ወይም የክፍል ልጆች የፈጠሩትን ዳንስ እንዲመለከቱ መጠየቅ።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ልጆች የተለያዩ አይነቶች ሙዚቃን በቡድን ወይም ብቻቸውን እንዲያዳምጡ እድል መስጠት።<br>• ልጆች በአካባቢው ያሉ የተለያዩ የዳንስ አይነቶችን እና የሙዚቃ ትርኢይቶችን እንዲያዩ መውሰድ።<br>• ለሙዚቃ እና ዳንስ መርሆች ግልጽ ቃላቶችን መጠቀም እንደ ምት፣ ስልት፣ ዜማ፣ የድምጽ ቃና፣ ወዘተ። | |
| 27a. በማስመሰል ድራማ እውነተኛ ወይም ምናባዊ ትእይንቶችን መመርመር<br>*ለምሳሌ፣*<br>• በድራማ ጨዋታ ላይ አንድ እቃ ሌላ እቃን እንዲወክል፣ የራስን የድራማ ትእይንቶች መፍጠር፣ አጋጣሚን በድራማ ማሳየት፣ ሰው ወይም እንስሳ እንደሆኑ ማስመሰል።<br>27b. እራስን ለመግለጽ በማስመሰል ድራማ ላይ ምናብም እና ፈጠራን ይጠቀማሉ።<br>*ለምሳሌ፣*<br>• የድምጽ ቅላጼዎችን እና የፊት መግለጫዎችን በማስመሰል እና በመድገም ሌሎችን ማዝናናት፣ ምናብን ወይም እውነተኛ የህይወት ገጠመኞችን በመጠቀም የማስመሰል ድራማን መስራት፣ ድራማቸውን ሌሎች እንዲያዩ መጠየቅ።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ልጆች የታወቁ ሁኔታዎችን ሚና እንዲጫወቱ ሁኔታዎችን መፍጠር።<br>• ልጆች በአዲስ አቅጣጫዎች እንዲጫወቱ ለማድረግ ጥያቄዎችን መጠየቅ እና ሀሳቦችን ማቅረብ።<br>• የገጸ ባህርይ የድምጽ ቅላጼዎችን እና የፊት መግለጫዎችን በተረት ማንበቢያ ጊዜ ማሳየት።<br>• ከተለያዩ የባህል አይነቶች ታሪኮችን ማንበበ እና መንገር።<br>• ሲጠየቁ ድራማዎችን ማየት።<br>• ለማስመሰል ድራማ ሀሳቦችን እና እድሎችን ማቅረብ።<br>• ከሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ኢንጂነሪንግ፣ አርት እና ሂሳብ (Science, Technology, Engineering, Arts and Math, STEAM) ሞያዎች ሀሳቦችን ድራማ ላይ ማካተት፣ እንደ ማይክሮስኮፕ፣ የላብራቶሪ ኮት፣ የደህንነት መሳሪያዎች፣ የግንባታ እቃዎች፣ የቀለም ቡርሾች እና የሙዚቃ መሳርያዎች።<br>• ምናባዊነትን እና ማስመሰልን ማበረታታት ትእይንቶችን በመጠቆም፣ እንደ በጫካ ውስጥ እንደ ነብር መንቀሳቀስ።<br>• ለድራማ መርሆች ግልጽ ቃላቶችን መጠቀም፣ እንደ መድረክ፣ ጽሁፍ፣ ድጋፍ፣ አጭመ ታሪክ፣ ገጸ ባህርይ፣ ወዘተ። | 27a. በድራማዊ ጨዋታዎች ላይ፣ ለተለያዩ ምናባዊ ገጸ ባህርዮች እና ትእይንቶች ምላሽ በመስጠት መሳተፍ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ትእይንት (ምናባዊ ወይም የእውነተኛ ህይወት) መፍጠር እና ሌላ ሰው ወይም እንስሳን ማስመሰል።<br>27b. ድራማ ለመፍጠር ድምጾችን ይጠቀማሉ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ገጸባህርዮችን ለመግለጽ ተወዳጅ መጽሀፍን በስሜት እና በተለያዩ የድምጽ ቃናዎች ለማንበብ መሞከር።<br>27c. ሀሳቦችን፣ ስሜቶችን፣ እና አጋጣሚዎችን በድራማዊ አገላለጽ መግለጽ።<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ስለ ልደቶች የሰሩትን ቲያትር እንዲመልከቱ አስተማሪውን መጠየቅ።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ልጆች እድሜያቸውን የሚመጥን በአካባቢያቸው ያሉ ትያትሮችን እንዲያዩ ይውሰዷቸው።<br>• ለድራማዊ ጨዋታ ግፊቶች እና እድሎችን ማቅረብ።<br>• የገጸ ባህርይ የድምጽ ቅላጼዎችን እና የፊት መግለጫዎችን በተረት ማንበቢያ ጊዜ ማሳየት።<br>• ልጆች በቤተሰባቸው ወይም አቻዎቻቸው ፊት የራሳቸውን ሀሳቦች እንዲገልጹ መፍቀድ።<br>• ልጆች የአንድን ታሪክ የራሳቸውን እይታ እንዲያቀርቡ ማበረታታት።<br>• ለድራማ መርሆች ግልጽ ቃላቶችን መጠቀም፣ እንደ መድረክ፣ ጽሁፍ፣ ድጋፍ፣ አጭመ ታሪክ፣ ገጸ ባህርይ፣ ወዘተ። | |

| ዘ አርትስ | ጨቅላ ህጻናቶች | ታዳጊዎች | ሁለት አመት ልጆች |
|---|---|---|---|
| መስፈርቶች | አመላካቾች | አመላካቾች | አመላካቾች |
| 28. የእይታ አርቶችን ማሰስ | 28a. ጀማሪ<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• የስነ ጥበብ እቃዎችን፣ እንደ የእጅ ስእሎችን በእጅ እንዲዳሱ ማድረግ።<br>• በአካባቢያቸው የሚስቡ እና ባለብዙ ቀለማት ምስሎችን ማቅረብ። | 28a. በኪነጥበብ ሂደት ውስጥ ለመሳተፍ የተለያዩ እቃዎችን ማዋሃድ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• በልጅ የሚሰሩ የስነጥበብ እንቅስቃሴዎች ላይ መሳተፍ፣ የተለያዩ አይነቶችን ጎጂ ያልሆኑ እቃዎች፣ እንደ ቀለም፣ ከለር፣ ማርከሮች፣ እንጨት፣ ፕሌይ ዶህ፣ ወዘት መጠቀም።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ቀኑን ሙሉ ለልጆች ጎጂ ያልሆኑ የኪነጥበብ እቃዎች እንዲኖራቸው ማድረግ።<br>• የልጆችን የኪነጥበብ ስራ ማሳየት።<br>• የተለያዩ አይነት ልምዶችን ለመስጠት የኪነጥበብ እቃዎችን ማዟዟር። | 28a. መሰረታዊ የሆኑ የእይታ ኪነጥበብን ግንዛቤን ማሳየት<br>*ለምሳሌ፣*<br>• የቀለም ግንዛቤ ማሳየት፣ የተለያዩ ቀለሞችን በመጠቀም ስእል መስራት።<br>28b. በኪነጥበብ ሂደት ውስጥ ለመሳተፍ የተለያዩ እቃዎችን ማዋሃድ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• የተለያዩ አይነቶች ጎጂ ያልሆኑ እቃዎችን ፣ እንደ ቀለም፣ ከለር፣ ማርከሮች፣እንጨት እና ፕሌይ ዶህ ተጠቀሙ፣ የስነጥበብ ቴክኖሎጂዎችን ማሳየት።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ቀኑን ሙሉ ለልጆች ጎጂ ያልሆኑ ቁሳቁሶችን እንዲያገኙ ያድርጉ።<br>• ምርቱ እስኪጠናቀቅ ሳይጠብቁ፣ ፈጠራዊ የሆነ ራስን የመግለጽ እቃዎችን እና መሳርያዎችን እንዲመረምሩ ያበረታቱ።<br>• እንደ ቀለም፣ ቅርፅ፣ መስመር፣ ወዘተ የመሳሰሉትን የእይታ ጥበባት መሰረታዊ መርሆችን ቃላቶችን በግልፅ ይጠቀሙ ፡፡<br>• አግባብነት ያላቸውን የስነጥበባት እቃዎችን አጠቃቀም ማሳየት። |



| ቅድም ትምህርት ቤት | ቅድመ መዋእለ ህጻናት ለመውጫ የሚጠበቁ ነገሮች | መዋእለ ህጻናት የመውጫ ተስፋዎች |
|---|---|---|
| አመላካቾች | አመላካቾች | |
| 28a. መሰረታዊ የእይታ ስነጥበባት ፍሬ ነገሮችን ያውቃሉ እና ይጠቀማሉ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ስለስነጥበብ መግለጽ፣ የቀለማት እና ቅርጾች ግንዛቤን ማሳየት፣ እቃዎችን ለታቀደላቸው አላማ መጠቀም።<br>28b. በኪነጥበብ ሂደት ውስጥ ለመሳተፍ የተለያዩ እቃዎችን ማዋሃድ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• የስነጥበብ እቃዎችን በአግባቡ መቆጣጠር እንደሚችሉ ማሳየት፣ ራሳቸውን ችለው የጥበብ ስራዎችን መስራት።<br>28c. እራስን ለመግለጽ ምናብን እና ፈጠራን ይጠቀማሉ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• አንድን ነገር የሚወክል ቀላል ስእሎችን ይሳሉ፣ የራስን ምስል መሳል፣ የራስን ፈጠራዎች ምልክት ማድረግ።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ልጆች ስለጥበብ ስራቸው እንዲያወሩ ማበረታታት።<br>• ጥያቄዎችን በመጠየቅ እና ምሳሌዎችን በማሳየት ፈጠራን ያበረታቱ።<br>• ቀኑን ሙሉ ልጆች ጎጂ ያልሆኑ የስነጥበብ እቃዎችን እንዲያገኙ ማድረግ።<br>• ምርቱ እስኪጠናቀቅ ሳይጠብቁ፣ ፈጠራዊ የሆነ ራስን የመግለጽ እቃዎችን እና መሳርያዎችን እንዲመረምሩ ያበረታቱ።<br>• እንደ ቀለም፣ ቅርፅ፣ መስመር፣ ወዘተ የመሳሰሉትን የእይታ ጥበባት መሰረታዊ መርሆችን ቃላቶችን በግልፅ ይጠቀሙ ።<br>• ተገቢ የስነጥበብ ቁሳቁሶች አጠቃቀምን ማሳየት።<br>• ፕሮጀክቶች ለበርካታ ቀናት እንዲራዘሙ መፍቀድ።<br>• የይዘት፣ ቅርጾች እና ቀለሞች ምሳሌ የሚያሳይ እቃዎችን ማቅረብ። | 28a. በስነጥበባዊ ተግባሮች ላይ፣ የእይታ የጠበብ ቅርጾች ላይ ምላሽ በመስጠት መሳተፍ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• የስእል ጋለሪን ከጎበኙ በኋላ ባለሶስት አቅጣጫ ቅርጽ መስራት።<br>28b. ምርቶችን ለመፍጠር የተለያዩ ቁሳቁሶችን ይጠቀማሉ።<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ወረቀት ላይ አንጸባራቂ ነገር መጨመር።<br>28c. በምስል ጥበባት ልምዶችን ፣ ሀሳቦችን እና ስሜቶችን ይገልጻሉ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ስለአስደሳች አጋጣሚዎች የግድግዳ ስእል ለመሳል ከትንሽ ቡድን ጋር አብረው ይስሩ።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• የስነጥበብ ፍላጎታቸውን ለማነሳሳት፣ ልጆች የመጽሀፍ ማብራርያዎችን እንዲመለከቱ፣ በኮምፒተር ላይ የቪዲዮ ክሊፖችን እንዲመለከቱ እና ስእሎችን እንዲጠቀሙ ያበረታቷቸው።<br>• ልጆች የሚመረምሯቸው የተለያዩ አይነት እቃዎች እንዲኖራቸው እቃዎችን ማዟዟር።<br>• ልጆች ከጥናት ምርመራዎች ጋር የተገናኙ ስእሎችን ወይም ቅርጾችን እንዲፈጥሩ መጋበዝ።<br>• ለልጆች ባለ ሁለት እና ሶስት ቅርጽ ያላቸውን የአርት እቃዎችን ማቅረብ።<br>• ልጆችን ወደ ስእል ጋለሪዎች ወይም ሙዚየሞች መውሰድ። | |

| ማህበራዊ እና ስሜታዊ እድገት | ጨቅላ ህጻናቶች | ታዳጊዎች | ሁለት አመት ልጆች |
|---|---|---|---|
| መስፈርቶች | አመላካቾች | አመላካቾች | አመላካቾች |
| 29. የተለያዩ አይነት ስሜቶችን መግለጽ እና እነሱን መቆጣጠር መማር | 29a. ስሜቶችን በፊት መግለጫዎች፣ የሰውነት እንቅስቃሴዎች፣ በማልቀስ እና በድምጽ መግለጽ፣ አብዛኛውን ጊዜ ለስሜት ለመጽናናት አዋቂዎች ጋር ጥገኛ በመሆን<br>*ለምሳሌ፣*<br>• እንግዳ ሲያነሳቸው ማልቀስ ይጀምራሉ ነገር ግን የወላጃቸውን ድምጽ ሲሰሙ ያቆማሉ።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• የጨቅላ ህጻን ስሜቶችን መለየት(ለምሳሌ፣ "You're waving your arms. ["እጆቹን እያውለበለባቹ ነው።] You must be glad to see me!" [እኔን በማየታቹ ተደስታቹ መሆን አለበት!"] | 29a. የተለያየ ማእቀፍ ያላቸውን ስሜቶች መግለጽ፣ ስሜቶችን ለመገራት የሌሎችን ሰዎች መግለጫዎችን መጠቀም፣ አብዛኛውን ጊዜ ለስሜታዊ መጽናናት አዋቂዎች ላይ ጥገኛ በመሆን፣ የተወሰኑ የራስ ማጽናናት ስልቶችን መጠቀም<br>*ለምሳሌ፣*<br>• የሌላ ልጅን መጫወቻ ከወሰዱ በኋላ ተንከባካቢያቸው ሲያይዋቸው ማልቀስ መጀመር።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• ልጆች በእንቅልፍ ጊዜ የግል የሚመቻቸውን እቃዎች እንዲያመጡ ሀሳብ ማቅረብ። | 29a. የአዋቂ ድጋፍ ሳይኖር የራስን ስሜቶች ማስተዋል እና መለየት፣ የተወሰኑ እራስን የማጽጽናናት ስልቶችን መጠቀም፣ ስሜቶችን በራስ የመቆጣጠር ስልቶችን አስመልክቶ የአዋቂ ምክሮችን መቀበል<br>*ለምሳሌ፣*<br>• አስተማሪ መጸዳጃ ቤቱን በትክክል በመጠቀማቹ፣ "You did it!" ["አደረግከው!"] ሲሉ ማጨብጨብ።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• የራስን ስሜቶች እና ድርጊቶችን ለመግለጽ ቃላቶችን መጠቀም (ለምሳሌ እንዲህ ማለት፣ "I'm frustrated, too, but we still need to clean up the toys that you threw." ["እኔም ተበሳጭቻለሁ፣ ነገር ግን የጣላችሁትን መጫዎቻዎች ማጽዳት አለብን።"]) |
| 30. የሌሎችን ሰዎች ስሜቶች እና መብቶችን መገንዘብ እና ተገቢውን ምላሽ መስጠት | 30a. ሌሎች ሰዎች ስሜታቸውን ሲገልጹ ምላሽ መስጠት<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ተንከባካቢያቸውን ማየት እና ተንከባካቢያቸው ንጽሁ ዳይበር አየር ላይ እያወዛወዙች አስቂኝ መዝሙር ስትዘምር መሳቅ።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• የልጅን ስሜቶች መለየት (ለምሳሌ፣ እንዲህ ማለት "Your smile tells me that you're happy." ["ፈገግታቹ ደስተኛ እንደሆናቹ ይነግረኛል።"])። | 30a. ሌሎች ስሜታቸውን ሲገልጹ ምላሽ መስጠት፣ አብዛኛውን ጊዜ የታማኝ አዋቂ ድጋፍ ኖሮበት<br>*ለምሳሌ፣*<br>• አስተማሪው እንዲህ ሲል፣ "Look how sad Marlo is. ["ማርሎ እንዴት እንዳዘነ ተመልከቱ።] Give Marlo a hug." [ማርሎን እቀፉት።"] ሲሉ ሌላውን ልጅ መታ መታ ማድረግ።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• ልጆች ስሜታቸውን የሚያሳዩበት እና ምላሽ ስለሚሰጥበት መንገዶች ትኩረት ይስጡ። | 30a. ሌሎች ስሜታቸውን ሲገልጹ ገንቢ በሆነ መልኩ ምላሽ መስጠት<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ሌላ ልጅ ወላጃቸው በመሄዱ ሲያዝኑ መጫወቻ መስጠት።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• የሌላን ሰው ችግር እንደሚረዱ ማሳየት (ለምሳሌ፣ "I'm sorry their juice spilled. ["ጭማቂያቸው በመፍሰሱ አዝኛለሁ።] I'm going to get them some more so they will have some." [ትንሽ እንዲጠጡ ለነሱ ተጨማሪ አመጣለሁ።"])። |
| 31. የራስን ባህርይ መቆጣጠር | 31a. በአቅራቢያው ባለ አከባቢ ወይም በአዋቂዎች ድምጾች እና ድርጊቶች ላይ ላለው ለውጦች ምላሽ መስጠት<br>*ለምሳሌ፣*<br>• የማይታወቁ አዋቂዎች ሲይዟቸው ያለቅሳሉ ነገር ግን የማይታወቀው አዋቂ መልሶ ሲያስቀምጣቸው ማልቀስ ያቆማሉ።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• ጨቅላ ህጻናቶች ሲያለቅሱ ወዲያውኑ ምላሽ ይስጡ። | 31a. ባህርይን ለመቆጣጠር ልዩ ሰውን ወይም እቃን መፈለግ፣ ነገሮችን ለራስ ማድረግ መፈለግ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ወላጅ ክፍሉን ለቆ ሲወጣ ከመጫወቻ ቤታቸው ብርድ ልብስ ማውጣት<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• የመጣደፍ ስሜታቸውን ለመቀነስ፣ ታዳጊዎች በተግባሮች መካከል የመሸጋገሪያ ጊዜ ይፍቀዱላቸው፣ ለምሳሌ ከእጅ መታጠብ ወደ መመገብ። | 31a. ከአዋቂዎች ወጥ የሆነ ድጋፍ በማግኘት መደበኛ ተግባሮችን መተግበር፣ ሌላ መመሪያን መቀበል፣ የራስን ፍላጎቶች ለማሟላት መሞከር<br>*ለምሳሌ፣*<br>• በመክሰስ ጊዜ መቀመጥ ነገር ግን አስተማሪ በልተው እሲከጨርሱ ድረስ እንዲቀመጡ እስኪያስታውሷቸው ድረስ ምግባቸውን ይዘው መዟዟር መጀመር።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• ተግባሮችን ከመቀየር በፊት ማስጠንቀቂያ መስጠት፣ እንደ በመንገዱ አንድ ተጨማሪ ጊዜ ሳይከላቸውን ከነዱ በኋላ ወደ ውስጥ መግባት እንዳለባቸው ለልጆች መንገር |

| ቅድም ትምህርት ቤት | ቅድመ መዋእለ ህጻናት ለመውጫ የሚጠበቁ ነገሮች | መዋእለ ህጻናት የመውጫ ተስፋዎች |
|---|---|---|
| አመላካቾች | አመላካቾች | |
| 29a. ስሜቶችን ለመቆጣጠር ከአዋቂዎች የተማሩ ስልቶችን ይጠቀማል ፣ ስሜቶችን መሰየም ይጀምራል<br>*ለምሳሌ፣*<br>• አካባቢው መሞቱን ከተነገረ በኋላ አሸዋውን እና የውሃውን አካባቢ በመተው እራሱን ያረጋጋል። በኋላ ተመልሰው ያብራሩ ፣ “I was mad because it was my turn.” [“ተራዬ ስለሆነ እብድ ነበር ።”]<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• ወደ ቡድን ለመግባት ወይም በሌላ ልጅ በሚጠቀሙበት አሻንጉሊት መጫወት ሲፈልጉ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ከልጆች ጋር ይነጋገሩ። | **ስሜቶች እና ባህሪዎች**<br>29a. ሀሳቦችን እና ስሜቶችን ለመግለጽ በማህበራዊ ተቀባይነት ያላቸውን መንገዶች ይጠቀማል<br>*ለምሳሌ፣*<br>• እንዲህ ይላል፤ “I’m using that shovel. [“ እኔ ያንን አካፋ እየተጠቀምኩበት ነው።] Please get another one.” [እባካቹ ሌላ ተጠቀሙ።”]<br>29b. የራስን ፍላጎቶች በማሟላት ላይ መተማመንን ያሳያል<br>*ለምሳሌ፣*<br>• የፈሰሰ ወተትን ለማጽዳት የወርቀት ፎጣ ማምጣት።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• ስለችግር ፈቺነት እና የግጭት አስተዳደር የቡድን ውይይቶችን መምራት። |  |
| 30a. ሌሎች ስሜታቸውን ሲገልጹ በአወንታዊ ሁኔታ ምላሽ መስጠት<br>*ለምሳሌ፣*<br>• የተበሳጩ አቻዎች የወተት ካርቶኑን እንዲከፍቱ መርዳት እና እንዲህ ማለት “I can do it. [“እኔ ላደርገው እችላለሁ።] You’ll learn how, too.” [እናንተም እንዴት ማድረግ እንደሚቻል ትማራላቹ።”]<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• ፈታኝ ሁኔታዎች ያሏቸውን መጽሀፎች፣ እንደ “አሌክሳንደር እና አስከፊው፣ አስፈሪው፣ ጥሩ ያልሆነ፣ በጣም መጥፎ ቀን” ያንቡ፣ ስለገጸባህርዮቹ ስሜቶች ያውሩ። | 30a. የሌሎችን መሰርታዊ ስሜቶች ማስተዋል እና መለየት<br>*ለምሳሌ፣*<br>• የክፍል ተማሪው ማልቀስ ሲጀምር ተማሪው አዝኗል ይበሉ።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• የተለያዩ አይነት ስሜቶችን እና ሰዎች እንዴት እንደሚገልጿቸው መወያየት፣ ስለስሜቶች እና ሰዎች እርስ በርስ እንዴት ምላሽ እንደሚሰጡ ታሪኮችን ማንበብ | |
| 31a. የመማሪያ ክፍል ህጎችን እና መደበኛ ተግባሮችን መተግበር (አዳዲሶችን ጨምሮ) አልፎ አልፎ ከአስታዋሾች ጋር<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ከማጽዳት መዝሙሩ በኋላ መጫወቻን ማስቀመጥ።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• ከልጆች ጋር ቀላል የመማሪያ ክፍል ህጎችን ያዘጋጁ። እነሱን ወጥነት ባለው መልኩ መወያየት እና መተግበር። | 31a. ገደቦችን እና የሚጠበቁ ነገሮችን መተግበር<br>*ለምሳሌ፣*<br>• በማስታወሻ፣ አንድን ተግባር ከመጀመር በፊት መመርያዎችን መጠበቅ።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• ከልጆች ጋር ስለ እለታዊ እቅዶች፣ የመደበኛ ተግባሮች ላይ ያሉ ለውጦችን ጨምሮ ማውራት (ለምሳሌ፣ በጣም በሚዘንብበት ጊዜ ወደ ውጭ አለመውጣት)። | |

| ማህበራዊ እና ስሜታዊ እድገት | ጨቅላ ህጻናቶች | ታዳጊዎች | ሁለት አመት ልጆች |
|---|---|---|---|
| መስፈርቶች | አመላካቾች | አመላካቾች | አመላካቾች |
| 32. ከአዋቂዎች ጋር አወንታዊ ግንኙነትን ማዳበር | 32a. የሚታወቁ አዋቂዎችን ማስታወስ፣ አወንታዊ ምላሽ መስጠት እና ከነሱ መቆየት መፈለግ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ሊወስዷቸው ወላጆች በሚመጡበት ጊዜ ሲያይዋቸው መጮህ እና ወደ ወላጃቸው መንፏቀቅ።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• ጨቅላ ህጻናቶችን መያዝ፣ ከነሱ ጋር ማውራት እና የግል ምላሾቻቸውን መቀበል። | 32a. ከአዳዲስ ህጻናቶች ጋር መግባባት፣ አብዛኛውን ጊዜ የሚታወቁ አዋቂዎችን አስተማማኝ መጠጊያ አድርጎ በመጠቀም፣ከሚታወቁ አዋቂዎች መሄድ እና ተመልሶ ወደነሱ መምጣት<br>*ለምሳሌ፣*<br>• የሚታወቅ አዋቂ(ለምሳሌ፣አስተማሪ፣ ዋና ተንከባካቢ፣ ወላጅ፣ ወዘተ) በመማሪያ ክፍሉ ውስጥ ሲሆን በእርጋታ መጫወት ነገር ግን፣ የሚታወቀው አዋቂ ክፍሉን ለቆ ሲወጣ ማልቀስ መጀመር እና ወደ በሩ መሄድ።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• የታዳጊ ልጅን የትኩረት ፍለጋን ፈገግታ በማሳየት፣በመሳቅ እና ከነሱ ጋር በማውራት ምላሽ መስጠት። | 32a. የተለያዩ ማእቀፍ ባላቸው ስፍራዎች ምቾት አላቸው፣ አስፈላጊ ሲሆን ለመጽናናት የሚያቋቸው አዋቂዎች ላይ ይደገፋሉ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• አስተማሪው፣ “Your parent will be here after your nap.” [“ወላጆችህ ከተኛህ ይመጣሉ።”] ብለው ሲናገሩ በአልጋቸው ላይ ሆነው ዘና ያላሉ።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• የቤተሰብ አባሎች ከልጆቻቸው ጋር አወንታዊ የሆነ የመለያየት ልምዶችን እንዲያዳብሩ ማበረታታት (ለምሳሌ፣ ልጁ በየቀኑ መስኮት ጋር ሆኖ ቻው እያለ እንዲያውለበልብ ማድረግ)። |
| 33. ከአቻዎች ጋር መሳተፍ እና መጫወት | 33a. ሌሎች ልጆችን ይመለከታሉ እና ከነሱ ጋር ማህበራዊ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ይሞክራሉ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• መገልበጥ፣ወደ ሌላ አቻ እየቀረበ መጠጋት እና አቻው እስኪመለከት እና ፈገግ እስኪል ድረስ መጮህ።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• ጨቅላ ህጻናት እናንተ ስታዋርዋቸው እርስ በርስ እንዲተያዩ እና እንዲግባቡ ለማስቻል አጠገብ ላጠገብ ማስቀመጥ። | 33a. ለአጭር ጊዜ ማህበራዊ ተሳትፎ በማድረግ፣ ከሌላ ልጅ አጠገብ መጫወት<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ይንጠራሩ፣ ልጁ የያዘውን የታጨቀች ድመትን መታ መታ ማድረግ እና በራሳቸው መጫወቻ ወደ መጫወት መመለስ።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• ለብቻ፣ ትዩዩ እና ማብሀራዊ ጨዋታ በቂ ስፍራ ቦታ መኖሩን ማረጋገጥ። | 33a. በተመሳሳይ እቃዎች ወይም ተግባሮች ላይ ከሚሳተፉ ልጆች ጋር መግባባት<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ሌላ ልጅ በሚሞላው ባልዲ ውስጥ አሸዋ በማንኪያ መሙላት።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• ጥንዶች ወይም ትንሽ የልጆች ቡድኖች፣ እንደ ፕሊይ ዶህ፣ አንድ ላይ እንዲጫወቱ ሀሳብ ማቅረብ። |
| 34. ከሌሎች ጋር ያለን ግጭት መፍታት | 34a. ጀማሪ<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• የተለያዩ ስሜቶችን የሚገልጹ የህጻናት ፊቶች ያላውን መጽሀፍ ማንበብ።<br>• የልጅን ስሜቶችን መለየት እና ስለዚያ እነሱን ማናገር (ለምሳሌ፣ እንዲህ ማለት፣ “Sara, you feel angry because Mia took your toy.” [“ሳራ፣ ንዴት ይሰማሻል ምክንያቱም ማያ መጫወቻሽን ስለወሰደች።”])። | 34a. ግጭት በሚኖርበት ጊዜ ያሉ ስሜቶችን በመግለጽ ምላሽ ይሰጣል<br>*ለምሳሌ፣*<br>• የእንቅልፍ ጊዜ መሆኑን እና መጫወት ማቆም እንዳለባቸው ሲነገራቸው በጣም ይጮሃሉ እና መጫወቻ ይጥላሉ።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• የልጁን ስሜት ይለዩ እና ከእንቅልፍ ጊዜ በኋላ እንደገና መጫወት እንደሚችሉ በመግለጽ ማባበል (ለምሳሌ ፣ እንዲህ ማለት “I know you are mad but you may play again after nap time.” [“እንደተናደዳችሁ አውቃለሁ ግን ከእንቅልፍ በኋላ እንደገና መጫወት ትችላላቹ።]”)። | 34a. ማህበራዊ ችግሮችን ለመፍታት የአዋቂዎችን ድጋፍ ይፈልጋል<br>*ለምሳሌ፣*<br>• “Teacher, they took my apple!” [“መምህር ፣ ፖሜን ወሰዱ!”] ብለው ይጩሁ እና አስተማሪው እስኪያስመልስልዎ ድረስ ይጠብቁ።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• ድጋፍዎን ይስጡ፣ ለምሳሌ፣ “I see you want the doll. [“አሻንጉሊቱን እንደምትፈልጉ አይቻለሁ።] Let’s get another one so each of you has a doll.” [እያንዳንዳቹ አሻንጉሊት እንዲኖራቹ ሌላ አሻንጉሊት እናምጣ።”] |

| ቅድም ትምህርት ቤት | ቅድመ መዋእለ ህጻናት ለመውጫ የሚጠበቁ ነገሮች | መዋእለ ህጻናት የመውጫ ተስፋዎች |
|---|---|---|
| አመላካቾች | አመላካቾች | |
| 32a. ለመረጃ እና ለመግባባት ከሚታመኑ አዋቂዎች ጋር መሳተፍ፣ መለያየትን መቆጣጠር<br>*ለምሳሌ፣*<br>• አስተማሪውን አዲስ ጫማ እንዳደረጉ ይንገሯቸው እና ለምን እንደሚወዱት ሲጠይቁ፣ "They light up!" ["ይበራል!"] በማለት ይግለጹ።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• ቀኑን ሙሉ ከልጆች ጋር በንግግር ይሳተፉ። | **አወንታዊ ግንኙነቶች**<br>32a. ሀሳቦችን ለመጋራት እና ተግባሮችን ለማቀድ ከአዋቂዎች ጋር በአወንታዊ መልኩ መሳተፍ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• አስተማሪውን እንዲህ ብለው ይጠይቁት፣ "Do you take the bus to school like I do?" ["እኔ እንደማደርገው ወደ ትምህርት ቤት በአዎቶብስ ነው የሚሄዱት?"]<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>ከልጆች ጋር ስለየእለት ህይወታቸው ያውሩ። | |
| 33a. ከሌሎች ጥቂት ልጆች ጋር አንድን ተግባር ለመጀመር ወይም ለመቀላቀል ስኬታማ ስልቶችን መጠቀም።<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ሌሎችን ልጆች ይጠይቁ እንዲህ በማለት፣ "Want to run with me?" ["ከኔ ጋር መሮጥ ትፈልጋላችሁ?"]<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• የሌሎችን ልጆች ጨዋታ ለመቀላቀል ልምድ ወይም ቋንቋ የሌላቸውን ልጆች ተገቢ የሆኑ ስልቶችን ወይም ቋንቋ በመጠቀም መርዳት። | 33a. ከሌሎች ጥቂት ልጆች ጋር መጫወትን መቀጠል።<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ለድራማዊ የመጫወቻ ስፍራ ለልጆች የተለያዩ ሚናዎችን መመደብ፣ እንዲህ በማለት፣ "You're the mother, you're the father and you're the sister." ["አንቺ እናት ነሽ፣ አንተ አባት ነህ እና አንቺ ደግሞ እህት ነሽ።"]<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• ልጆች በጡብ አንድ ላይ ከተማ እንዲሰሩ ማበረታታት፣ | |
| 34a. አዋቂዎችን እርዳታ ይጠይቃል እና አንዳንድ ጊዜ ማህበራዊ ችግሮችን መፍታት የሚችሉባቸውን መንገዶች ይጠቁማል<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ሌላው ልጅ በሸርተቴው ላይ ተራቸውን እንዲጠብቁ ይንገሯቸው።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• ልጆች ችግሮቻቸውን እንዲፈቱ ለመርዳት የክፍል ውስጥ ህጎችን ይጥቀሱ (ለምሳሌ ፣ አንድ ልጅ ውስጥ እየሮጠ ሌላ ልጅ ሲገጭ "Walk in the classroom" ["በክፍል ውስጥ ይራመዱ"] የሚለውን መመርያ ይከልሱ)። | 34a. ማህበራዊ ግጭቶችን ለመፍታት መንገዶችን ይጠቁማል<br>*ለምሳሌ፣*<br>• የተናደደ የክፍል ልጅ የሆነ ነገር ሲፈልግ ከመምታት ይልቅ "ቃላቶችቻቸውን እንዲጠቀሙ" መንገር።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• ግጭቶች ከመከሰታቸው በፊት የማህበራዊ ችግር አፈታት እርምቻዎችን ማስተማር ግጭት ሲነሳ እነዚህን እርምጃዎችን እንዲተገብሩ ልጆችን ማስተማር። | |

| የአካል እድገት ፣<br>ጤና እና ደህንነት | ጨቅላ ህጻናቶች | ታዳጊዎች | ሁለት አመት ልጆች |
|---|---|---|---|
| መስፈርቶች | አመላካቾች | አመላካቾች | አመላካቾች |
| 35. የትላልቅ ጡንቻዎችን ጥንካሬ እና ቅንጅትን ማሳየት | 35a. ለመንቀሳቀስ እጆችን፣ እግሮችን እና መላ አካልን ይጠቀማሉ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ይንከባለል፣ ይቀመጣል፣ ይንፏቀቃል እና ከዚያ ይራመዳል።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• ጨቅላ ህጻናት መገልበጥ፣ መነሳት እና መራመድን መማር የሚችሉበት አስተማማኝ የሆነ አካባቢን መስጠት። | 35a. በተለያዩ አይነት መንገዶች እና አቅጣጫዎች መንቀሳቀስ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ያለድጋፍ መራወጥ፣ ለመዝለል መሞከር፣እየተራመዱ ትልቅ ኳስ መያዝ።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• ታዳጊዎች ሰውነታቸውን በተላያዩ መንገዶች እንዲያንቀሳቅሱ የሚያበረታታ ሙዚቃ ማጫወት። | 35a. ቅንጅት እና ሚዛን የሚሹ አዳዲስ ትላልቅ የጡንቻ እንቅስቃሴዎችን ይሞክራል<br>*ለምሳሌ፣*<br>• የኳሶቹን አቅጣጫ ወይም ፍጥነት በትንሽ ቁጥጥር ኳሶችን ይሮጡ፣ ያሽከርክሩ፣ ይጣሉት፣ ያዙ እና ይጫኗቸው ::<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• ልጆችን አስተማማኝ የእንቅስቃሴ ጨዋታን ወደሚያበረታታ ወደ ውጭ ወይም ቤት ውስጥ ባለ ትልቅ ቦታ ወዳለው ስፍራ መውሰድ |
| 36. የትናንሽ ጡንቻዎችን ጥንካሬ እና ቅንጅትን ማሳየት | 36a. እቃዎችን ለመንካት፣ ለመያዝ እና ለማንሳት መላው እጅ እና ጣቶችን (ሁሉንም በአንድ ላይ፣ ማነጣጠር እና በመቀጠል አውራ ጣት እና ጠቋሚ ጣትን መጠቀም) መጠቀም<br>*ለምሳሌ፣*<br>• በሁለት እጆች ጠርሙስ መያዝ፣ ሲርየል (እህል) ማንሳት፣ ከእቃ መያዣ እቃዎችን ማውጣት።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• አስተማማኝ የሆኑ እቃዎችን ጨቅላ ህጻናት ሊደርሱበት በሚችሉት ቦታ ማስቀመጥ እና እንዲይዟቸው ማበረታታት። | 36a. ሁለት እጆች የሚጠይቁ እንቅስቃሴዎችን መሞከር፣ እቃዎችን ለማስቀመጥ እና ለመልቀቅ ጣቶችን እና መላ የእጅ እንቅስቃሴዎችን መጠቀም<br>*ለምሳሌ፣*<br>• በትልቅ እርሳሶች መሞነጫጨር፣ የመጽሀፍን ገጾች መግለጥ (አብዛኛውን ጊዜ ባንዴ ከአንድ በላይ)፣ ማንኪያ እና ሹካ መጠቀም መጀመር።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• ልጆች የተለያዩ እቃዎችን ለምሳሌ የተለያየ መጠን ያላቸው ኳሶችን እንዲያነሱ እና ወደ ቅርጫት ውስጥ እንዲከቱ ማበረታታት። | 36a. የአይን- እጅ ቅንጅትን የሚጠይቁ እንቅስቃሴዎችን ማበረታታት፣ እቃዎችን ለማንቀሳቀስ የእጅ አንጓን እና የጣት እንቅስቃሴዎችን መጠቀም<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ፈሳሾችን ከእቃ መያዣ ወደ ኩባያ መቅዳት፣ ቀላል እንቆቅልሾችን መስራት፣ ትላልቅ ዶቃዎችን ማያያዝ።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• ለመደርደር እቃዎችን ማቅረብ (ለምሳሌ ፣ የተለያዩ መጠኖች እና ቅርጾች ያሏቸው ጡቦች)። |

| ቅድም ትምህርት ቤት | ቅድመ መዋእለ ህጻናት ለመውጫ የሚጠበቁ ነገሮች | መዋእለ ህጻናት የመውጫ ተስፋዎች |
| --- | --- | --- |
| አመላካቾች | አመላካቾች | |
| 35a. ውስብስብ በሆኑ ተጣጣፊነትን፣ መቆጣጠርን እና ሙሉ እንቅስቃሴ በሚጠይቁ ባለትልቅ ጡንቻ እንቅስቃሴዎች ላይ መሳተፍ።<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ባለሶስት ጎማ ሳይክልን መንዳት፣ ለመጋለብ መሞከር፣ እግሮችን በማቀያየር ደረጃዎችን ወደላይ መውጣት እና መውረድ፣ ኳስን ወደ ሰው ወይም ቦታ መምታት እና መወርወር።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• ልጆች የላይኛው እና የታችኛው የሰውነት እንቅስቃሴዎችን እንዲያቀናጁ የሚያበረታቱ የተለያዩ መሣሪያዎችን ይጠቀሙ። | **ትልቅ ጡንቻ ጥንካሬ እና ቅንጅት**<br>35a. በተቀላጠፈ ሁኔታ በመሮጥ የመንቀሳቀስ ችሎታዎችን ማሳየት<br>*ለምሳሌ፣*<br>• በሁለት የመጫወቻ ሜዳዎች መካከል ወደኋላ እና ወደ ፊት መሮጥ።<br>35b. በአንድ ቦታ ላይ በመዝለል ሚዛን የመጠበቅ ችሎታን ማሳየት<br>*ለምሳሌ፣*<br>• አስተማሪው “Who would like to set the table?” [“ጠረጴዛውን ማዘጋጀት የሚፈልግ ማነው?”] በማለት ሲጠይቁ፣ ባሉበት ወደላይ እና ወደታች መዝለል።<br>35c. ሙሉ እንቅስቃሴን በመጠቀም፣ የኳስ አያያዝ ችሎታን ማሳየት<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ሁለቱንም እጆችን ወደላይ እና ወደታች በማንቀሳቀስ፣ ኳሶችን ወደትልቅ የማከማቻ ገንዳ መወርወር።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ሩጫን የሚያካትቱ ጨዋታዎችን መጫወት፣ ለምሳሌ፣ “ዳክዬ ፣ ዳክዬ፣ ጉዝ።”<br>• ልጆች ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ መንቀሳቀስ የሚቻልባቸውን መንገዶች እንዲያስቡ መጠየቅ፣ ለምሳሌ እንደ ጥንቸል መዝለል ወይም እንደ ዝሆን እያዘገሙ መራመድ።<br>• መወርወርን መለማመድ የሚያስችል የተያየ እድሎችን ለልጆች ማቅረብ (ለምሳሌ፣ በክፍል ውስጥ ቢንባግ ጨዋታ ላይ (በቦርሳ ውስጥ ያሉ የደረቁ ባቄላዎችን ውርወራ ጨዋታ) እና ከክፍል ውጭ ደግሞ የኳስ ጨዋታ)። | |
| 36a. በትናንሽ ዕቃዎች ለመስራት እና ተግባሮችን ለማከናወን የጣት እና የእጅ እንቅስቃሴዎችን መጠቀም<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ቅርጾችን ኮፒ ማድረግ፣ በመቀስ መቁረጥ፣ ትልቅ ቁልፎች ያላቸውን መቆለፍ፣ የተወሰኑ ፊደል ወይም ቁጥር ነክ ቅርጾችን መጻፍ፣ስቴፕለር እና ፕላስተር መጠቀም።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• ትክክለኛ እንቅስቃሴዎችን የሚያበረታቱ የተለያዩ የአርት እቃዎችን ለምሳሌ፣ እንደ ቀጭን ጫፎች ያላቸውም ማርከሮች ማቅረብ። | **ትናንሽ ጡንቻ ጥንካሬ እና ቅንጅት**<br>36a. ትናንሽ እቃዎችን ለመያዝ ትክክለኛውን እጅ፣ጣት እና የእጅ አንጓ እንቅስቃሴዎችን ይጠቀማሉ።<br>*ለምሳሌ፣*<br>• የተለያየ ማእቀፍ ያላቸውን የጡንቻ እንቅስቃሴዎችን በመጠቀም፣ የካቢኔት ቁልፍ በመክፈት፣ የአሻንጉሊት ልብስ ቁልፍ በመቆለፍ እና ትናንሽ ሳህኖችን ጠረጴዛ ላይ በማስቀመጥ በድራማዊ የእቃ እቃ ጨዋታ እና ግፊቶች ይጫወታሉ።<br>36b. የተወሰነ ተግባር ለማከናወን የመጻፊያ እና የመሳያ መስርያዎችን ይጠቀማሉ።<br>*ለምሳሌ፣*<br>• የምስጋና ካርድ ለመስራት የተለያዩ አይነት እቃዎችን፣ እንደ ቀለም ያላቸው እርሳሶችን፣ እስክርቢቶዎች እና ቀጭን ማርከሮችን መጠቀም።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ልጆች የምግብ ማብሰያ መስርያዎችን እንዲጠቀሙ ማበረታታት፣ በምግብ ማብሰል ተግባሮች፣ መክሰስ እና ምግብ ወቅት የምግብ ቁሳቁሶችን እና የግል የምግብ ቁሳቁሶችን እንዲያቀርቡ ማድረግ።<br>• በሁሉም ፍላጎት ባላቸው ነገሮች ላይ የጽሁፍ ሰነዶችን ማቅረብ እና ልጆች እንዲጠቀሙባቸው ቀኑን ሙሉ ማበረታታት። | |

| የአካል እድገት ፣<br>ጤና እና ደህንነት | ጨቅላ ህጻናቶች | ታዳጊዎች | ሁለት አመት ልጆች |
| --- | --- | --- | --- |
| መስፈርቶች | አመላካቾች | አመላካቾች | አመላካቾች |
| 37. ጤናን እና ደህነትን የሚያበረታቱ ባህርዮችን ማሳየት | 37a. የጤና እና የደህንነት መደበኛ ተግባሮችን መልመድ፣ ደህነነቱ የተጠበቀ አካባቢን ለማቅረብ ግን በአዋቂ ላይ መደገፍ<br>*ምሳሌዎች፣*<br>• ጡጦው እንዲጠቡ ሲመጣላቸው ጭንቅላታቸውን ወደ ጡጦው ማዞር፣ ጡጦ ወይም ኩባያ ለመያዝ መሞከር፣ ለምግብ አፋቸውን መክፈት።<br>• መሰረታዊ የእንክብካቤ እና የጤና ፍላጎቶችን እንደ ረሀብ፣ ህመም፣ እንቅልፍ መፈልግ፣ ወዘተ የመሳሰሉትን ለማመልከት የተለያዩ ምልክቶችን መጠቀም እና ማልቀስ።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ትን የሚያስብሉ ምግቦችን እና ማንኛውም ለጨቅላው ህጻን ወይም ሌሎች ግለሰቦች አለርጂ የሆኑ ምግቦችን ይገንዘቡ።<br>• ጨቅላ ህጻን የሚፈልገውን ነገር ሲያመለክት መረዳት፣ ማስተዋል እና በአወንታዊ ሁኔታ ወዲያዉኑ ምላሽ መስጠት።<br><br>37b. የራሳቸውን ፍላጎት ለማሟላት መሳተፍ መጀመር።<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ምግብ ሲሰጣቸው አፋቸውን መክፈት።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• አወንታዊ የሆነ የምግብ ጊዜ ማቅረብ።<br><br>37c. ጀማሪ<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• ልጆች እንዴት መነካት/መያዝ እንደሚፈልጉ (ወይም እንዴት እንደማይፈልጉ) የሚሰጡትን ምልክቶች ማክበር እና ምላሽ መስጠት።<br><br>37d. ጀማሪ<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• ለጨቅላው ህጻን ምቾት ማጣት ሊያረጋጋቸው በሚችል እና ወዲያኑ ምላሽ መስጠት። | 37a. በማስመሰል እና በመሳተፍ የጤና እና የደህንነት ተግባሮች እውቀታቸው መጨመሩን ማሳየት<br>*ምሳሌዎች፣*<br>• እጃቸውን ለመታጠብ ማቅረብ፣ የጥርስ ቡርሽ መያዝ፣ ጠረጴዛውን በጨርቅ መወልወል።<br>• የቃል የደህንነት ማስጠንቀቂያዎችን ምላሽ መስጠት መጀመር እንደ አቁም፣ ትኩስ፣ አይ፣ ወዘተ።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• መደበኛ የእንክብካቤ ተግባሮችን አስደሳች ያድርጉ መዝሙሮችን በመዘመር እና የጣት ጨዋታዎችን በመጋራት (ለምሳሌ፣ መዘመር፣ “This Is the Way We Wash Our Hands” [“እጃችንን የምንታጠበው እንደዚህ ነው”])።<br>• በመደበኛ ተግባር ላይ ስለቀጣዩ ደረጃ ልጆችን ማዋራት።<br><br>37b. መሰረታዊ የአመጋገብ፣ የአለባበስ እና የንጽህና ተግባሮችን መሞከር።<br>*ለምሳሌ፣*<br>• እራስን ለመመገብ ሲሪያሉን ማንሳት፣ ካልሲ ማውለቅ።<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• ልጁ ተግባሮችን ማከናወን የሚችልበት እድል መስጠት (ለምሳሌ፣ ቼሪዮ ማንሳት እና ኮፍያ ማድረግ)።<br><br>37c. ጀማሪ<br>*ደጋፊ ልምዶች፣*<br>• ልጆች እንዴት መነካት/መያዝ እንደሚፈልጉ (ወይም እንዴት እንደማይፈልጉ) የሚሰጡትን ምልክቶች ማክበር እና ምላሽ መስጠት።<br><br>37d. ጀማሪ<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• የታዳጊውን ልጅ ምቾት ማጣት ሊያረጋጋቸው በሚችል መንገዶች እና ወዲያውኑ ምላሽ መስጠት።<br>• ከልጆች ጋር ደህንነታቸውን የሚያበረታታ እና ወጥነት ባለው መልኩ፣ የእንክብካቤ እና የመግባባት ሁኔታን ማሳየት እና/ወይም መግለጽ። | 37a. የጤና እና የደህንነት ተግባሮችን መሞከር በመጀመር ግንዛቤያቸው መጨመሩን ማሳየት<br>*ምሳሌዎች፣*<br>• ዳይፐር መነተት እና ዳይፐሩ ሲረጥብ “pee pee” [“ፒ ፒ”] ማለት።<br>• እጃቸውን ከታጠቡ በኋላ እንዲያደርቁ ሲነገራቸው ፎጣ መያዝ።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ልጆች በጤና እና እንክብካቤ መደበኛ ተግባሮች ላይ እንዲሳተፉ ማበረታታት (ለምሳሌ፣ እያገዟቸው እጃቸውን መታጠብ እና ማድረቅ፣ ጃኬት ሲለብሱ እጃቸውን ማውጣት፣ የተደፋ ነገር በማጽዳት ማገዝ)።<br>• አወንታዊ የሆነ የመጸዳጃ ቤት የመማር ልምድን ማቅረብ (ለማሳሌ፣ “Nate, it is time to go potty.” [“ኔት፣ አሁን መጸዳጃ ቤት የመሄጃ ሰዓት ነው።”] ልጁ ሽንት ቤት ላይ ለአጭር ጊዜ እንዲቀመጥ ማድረግ)። ሽንት ቤት ላይ የተቀመጠውን ልጅ እና በክፍሉ ውስጥ ያሉ ሌሎች ልጆችን ለማየት በሚያሥችል ቦታ ይሁኑ።<br><br>37b. የተወሰኑ የመመገብ፣ የመልበስ እና የንጽህና ተግባሮችን ማከናወን<br>*ለምሳሌ፣*<br>• እጅ ለመታጠብ ቧንቧ ላይ እጅን ማድረግ።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ቀላል የሆኑ ስራዎችን ሲያከናውኑ አወንታዊች ልምዶችን ይስጡ (ለምሳሌ፣ መዝሙር መዘመር እና አወንታዊ ንግግር)።<br>• ልጆች ለራሳቸው አንዳንድ ነገሮችን ሲያደርጉ መቀበል እና ጠቃሚ ምክሮችን ማቅረብ።<br><br>37c. ለእድገት ተገቢ የሆነ፣ ከአዋቂዎች እና ሌሎች ልጆች ጋር አስተማማኝ የንኪኪ ባህርያቶች ላይ መሳተፍ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ሌላ ልጅ ማልቀስ ሲጀምር፣ ተንከባካቢያቸው እንደሚያደርጉት ልጁን በቀስታ መታ መታ ማድረግ።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ተገቢ የሆኑ የንክኪ ባህርዮችን፣ እንደ ማቀፍ፣ ሃይ ፋይቭ፣ ወዘተ ያሳዩ።<br>• ተገቢ ያልሆኑ የመንካት ባህርዮችን ተገቢ የሆነ እርምጃዎችን እንደሚያስከትሉ ማሳየት (ለምሳሌ፣ ተንከባካቢ ሆነው ልጁ ሲመታቹ፣እንዲህ ይበሉ፣ “Ouch! [“አውች!] That hurts me. [ያ እኔን ይጎዳኛል።] don’t want to play anymore.” [እኔ ከአሁን በኋላ መጫወት አልፈልግም።”])።<br>• የልጆችን የመነካት ምርጫዎችን ማክበር።<br><br>37d. የሚታመኑ አዋቂ ሰዎችን መለየት እና እርዳታ የሚፈልጉ መሆኑን በቋንቋ ወይም ደግሞ በአካል መግለጽ<br>*ለምሳሌ፣*<br>• ከተጎዱ ወይም እርዳታ ከፈለጉ ከሚታወቅ ሰው እርዳታ መጠየቅ/ወደሚታወቀው ሰው መሄድ።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• የልጅን የእርዳታ ጥያቄን በተረጋጋ ሁኔታ እና ለሁኔታው ምላሽ በሚሰጥ ውጤታማ መልኩ መመለስ።<br>• በመማርያ ክፍል ውስጥ የተለያዩ የክፍሉ ልጆችን ተቀባይነት ያላቸው ባህርዮችን በማሳየት ማህበራዊ ስሜትን መፍጠር። |

<table>
<tr><th>ቅድም ትምህርት ቤት</th><th>ቅድመ መዋእለ ህጻናት ለመውጫ የሚጠበቁ ነገሮች</th><th>መዋእለ ህጻናት የመውጫ ተስፋዎች</th></tr>
<tr><td>አመላካቾች</td><td>አመላካቾች</td><td></td></tr>
<tr><td>
37a. አልፎ አልፎ እያስታወሷቸው፣የታወቁ የጤና እና የደህንነት ህጎችን ይተገብራሉ<br>
ለምሳሌ፣<br>
• አስተማሪው እጃቸውን ሸፍነው ሲያስነጥሱ ሲያዩ እንደዚያ ማድረግ።<br>
ደጋፊ ልምዶች፣<br>
• ጤናማ ልምዶችን ማሳየት፣ እንደ ለመናፈጥ ሶፍት መጠቀም።<br>
<br>
37b. መሰረታዊ ራስን የመርዳት ተግባሮችን ከእገዛ ጋር ያከናውናሉ<br>
ለምሳሌ፣<br>
• ለመሽናት ፓንትን ወደ ታች ማውለቅ፣ ዚፑ ላይ እርዳታ ሊፈልጉ ይችላሉ።<br>
ድጋፍ ሰጭልምዶች፣<br>
• መሰረታዊ የራስን መርዳት ተግባሮችን እንዲያከናዉኑ በቂ ጊዜ መስጥት።<br>
• መልበስን ቀላል የሚያደርጉ ቴክኒኮችን ማስተማር (ለምሳሌ፣ ጃኬቶችን ከላይ ወደ ታች እና በጭንቅላት ላይ በማድረግ መልበስ)።<br>
<br>
37c. በራሳቸው ሰውነት እና በሌሎች ሰውነት መካከል ያለውን የአካል ገደቦች ማስተዋል።<br>
ለምሳሌ፣<br>
• የአንድን ሰው እጅ መገፍተር ወይም በሆነ አይነት መልኩ ሲያዙ ወይም ሲነኩ “No” [“አይ”] ብሎ መናገር።<br>
ድጋፍ ሰጭልምዶች፣<br>
• በልብስ የሚሸፈኑ ሚስጥራዊ የሰውነት አካሎችን አስመልክቶ ማውራት እና ማንም ሰው እነሱ ካልፈለጉ የልጆችን ሰውነት የመንካት መብት እንደሌለው መንገር።<br>
• ለልጆች ምልክቶች ምላሽ መስጠት እና የእርስ በርሳቸውን ምልክቶች እንዲለዩ እና ምላሽ እንዲሰጡ መርዳት።<br>
• ስለመነካት የልጆችን ምርጫዎች ማወቅ እና ማክበር።<br>
<br>
37d. የሚታመኑ አዋቂ ሰዎችን ይለያሉ እና ያንን ሰው እርዳታ እንዴት መጠየቅ እንደሚችሉ እና አንድ ችግር ሲከሰት እርዳታ እንዴት እንደሚያገኙ ይረዳሉ<br>
ለምሳሌ፣<br>
• አስተማሪ ወይም ሞግዚት የነሱን ደህንነት የሚጠብቅ ሰው ስለመሆኑ መግለጽ።<br>
ድጋፍ ሰጭልምዶች፣<br>
• ስለ አስተማሪዎች እና ሌሎች በክፍሉ ውስጥ እና በህንጻው ያሉ አዋቂዎች ሚናዎች ማውራት።<br>
• ያልተጠበቁ ሁኔታዎ ሲፈጠሩ በክፍል ውስጥ አወንታዊ ሁኔታን መፍጠር።
</td><td>
ጤንነት እና ደህንነት<br>
<br>
37a. መሰረታዊ የጤንነት እና የደህንነት ህጎችን ይገልጻሉ እና ይተገብራሉ<br>
ለምሳሌ፣<br>
• ሌሎችን ልጆች እንዳይገጩ በባለሶስት እግር ሳይክል ሲሄድ አንዱን አቅጣጫ ይዘው መሄድ እንዳለባቸው መግለጽ።<br>
ደጋፊ ልምዶች፣<br>
• ልጆችን የጤንነት እና የደህንነት ህጎችን አስመልክቶ ባለ ውይይት ላይ ማሳተፍ።<br>
<br>
37b. በአነስተኛ እርዳታ እራስን የመርዳት ተግባሮችን ማከናወን<br>
ለምሳሌ፣<br>
• መጸዳጃ ቤት ከገቡ በኋላ ሽንት ቤቱ ላይ ውሃ መድፋት እና እጅ መታጠብ።<br>
ደጋፊ ልምዶች፣<br>
• የእጅ አስተጣጠብ ደረጃዎችን የሚያሳይ የስእል እና የቃል ቻርቶችን መስራት።<br>
<br>
37c. አካላዊ ወሰኖችን አስመልክቶ ፍቃድ ምን እንደሆነ መለማመድ።<br>
ለምሳሌ፣<br>
• ለማቀፍ የክፍል ልጅ ጋር መጠጋት ነገር ግን ልጁ ፊቱን ሲያዞር ወይም እጆቹን ሲይጣምር ማቆም።<br>
ድጋፍ ሰጭልምዶች፣<br>
• ለልጆች ፍቃድ ምን እንደሆነ ማስተዋወቅ እና ማለማመድ በ “ሳይመን ሴይስ” የሚለውን ጨዋታ በማሻሻል።<br>
• ለህፃናት ምልክቶች ምላሽ ይስጡ እና እርስ በእርስ የእያንዳንዳቸውን ምልክቶች እንዲለዩ እና ምላሽ እንዲሰጡ ይርዷቸው።<br>
• መንካትን በተመለከተ የልጆችን ምርጫዎች ይወቁ እና ያክብሩ።<br>
<br>
37d. እምነት የሚጣልበት አዋቂ ሰው የሚያስፈልግበትን ሁኔታዎችን ይለያሉ እና እርዳታ ሲጠየቅ ምን እንደሚፈጠር ወይም ደህንነትን አስመልክቶ ሪፖርት ሲደረግ የሚሆነውን ያውቃሉ<br>
ለምሳሌ፣<br>
• ደህንነት ሳይሰማቸው ሲቀር ወደ አስተማሪ መሮጥ እና መንገር።<br>
ድጋፍ ሰጭልምዶች፣<br>
• ልጁ ሪፖርት ያደረገውን የደህንነት ስጋቶች በረጋ መንፈስ ምላሽ ይስጡ እና ሁኔታውን ውጤታማ በሆነ መንገድ ይፍቱ።<br>
• በመማሪያ ክፍል እና በህንፃው ውስጥ ስላሉ አስተማሪዎች ወይም አዋቂዎች ሚናዎች ይናገሩ።
</td><td>

</td></tr>
</table>

| የአካል እድገት ፣<br>ጤና እና ደህንነት | ጨቅላ ህጻናቶች | ታዳጊዎች | ሁለት አመት ልጆች |
|---|---|---|---|
| መስፈርቶች | አመላካቾች | አመላካቾች | አመላካቾች |
| 38. አወንታዊ የአመጋገብ ባህርዮችን፣ ከፍተኛ የምግብ መቀበል ክህሎቶችን፣ የምግብ አወሳሰድን ራስ መቆጣጠርን፣ የታቀዱ የምግብ ምርጫዎችን እና አወንታዊ የሰውነት ምስልን በመጠበቅ ብቃት ያለው የአመጋገብ ባህርዮችን ማሳየት | 38a. ምላሽ ከሚሰጡ የአመጋገብ ልምዶች ጋር የሚጣጣሙ የረሃብ እና የጥጋብ ምልክቶችን ያሳያሉ<br>*ምሳሌዎች፣*<br>• ወደ ምግብ በመንጠራራት ወይም በማመልከት የረሀብ ምልክቶችን ማሳየት፣ ምግብ ሲቀርብ ደስታን መግለጽ፣ ለመጉረስ አፍን መክፈት፣ የምግብ ፍላጎትን ለማሳየት የፊት ምልክቶችን ወይም ድምጾችን መጠቀም።<br>• መመገብን በመቀነስ ፣ ምግብን በመግፋት ፣ አፍን በመዝጋት እና/ወይም በፊት መግለጫዎች ወይም በድምጽ መጥገባቸውን መግለጽ።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• አስደሳች፣ ሞቅ ያለ እና እንክብካቤ የሚሰጥ የምግብ አካባቢን ማቅረብ።<br>• ልጅን ተንከባካቢውን እና ሌሎችን ፊት ለፊት የሚያይበት ምቹ ቦታ ላይ ማስቀመጥ።<br>• ከአመጋገብ የሚጠበቁ ግልጽ እና ወጥ የሆኑ<br>• ተገማች የሆነ የአመጋገብ መርሃግብሮች ምግብ በሚቀርብበት ጊዜ ልጅ የራበው መሆኑን ለማረጋገጥ ይረዳሉ።<br>• ገንቢ የሆኑ እና ለእድገት ተገቢ የሆኑ መጠጦች እና ምግቦች ያቅርቡ።<br>• ለልጁ የረሃብ እና የጥጋብ ምልክቶች ወዲያውኑ ምላሽ ይስጡ። | 38b. የራሳቸውን የረሃብ እና የጥጋብ ምልክቶችን ማሳደጋቸውን ለመቀጠል ፣ ለተለያዩ ምግቦች ገለልተኛ ተጋላጭ ለመሆን እና የግል የምግብ ምርጫዎችን ለማሳደግ በመሰረታዊ የአመጋገብ እና የምግብ ጊዜያቶች ይሳተፋሉ።<br>*ምሳሌዎች፣*<br>• እራስን ለመመገብ ተገቢ የሆኑ የምግብ ቁሳቁሶችን እንደ የህጻን ማንኪያ፣ የታዳጊ ሳህኖች እና የህፃን መጠን ያላቸውን ኩባያዎች መጠቀም።<br>• በምግብ ሰዓት ከሚቀርቡ የተለያየ አይነት ምግቦች፣ጤናማ ምግቦችን እና የተለያየ ይዘት፣ ጣእሞች፣ወዘተ ያላቸውን ምግቦች ይምረጡ።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• መደበኛ የምግብ ጊዜ መመስረት። ጥቂት ሀሳብ የሚበትኑ ነገሮች ያለበት (ለምሳሌ፣ ከቴሌቪዥን ወይም ሌሎች ሀሳብ የሚበትኑ ስክሪኖች ውጭ) ከውጥረት ነጻ በሆነ አካባቢ ያልተጣደፈ ምግብ ወይም መክሰስ መመገብን ለማወቅ ጊዜ መውሰድ።<br>• ከልጆች ጋር በቤተሰብ የአመጋገብ ዘዴ መሳተፍ፣ በቃል እና ያለቃል ለሚያቀርቡት ጥያቄዎች ምላሽ ይስጡ። ለረሀብ እና ጥጋብ ምልክቶች ትኩረት መስጠት።<br>• በልጆች ፊት አወንታዊ የሆነ የአመጋገብ ባህርዮችን ማሳየት። በተጨማሪ በልጆች ፊት ስለ ምግብ እና የሚጠጡ ነገሮች አሉታዊ የሆኑ አስተያየቶች፣ የፊት መግለጫዎች እና/ወይም ምላሾችን ከመስጠት መቆጠብ አስፈላጊ ነው። | 38c. አወንታዊ የአመጋገብ ባህርያትን የሚማሩበትን እና የምግብ አወሳሰዳቸውን እራሳቸው በመቆጣጠር ላይ በመላቅ የአመጋገብ ብቃታቸውን ማሳደግ መቀጠል<br>*ምሳሌዎች፣*<br>• ሲጠግቡ እና/ወይም ተጨማሪ ምግብ ሲፈልጉ የቃል ምልክቶችን መጠቀም።<br>• እራሳቸውን ማገልገል መለማመድ፣ እንደ ወደ ኩባያ መቅዳት ወይም ሰላጣ ለራሳቸው ለማቅረብ ሹካዎችን መጠቀምን።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ከልጆች ጋር በቤተሰብ የአመጋገብ ዘዴ መሳተፍ፣ በቃል እና ያለቃል ለሚያቀርቡት ጥያቄዎች ምላሽ ይስጡ።<br>• የልጅን የጥጋብ ምልክቶችን ማክበር። ልጅ ከተቃወመ አዲስ ምግብ እንዲጀምር ወይም ሰሀኑን እንዲጨርስ ግፊት አለማድረግ።<br>• የተለያዩ አይነት ምግቦችን ከሁሉም የምግብ ቡድኖች (ፍራፍሬዎች፣ አትክልቶች፣ ስጋዎች/ፕሮቲን፣ የወተት ተዋጾአ፣ ጥራጥሬዎችን) በምግብ እና መክሰስ ለማቅረብ ማቀድ።<br>• 38d. በመለማመድ ምግብን መቀበል መማር (ለማይታወቁ ምግቦች ገለልተኛ የሆነ ተደጋጋሚ ተጋላጭነት)፣ የምግብን ምርጫ በምልከታ መማር (የአቻን እና የተንከባካቢን የአመጋገብ ባህርያትን ማስመሰል) እና በምግብ ጊዜያት ማህበራዊነትን ማሳለጥ<br>*ምሳሌዎች፣*<br>• በምግብ ጊዜያቶች ተንከባካቢዎች ወይም አቻዎቻቸው ሲደሰቱባቸው የተመለከቷቸውን አዲስ ምግቦች ይሞክሩ።<br>• በምግብ ጊዜያቶች የሚቀርቡትን ምግቦች የተወሰኑትን መጥራት።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ለልጁ የምግብ ምርጫዎችን ለማስተካከል እንዲረዳ አንድ አይነት ምግብን ቢያንስ10–20 ገለልተኛ ለሆነ ለአንድ አይነት ምግብ ልጁን ተጋላጭ ማድረግ።<br>• በልጆች ፊት አወንታዊ የሆነ የአመጋገብ ባህርዮችን ማሳየት።<br>• በምግብ ማብሰል ትምህርቶች፣ በድራማዊ ጨዋታ፣ በጣእም ፈተናዎች እና ወደ ጓሮ እርሻዎች፣ እርሻ ወይም የገበሬ ገበያዎች እና ወደ ምግብ መደብሮች ጭምር በመጓዝ አዲስ ምግቦችን በስሜት ህዋሳት አማካኝነት የሚዳስሱበትን እድሎች ማቅረብ። |

| ቅድም ትምህርት ቤት | ቅድመ መዋእለ ህጻናት ለመውጫ የሚጠበቁ ነገሮች | መዋእለ ህጻናት የመውጫ ተስፋዎች |
|---|---|---|
| አመላካቾች | አመላካቾች | |
| 38e. ጠንቃቃ የአመጋገብ ልምዶች ላይ ራስን ችሎ መሳተፍ መጀመር<br>*ምሳሌዎች፣*<br>• የምግብን ምርጫ ለመወሰን የምግብን ውፍረት፣ ጣእም፣ መዓዛ እና እይታ መግለጽ።<br>• የራሳቸውን የረሀብ እና የጥጋብ ደረጃዎችን ማዳመጥ እና ለተንከባካቢያቸው መንገር።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ማናቸውንም ስክሪኖች (የቴሌቪዥንት፣ የስልኮች፣ ታብሌቶች፣ ወዘተ)፣ መጫወቻዎች ወይም ተመሳሳይ ሀሳብን የሚሰርቁ ነገሮችን በምግብ- እና በመክሰስ ጊዜያቶች ማስወገድ።<br>• ልጆች አወንታዊ የአመጋገብ ልምዶች እንደ የምግብ ጊዜ ስነምግባሮች፣ የረሀብ እና የጥጋብ ምልክቶችን መግለጽ እና የምግብ ጠረጴዛን ማዘጋጀት እና ማጽዳት እንዲለማመዱ መርዳት።<br>• በምግብ ጊዜዎች፣ በድራማዊ ጨዋታ እና ሌሎች የቀኑ ክፍሎች ወቅት ልጁ ሁሉንም የስሜት ህዋሳቶችን እንዲጠቀም መደገፍ።<br>• ልጅ ትንሽ ወይም የሚያስፈልገውን ያክል እንዲመገብ መፍቀድ።<br><br>38f. በልምድ የስነምግብ ተግባሮች ላይ መሳተፍ መጀመር።<br>*ምሳሌዎች፣*<br>• የሚሰጡት ስራዎች ከእድገት ጋር አግባብነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በአዋቂ ክትትል እየተደረገ በምግብ ማብሰል ትምህርቶች ላይ መሳተፍ።<br>• በጓሮ አትክልት ተግባሮች፣ ወደ አካባቢው ወዳለው እርሻ እና/ወይም ወደ ክፍል እርሻ ሲጓዙ ስለ እህል ማሳደግ ይማሩ።<br>• በምግብ ወቅት ስለተለያዩ የምግብ አይነቶች፣ በጠረጴዛ እንቅስቃሴዎች፣ በመጽሀፍ ንባብ፣ በድራማዊ ጨዋታ እና ሌሎች የቀኑ ክፍሎች ላይ ይማሩ።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• ልጁ ያልተለመዱ ወይም አዲስ ምግቦችን በራሳቸው ፍጥነት እንዲያስሱ እና እንዲቀርቡ ይፍቀዱ።<br>• ልጆች ፊት አወንታዊ የአመጋጋብ ባህርያቶችን ያሳዩ (ለምሳሌ፣ በምግብ ወቅት፣ አስተማሪው "This milk is tasty." ["ይህ ወተት ጣፋጭ ነው።"] ይላል፣ ከዚያ ፣ "Did you know that milk makes your bones strong?" ["ወተት አጥንቶቻችሁን ጠንካራ እንደሚያደርግ ታውቃላችሁ?"] ብሎ ይጠይቃል።<br>• ስለምግብ ጥቅሞች ልጆችን በወሬ ያሳትፏቸው (ብዙ ክፍት የሆኑ ጥያቄዎችን ይጠቀሙ እንደ፣ "Can you name food that comes from a plant?" [" ከአትክልት የሚገኝ ምግብ መጥራት ትችላላችሁ?"])። | 38g. አወንታዊ የአመጋገብ ባህርዮችን ያሳዩ<br>*ምሳሌዎች፣*<br>• ሲራቡ፣ ሲጠሙ ወይም ሲጠግቡ ያስተውሉ እና ይግለጹ።<br>• ከምግብ ጋር ገለልተኛ የሆነ ግንኙነት ያሳዩ (ምግብ "መጥፎ " ወይም "ጥሩ" አይደለም ምክንያቱም ሁሉም ምግቦች ለሰው ሀይል ይሰጣሉ እና እንዲያድጉ ይረዳቸዋል)።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• አዎንታዊ የአመጋገብ ባህርዮችን ያሳዩ (ለምሳሌ፣ "I am full from our lunch today." ["በዛሬ ምሳ ጠግብያለሁ።"] ይበሉ)።<br>• በምግብ ጊዜ በምግብ ወሬ ተሳተፉ።<br><br>38h. ምግብ ሰውነታችንን ጠንካራ እና ጤናማ ሆኖ እንዲቆይ ምግብ ስላለው ሚና መሰረታዊ መረዳትን ማሳየት<br>*ምሳሌዎች፣*<br>• ምግቦችን በቀለሞች፣ በጣእሞች እና መሰረታዊ የምግብ ቡድኖች ይመድቡ (ከአትክልቶች የሚገኙት ምግቦች ምንድን ናቸው፣ ከእንስሶች ምን ይገኛሉ፣ ወዘተ)።<br>• ምግብ ሀይል እንደሚሰጠን እና ሰውነት እንዲያድግ እንደሚረዳ ያስተውሉ።<br>*ድጋፍ ሰጭልምዶች፣*<br>• በድራማዊ የጨዋታ ስፍራ ላይ ልጆች እንዲያስሱ እንዲረዳቸው የተለያዩ አይነት የጨዋታ ምግብ ይኑሮት።<br>• ምግብ በሰውነታችን ላይ ስለሚኖረው ሚና ልጆችን ያሳትፏቸው (ለምሳሌ፣ "Which among the food in the dramatic play area comes from plants?" [" በድራማዊ የመጫወቻ ስፍራ ላይ ካሉት ምግቦች ከአትክልቶች የሚገኝ ምግብ ምንድን ነው?"] ብለው ይጠይቁ )። | |



# ማስታወሻዎች


ABC

Office of the State Superintendent of Education (የክልል የትምህርት ቢሮ የበላይተቆጣጣሪ)
1050 First Street, NE, Washington, DC 20002

osse.dc.gov
facebook.com/ossedc
@OSSEDC
(202) 727-6436

WE ARE WASHINGTON DC
GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
MURIEL BOWSER, MAYOR